
# ሐመር


## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

መጀመሪያ ዓመት ቁጥር 6

ጥቅምት 1986 ዓ.ም.



- ስለክርስቶስ የተቃዋሚዎች ጥያቄና መልሶቻቸው
- ኃጢአቴን ለካህን ባልናገርስ?
- ውጊያው
- ከቦረዳ ዋሻ ጽላት ወጣ



- መዳን በክርስቶስ ብቻ ነው
- ትዳርና ሕይወት (ቃለ መጠይቅ)
- ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል

# አስደሳች ዜና

**የማኅበረ-ቅዱሳን መዝሙርና ሥነ - ጽሑፍ ክፍል አዲስ ያሬዳዊና ኦርቶዶክሳዊ መዝሙር አዘጋጅቷል ይህንኑ ለምዕመናን ስናስታውቅ ካሴቱ በቅርብ ጊዜ በገበያ ላይ የሚውል መሆኑን በታላቅ መንፈሳዊ ደስታ እየገለጥን ነው ።**

**የማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት**

## አስደሳች ዜና ለምእመናን ፤

አከራካሪ በሆኑ መንፈሳዊ ርዕሶች ላይ አሳማኝ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ የሚሰጥ መንፈሳዊ መጽሐፍ በቅርቡ በገበያ ላይ ውሏል ።

«ኖኅተ ሃይማኖት» የሚል ስያሜ ይዞ የወጣው ይህ መጽሐፍ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን የምታምነውን ትክክለኛ እምነት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ያቀርባል ፤—

በመጽሐፍ ውስጥ ከተካተቱት ጥቂቱን ብንጠቅስ ፤

— መንፈስ ቅዱስ
— የቅዱሳን መላእክት አማላጅነት
— ተዝካርና ፍትሐት
— መጭው አውሬ (666)

ሌሎችንም ርዕሶች ፤ ይዟል ። የመጽሐፉ ቅጂ ብዛት አነስተኛ ስለሆነ ሳያልቅብዎት ተሽቀዳድመው በእጅዎ እንዲያስገቡ እንመክረዎታለን ።

መጽሐፉን በጅምላ ለማከፋፈል ለምትፈልጉ ግቢ ገብርኤል በሚገኘው ዓመደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት ዘወትር ከ10.00 ስዓት በኋላ ብቅ ማለት ትችላላችሁ ።

የመጽሐፉ አዘጋጅ ብርሃኑ ጐበና ።

| የጥያቄአችን መልስ |
|---|
| ጥያቄ ሴት የምታሸንፋቸው ሁለት አሸና ፊዎች እነማንናቸው ? |
| መልስ ወይንና ንጉሥ |
| ዕዝራ ካልዕ 4፥1 - ፍፃሜው |

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሐመር

መጀመሪያ ዓመት ቁጥር 6

ጥቅምት 1986 ዓ.ም.


## ይዘት


ከአዘጋጁ ............................... 1

የማኅበሩ መልእክት ................. 2

ደብዳቤዎቻችሁ ...................... 3

ትምህርተ ሃይማኖት

✣ ስለክርስቶስ የተቃዋሚዎች ጥያቄና መልሶቻቸው .............. 5

✣ መዝሙርና ምሥጢራዊ ሥርዓቱ ........ 7

✣ እመአምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ .... 8

የጥያቄዎቻችሁ መልስ

✣ ኃጢአቴን ለካህን ባልናገርስ? .... 9

ኪነጥበብ

✣ ውጊያው ......................... 13

✣ ማዳኑን ያዩ ይናገሩ ............... 16

እናስተዋውቃችሁ

✣ ከቦረዳ ዋሻ ጽላት ወጣ ........... 17

መታዘዝ ይበልጣል (ስብከት) ........ 19

ዓምደ ወራዙት

✣ ካልባረክኸኝ አልለቅህም .......... 21

✣ መዳን በክርስቶስ ብቻ ነው ....... 23

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

✣ ትዳርና ሕይወት (ቃለ መጠይቅ) .... 25

በረከተ ወንጌል

✣ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል .. 28

✣ አማላጅ አብጁ (ግጥም) .......... 29

ስብከት

✣ እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው ...... 30



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክንን ትምህርተ ሃይማኖት፥ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ


# ከአዘጋጁ

## እንኳን ለዘመነ ማርቆስ አደረሳችሁ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

«ቀኑ የአንተ ነው፥ ሌሊቱም የአንተ ነው፥ አንተ ፀሐይንና ጨረቃን አዘጋጀህ፥ አንተ የምድርን ዳርቻ ሁሉ ሠራህ በጋንም ክረምትንም አንተ አደረግህ»

መዝ.73፥16–17።

ሰዎች ሁላችን በተሰጠን ጸጋ እግዚአብሔርን እያመሰገንን እንኖር ዘንድ ጊዜያትን እርሱ እግዚአብሔር ፈጠረልን። የተለያዩ ወቅቶችንም ማንም ሊመረምረው በማይችል ጥበቡ አዘጋጀ። ሥጋዊ የሆነው ፍጥረታዊው ማንነታችን በእነዚህ የጊዜ ሁኔታዎች እንዳይሰለች ጌታችን በረቀቀ ዕውቀቱ አንዱ ሲያልፍ አንዱን እየተካ ዘመናችንን ሳንጠግብ እንድንኖር አድርጓል።

በተለያየ የኑሮ ደረጃና ሁኔታም ወቅቶችን እንዲህ እየተለዋወጡ ዘመን አልፎ ዘመን እየተተካ ያለፈውን ዓመት ፈጽመን ወደዚህኛው ስንገባ ከአሮጌ ወደ አዲስ ዘመን የተዘዋወርን ይመስለናል። እንደዚያም ይሰማናል። ስለዚህም በሀገራችን «እንኳን ከአሮጌው ወደ አዲሱ ዘመን አሸጋገረህ(ሽ)» መባባል ልማዳችን ነው። በውኑ ግን ዘመን አርጅቶ አዲስ ዘመን ይተካ ይሆን? ወይስ ለዚህ የዘመናት በጊዜ ገደብ መፈራረቅ የተሰጠው ትርጉም የተሳሳተ ወይም ያልተገባ ይሆን? ዘመን ያረጃል አዲስ ዓመት ይመጣል የሚባል ከሆነ ሲገባ አዲስ ያልነው ዘመን ሳንጠግበው አሮጌ መባሉ ይገርማል። ሲያልቅ አሮጌ ከተባለ ከኖርንባቸው ዘመናት ሁሉ አንድ ስንኳ ያላረጀ የሌለ ሲሆን የማናውቀውና ያልኖርንበት ዘመን ሁሉ ዛሬ አዲስ ከሦስት መቶ ስድሳ አምስት (365) ቀናት በኋላ አሮጌ መሆኑ ነው።

ዘመናት የእግዚአብሔር ሥራዎች ናቸው። ማርጀት የለባቸውም። አዲስና አሮጌም አይባሉም። በዘመናት ውስጥ እንደሚገባው ሊመላለስ ያልቻለና የተሰጠውን ጸጋ ሊጠቀም ያልቻለ ሕይወት፥ በራሱም ላይ የመንፈስ መታደስን ጨምሮ የጽድቅ ፍሬን ማፍራት ያልቻለ ሕይወት እርሱ በኃጢአት ምክንያት አርጅቷል። በንስሐም መታደስ ይገባዋልና ባለፈው ዘመን ራሱን ያላነጻ በዚህኛው ዘመን ራሱን ያነጻ ዘንድ በአዲስ ተስፋና መንፈስ ሊነሣ ይገባዋል። ምድሪቱም ላለፈው ዓመት የሚጠበቅባትን ፍሬ ትሰጣለች። በዚህኛውም ዓመት እንዲሁ ሌላ ፍሬ ለማፍራት ታስባለች። የሚገባትን መስጠት ባቋረጠች ጊዜ አረጀች ትባላለች። ምድርን የተመሰለው የሰው ልጅ ሕይወትም ባለፈው ዓመት ካፈራው መልካም ፍሬ በተጨማሪ በዚህኛውም ዓመት መልካም ፍሬ ማፍራት ይጠበቅበታል። መልካም ፍሬ ያልተገኘበት እርሱ አርጅቷልና ዳግመኛ በንስሐ መታደስና አዲስ ፍሬ ምግባር፥ ፍሬ ሃይማኖት ማፍራት ይኖርበታል። እንግዲህ ዘመናትን አዲስ አሮጌ በማለት ብቻ ራሳችንን ሳናሞኝ በኃጢአት ያረጀውን ማንነታችንን በንስሐ አጥበን ቃለወንጌልን በመልበስ አዲስ እናድርገው፤ ለዚሁ የበቃን እንሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን።


ዋና አዘጋጅ – ብርሃኑ ጎበና ካሣ

ም/ዋና አዘጋጅ – ዲ.እሸቱ ታደሰ ወንድም አገኘሁ

✉ 80078

☎ 12 34 25

አዲስ አበባ


©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የማኅበሩ መልእክት

## በጽድቅ ስም ተሰባስቦ ኃጢአት መሥራት ቅጣቱ ከባድ ነው

በዓለማችን ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያስደስቱና ለሰው ልጆች የሚጠቅሙ ተግባራት ለመፈጸም ጥረዋል ይጥራሉም። ከነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹ በየምክንያቱ ዕቅዳቸው ሳይሳካላቸው በጅምሩ ሲቀር እንመለከታለን። ለዚህም ትልቁ ምክንያት በፈቃደ እግዚአብሔር አለመመራትና የተነሡበትን የጽድቅ መንገድ ዐውቀውትም ይሁን ባለማወቅ ወደጐን በመተው የተሳሳተ መንገድ መያዝ ነው።

ምንም እንኳ በፈቃደ እግዚአብሔር የሚመራ ቢሆንም የጽድቅ ሥራ ሁል ጊዜ ብዙ ፈተናዎች ይገጥሙታል። ለጽድቅ ሥራ የተዘጋጀ ማንኛውም ሰው ፈተና ሲያጋጥመው ማሰብና ማስተዋል ያለበት ጽድቅ በመስቀል ላይ በተፈጸመው የክርስቶስ መሥዋዕትነት የተገኘ መሆኑን ነው። ፈተናውንም በጽድቅ ጌታ በእግዚአብሔር አጋዥነትና በመስቀሉ ኃይል ለመወጣት መዘጋጀት ይኖርበታል።

በመሠረቱ ሰዎች ለጽድቅ ሥራ በሚነሣሡበት ጊዜ ብቻቸውን አይሆኑም እግዚአብሔር አብሯቸው ይሆናልና። ከዚህም በተጨማሪ በመንፈስ ቅዱስ ቀስቃሽነት ለተመሳሳይ አገልግሎት የተሰማሩ ሰዎች አብረዋቸው ይሰለፋሉ፤ ስለጽድቅ ሥራም ይዋያያሉ፥ ስለፍጻሜውም በኅብረት ይጸልያሉ። የሐዋ.4፥32።

በተለይም ሰዎች ከፈቃደ እግዚአብሔር ውጭ እንዳሻቸው የሚጓዙ፤ ባለማወቃቸው ለሃይማኖት ደንታ የሌላቸው፤ እምነታቸውንና የእምነታቸውን ሥርዓት እንደፈለጉ የሚለዋውጡ ሆነው በተገኙበት በአሁኑ ጊዜ የጽድቅ ሥራ ለመሥራት መሰባሰብ እጅግ አስፈላጊ ነው። ዕብ.10፥24።

የጽድቅ ሥራ ማለት ሃይማኖትን በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ–ቢጽ (ወንድምን በመውደድ) መግለጽ ነው። በሌላም በኩል በፈቃደ እግዚአብሔር መመራት ማለት ነው። ፈቃደ ሥጋን ወይም ዓለምን የሚያስደስት ነገር መፈጸም በፍጹም የጽድቅ ሥራ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሁለቱ የማይስማሙና የሚቃረኑ መሆናቸውን ገልጿል። ገላ.5፥16–18። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ትምህርቱ የጽድቅ ሥራ ሌላ የዓለም ሥራ ሌላ መሆኑን አስተምሯል። ማቴ.6፥24። በተጨማሪም በጽድቅ ስም ተሰብስቦ ኃጢአት የሚሠራ ሁሉ ከፍሬው እንደሚታወቅ በማስተማር ማንም ራሱን ሊሰውር ቢጥር መጥፎ ሥራው እንደሚገለጥበት ነግሮናል።

ስለዚህ በጽድቅ ስም ተሰባስቦ ኃጢአት መሥራት ቅጣቱ ከባድ መሆኑን አስቀድሞ ማወቅና መገንዘብ ይገባል። ቤተ–ክርስቲያንን ለመገንባት ተነሥቶ አፍርሶ መገኘት፥ ሃይማኖት ለመጠበቅ ተዘጋጅቶ ለውጦ መገኘት ከሁሉ የከፋ ኃጢአት ከመሆኑም በላይ በቤተክርስቲያን ጉዞም ላይ መሰናክል ማስቀመጥ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለጽድቅ ሥራ ተጠርተው በኋላ ግን ዓላማቸውን ለመጠበቅ ያልዋሉትን እንዲህ ይላቸዋል «አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ሰማያዊውን ስጦታ የቀመሱትን በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው። ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታል፥ ያዋርዱታልም።» ዕብ.6፥4–6።

በመሆኑም ለጽድቅ ሥራ የተዘጋጀ ሁሉ የተሰለፈበትን ዓላማ ከፍጻሜው ለማድረስ እንዲችል ኃይልን ይሰጠው ዘንድ ዘወትር አምላኩን ከመማፀን ማቋረጥ አይገባውም።

ማኅበራችንም ይህንን የጽድቅ ሥራ ለመፈጸም የተነሣ ነውና ሰው ሠራሽ የሆነ ለዓለም የሚመች ከንቱ ዓላማ የለውም። ይህ ካልሆነ ግን የጽድቅ አባት ያልተከለው ነውና መነቀሉ አይቀርም። ኢያሱ ከሙሴ እግር ሥር እየተከተለ ተምሮ በረከትን እንዳገኘ ሁሉ ማኅበራችንም ዓላማው ከቤተክርስቲያን አባቶቻችን እግር ሥር ሆኖ ቤተክርስቲያንን ለማገልገልና ለመታዘዝ ከነርሱም ተምሮ በረከታቸውን ለመቀበል ነው።

በአንጻሩ የማኅበራችን ዓላማ ያልገባቸው አንዳንድ ሰዎች ማኅበሩ ከተነሣበት ዓላማና ከሚሰጠው አገልግሎት ውጪ የተለየ ስም በመስጠት ሲናገሩለት ይሰማል፤ የሌሎች ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች መጠቀሚያና መሣሪያ የሚመስላቸውም አሉ። ይሁን እንጂ ማኅበሩ ሊያገለግል የተነሣነው ክርስቶስን ሊታዘዝ የተነሣው የቤተክርስቲያናችንን አባቶች ብቻ እንጂ ለማንም መጠቀሚያና መሣሪያ አይደለም፤ አይሆንምም። ይሆንም ዘንድ ክርስትናው አይፈቅድለትምና።

ከዚህም ሌላ ለጽድቅ ሥራ በቤተክርስቲያን ለመሰባሰብ መሥፈርቱ ግሪካዊ ወይም አይሁዳዊ ወይም ሌላ መሆን አይደለም፥ በቤተክርስቲያን እምነት፥ ሥርዓትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ተመሥርቶና ጸንቶ መገኘት ነው እንጂ። ቆላ.3፥11። አበው «ስንዴ ለመሥዋዕትነት የሚቀርበው ንጹሕ ስንዴ ሆኖ ስለተገኘ እንጂ ደጋ ወይም ቆላ ስለበቀለ አይደለም» እንዲሉ።

እግዚአብሔር የጽድቅን ሥራ በኃጢአት ለውጠን ከመገኘት ይጠብቀን፤ የእመቤታችን አማላጅነት አይለየን። አሜን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

በዚህ ዓምድ ከአንባብያን የተላኩ ገንቢ አስተያየቶችንና መንፈሳዊ ምክሮችን እናቀርባለን።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን። ይድረስ እግዚአብሔር አገልግሎታችሁን ላቃናላችሁ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች የእግዚአብሔር ኃይልና ተአምር በእናንተና በመለከት መጽሔት በማውጣቱ ጌታ ይመስገነው። መጽሔታችሁ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በመሆኑ ተወዳጅነት እያገኘ ከመሆኑም በላይ ለሌሎች ትምህርት እየሆነ መጥቷል።

ባለፈው የወጣው የአስከሬኖች ታሪክ በጣም ስለአስደሰተን የእግዚአብሔር ተአምር አያልቅምና በርቱበት እላለሁ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን:-አሜን።

በኃይሉ ተረፈ — ከሻሸመኔ

• እግዚአብሔር እንዲያበረታን በጸሎት ያስቡን።

✣ ✣ ✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን። ከሁሉ አስቀድሜ ሐመሮች እንደምን ከርማችኋል? እንደምን ከርማችኋል ስላችሁ ከቁጥር 1 ጀምሬ በሥራችሁ ስለማውቃችሁ አሁንም በበለጠ ወዳጅነታችን በዚህች አጭር ደብዳቤ ይጠንክር ለማለት ነው። ገባችሁ? በርቱ ጠንክሩ ለማለት ነው። ምክንያቱም ይህንን የመሰለ የተቀደሰ ሥራ በምትሠሩበት ጊዜ ምናልባት ዲያብሎስ እንዳይገባና አስተማሪአችንን ሐመርን እንዳያሰናክልብን ብዬ ስለምፈራ ነው። በተረፈ ሐመሮች ከተለያዩ ዋቢ መጻሕፍት ያገኛችሁትን ጠቃሚ ምክሮች አብሬ የላኩ ስለሆነ ጠቃሚ መስሎ ከታያችሁ እንደሚሆን አድርጓት።

የልዑል እግዚአብሔር ቸርነት አይለያችሁ

የእናንተው ያለው ተጋፋው

(ከወልድ ዋሕድ) ደሴ

• ለአስተያየቱና ማበረታቻው እናመሰግናለን። የላኩት ምክሮች ደርሰውናል ለወደፊቱም ድጋፍዎ አይለየን።

ይድረስ ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል። ጊዜዋን ጠብቃ የምትወጣውን መጽሔታችሁን ምንም አልፎ አልፎ ለማገር ባላገኛትም ለማንበብ ግን አልፎኝ አያውቅም። ከሚገባው በላይ ትምህርት ትሰጣለች፣ አእምሮን በማደስ መንፈስን ታረካለች፣ ሕይወትን ታስተካክላለች፣ በዚሁ ቀጥሉ እላለሁ።

እምቢአለ አያሌው — ባህር ዳር

• እግዚአብሔር ለመቀጠል እንዲያበቃን አብዝተው ይጸልዩልን።

✣ ✣ ✣

ሰላም ጤና ይስጥልኝ እንደምን አላችሁ ውድ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች። ለቸርነቱ ወሰን የሌለው ለልግስናው ይህ ቀረ የማይባለው እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን። እሰይ የተዋሕዶ ልጆች እንዲህ ነው እንጂ—በርቱ—በምክሯ፣ ድንቅ ቦታዎችን በማስተዋወቅ እየጠነከረች የመጣችው ሐመር አንድ ብላ ጀምራ እነሆ ከዚህ ደርሳለች በርቱ—ከእንግዲህ ወደኋላ የለም ሉቃ.9፥62።

የእመቤታችን የድንግል ማርያም የመላእክት የጻድቃን ሰማዕታት ድጋፍ አይለያችሁ። የሰላም ባለቤት በዝግጅታችሁ እየተገኘ «ሰላም ለሁላችሁ» እያለ ዝግጅታችሁን ያቃናላችሁ። በርቱ ጠንክሩ። ደህና እንሁን።

ፍሥሐ እንግዳወርቅ — ከድሬዳዋ

• አሜን! ከሁላችን አይለይ:- በጸሎትዎ ግን ዘወትር ያስቡን።

✣ ✣ ✣

ትድረስልኝ ለማኅበረ ቅዱሳን የሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል ሰላምታዬ ከያላችሁበት ትድረስልኝ።

«ሠናየ አገሪሆሙ ለእለ ይዜንው ሠናየ ዜና» ‹መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው› ይላል። ይህ የጥፋት ውኃ (ኑፋቄ) ባልበዛበት ወቅት (ለነበሩት ሐዋርያት) የተነገረ ሲሆን ፍጻሜው ግን ለእናንተም ይሆናል።

በአሁኑ ጊዜ የጥፋት ባሕር (ክህደት) በአጥለቀለቃት ዓለማችን እኛን ከስጥመት ለማዳን በኑፋቄው ባሕር ላይ የምትንሣፈፍ በመላው ሀገሪቱ የምትዘዋወር የማኅበረ ቅዱሳን መርከብ ናት። እናንተም በማቴ.10፥16።በተኩላዎች መካከል የተላካችሁ ስለሆነ ቃሉን ለማዳረስ እንደዕባብ ብልሆች እንደርግብም የዋሆች ሁኑ ተብላችኋልና በሥራችሁ ሁሉ እግዚአብሔር ረዳት ይሁናችሁ።

ዲ.ምትኩ አርጋው — ከቡታጅራ

• አሜን! ያለእግዚአብሔር ረዳትነት ከቶ ምን ሊሠራ—ብቻ ይጸልዩልን።

✣ ✣ ✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን። ይድረስ ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች:- እንደምን ሰንብታችኋል እያልኩ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ። ከሁሉም ከሁሉም ይህች የተዋሕዶ እምነታችን ጸንታና አብባ እንድትኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ናችሁና የእግዚአብሔር ፈቃዱና ቸርነቱ አይለያችሁ።

ዘነበ አየለ — ከጅማ

• አሜን:- ዘነበ መቼም ሥራው የእግዚአብሔረ ነውና ምሥጋናው ለርሱ ይሁን።

✣ ✣ ✣

ይድረስ ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል።

በመጀመሪያ ስለአገልግሎታችሁ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ምሕረት ይብዛላችሁ በማለት መልካም ምኞቴን ሳበሥር ከሙሉ ልቤ ነው። በመቀጠል ወደዋናው ቁም ነገር ስገባ እስከዛሬ ላለው እትማችሁ አንባቢአችሁ በመሆን ብዙ ዕውቀት ገበየሁ። ውስጣዊ የኃጢአት ስብራቴንና—ቁስለቴን አየሁ። «በረከተ ወንጌል» በምትለው ዓምዳችሁ በምታስተላልፉት ምክር አዘል ትምህርት ቁስሌም ጠገገ። ስብራቴም ተጠገነ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁንና አሁንም በእናንተው የሐመር መጽሔት ተሳታፊ ልሆን አንድ ትምህርትና አንድ ልብወለድ ይዤ ብቅ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ብያለሁ ቁምነገር አለው ካላችሁ አርሙትና አቅርቡት ካልሆነም አልቀየምም ለሁለተኛው እሻሻላለሁ።

እምሻው ዑመታ

ከወንጂ የሠራተኛ መንፈሳዊ ጉባኤ

● እምሻው፥ ለአስተያየቱ ስናመሰግን ጽሑፎቹ በሙሉ የደረሱን መሆኑን እየገለጥን ተራቸውን የሚጠብቁ መሆኑንም እንገልጻለን ታዲያ ተሳትፎዎን ይቀጥሉ።

✣ ✣ ✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

በመጀመሪያ ይህን ቀንና ሰዓት ባርኮ ለሰጠንና እያንዳንዷን ቀን ለዕድሜአችን ተጨማሪ አድርጐ ለሰጠን ለእርሱ ክብርና ምስጋና ይግባውና በኖኅ ዘመን ከመከራ እንዳወጣችው መርከብ ይህች «ሐመር» መጽሔትም ለተከተላትና ላወቀባት እንደመር ከቢቷ ናት። ታዲያ እናንተ ክቡራን የመጽሔቷ አዘጋጆች ለእኛም ለወንድሞቻችንም አጽናኝ መካሪ፥ እምነትን፥ ምግባርን፥ ሥርዓትን አስተማሪ ምርኩዝ በሆነችው ሐመር ደስታ ይገባችኋል። «በሰው ፊት ለሚ መሠክርልኝ እኔም በአባቴ ፊት እመሰክርለ ታለሁ» ብሏልና፥ በሉ በርቱ ተበራቱ ጠንክሩ እያልኩ የእግዚአብሔር አብ ጸጋ፥ የወልድ ቸርነት፥ የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከእኛ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን።

መ/ር ንብረት ገበየሁ

ከደምበጫ ጽ/አ/ቅ/ሚ/ሰ/ትቤት

● መ/ር፥ ስለምክርዎ እግዚአብሔር ይስጥልን። በተሳትፎዎ ይጠንክሩበት።

✣ ✣ ✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

ይድረስ ለማኅበረ ቅዱሳን የሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል በመጀመሪያ እናንተን ለዚህች መጽሔት አዘጋጅነት እኛንም ለአንባቢነት ያበቃን አምላክ ይክበር ይመስገን። አሜን።

ውድ አዘጋጆች ሐዋርያው ቅ.ጳውሎስ ለሮም ሰዎች በጣፈው መልእክቱ ሮሜ.10፥14 «ያለሰባኪ እንዴት ይሰማሉ ያልሰሙትንስ እንዴት ያምኑታል?» በማለት እንደጻፈው እነሆ ዛሬ መጽሔታችሁ ያለሰባኪ አስተማሪና መካሪ አጽናኝ በመሆን የተዋሕዶ ልጆችን አሰባስባ በማገናኘቷ ደስታችን ወሰን የለውም። ሆኖም ግን ጅምራችሁን ያሳመረ አምላክ ፍጻሜአችሁንም ያማረ እንዲያደርግላችሁ የዘወትር ምኞቴ ነው። እናም በርቱ ጠንክሩ፥ ግፉበት። የዕውቀት ምንጭ የሆነው አምላክ ለእኛ የምትለግሱትን ዕውቀት ያብዛላችሁ፥ አሜን።

ወጣት ብርሃኑ ገብሬ

ከየቡ ደ/ፀ/ቅ/ሚ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት

● አሜን፥ ምኞትዎን በአኩቴት ተቀብለናል።

✣ ✣ ✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

ይድረስ ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች እንደምን ሰንብታችኋል እያልኩ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ። ከሰላምታዬ በመቀጠል ይህን ያህል ተአምር የተሠራበት የመልከጸዴቅ ዋሻ እስከአሁን ሳይታወቅ፥ ተመልካችና ሰሚ አጥቶ መገኘቱ የሚገርም ነው። ይህን የመሰለ ስንት ይኖር ይሆን? እግዚአብሔር ይከተላችሁ፥ ሳትሰለቹ በዚሁ ቀጥሉበት:- ሐመር ብዙ ድንቅ ነገሮች እንደምታቀርብ እተማመናለሁ፥ እግዚአብሔር ይርዳችሁ በማለት ጽሑፌን እደመድማለሁ። ደህና ሁኑ። የእመቤታችን አማላጅነት አይለያችሁ።

ስንታየሁ ተሾመ — ከአላባ ቁሊቶ

● አሜን፥ ስንታየሁ ለአስተያየትዎ እናመሰግናለን።

✣ ✣ ✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ጸጋ ይብዛላችሁ:- የሐመር መጽሔት አዘጋጆች እንደምን አላችሁ? ቸሩ ፈጣሪ ልዑል እግዚአብሔር ፍቅሩን—ሰላሙን ያድላችሁ። ሐመሮች መጽሔታችሁ መታተም ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ለምከተለው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነቴ ጥንካሬና እውነትነትን አግኝቻለሁ፥ ሌላም የመዳኛ መንገድ እንደሌለ ከእርሷ ተምሬአለሁ—መንፈሳዊ ሕይወቴንም አዳብሬ አለሁ። ነገር ግን በማይገባኝ ምክንያት ከአዲስ አበባ ውጭ ብዙም አትገኝም:- ስለዚህ የቃሉ ጥማት ያለባቸው ሰዎች ማግኘት ስለሚፈልጉ በየክፍለ ሀገሩ ማድረስ የምትችሉበትን መንገድ ፈልጉ እላለሁኝ በቸር ያቆየን።

ደረጀ ዓባይነህ

ከባሌ—ሴሮፍታ

● ስለአስተያየቱ እያመሰገንን በተቻለን ግን ወደክፍለ ሀገር በመላክ ላይ መሆናችንን እንገልጻለን። በተጨማሪም በዚህ ጉዳይ ላይ የሚተባበረን ብናገኝ ደስ ይለናል።

✣ ✣ ✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

የተከበራችሁ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች እንደምን ከርማችኋል? መጽሔታችሁ ሐመር ከተቋቋመችበት ጊዜ ጀምሮ እውነትን በማስጨበጥ ረገድ ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ ላይ እንደምትገኝ ማንም ኦርቶዶክሳዊ የሚያውቀው ሐቅ ነው። በአካባቢያችን ለሚገኙ መናፍቃንም በቂ መልስ በመስጠት በውስጣቸው ያለውን መንፈስ እያቃጠለች ነውና በርቱ ተበራቱ:-እግዚአብሔር አምላክ በእናቱ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል አማላጅነት ይርዳችሁ።

ዘለዓለም ማሞ — ጊምቢ—ወለጋ

● ዘለዓለም እግዚአብሔር እንዲያበረታን በመጸለይና በመሳተፍ ይርዱን።

✣ ✣ ✣

## ለመጻጻፍ እንፈልጋለን

ስለመንፈሳዊ ነገሮች ከእኔ ጋር መጻጻፍ ለሚፈልጉ አድራሻዬ:-

ዘለዓለም ማሞ

ምዕራብ ወለጋ አስተዳደር አካባቢ

ወለጋ —ጊምቢ

የመ.ሣ.ቁ.68

✣ ✣ ✣

ከእኔ ጋር መንፈሳዊ ደብዳቤ መለዋወጥ የሚፈልግ ካለ በአድራሻዬ ይጻፍልኝ:-

እምቢአለ አያሌው

ፖ.ሣ.ቁ.137

ባሕር ዳር



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ትምህርተ ሃይማኖት

ይህ ዓምድ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማና ቀኖና) የምንማርበት ይሆናል።

ዮሐ.20፥17።

«ጌታ ኢየሱስም አትንኪኝ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና ነገር ግን ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬ ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ አለ በያቸው አላት።»

በዚህ ጥቅስ ውስጥ አትንኪኝ ገና ወደ አባቴ አላረግሁም፥ አባቴ አምላኬ የሚሉትን አባባሎች ማብራሪያ የሚያሻቸው ስለሆነ እዚህ ላይ እናትታለን።

1ኛ. ስለምን ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ አላት

አትንኪኝ ማለቱ ይህቺን ሴት ተጸይፏት አይደለም ስለሌላ ምክንያት እንጂ። ለዚህ አባባል የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። አንደኛው– ይህቺ ሴት ለጌታ ያላት ፍቅር ወሰን የሌለው ቢሆንም ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አድሬ እነሣለሁ ብሎ የተናገረውን ከልቡናዋ ሰሌዳ ላይ እንዳልጻፈችው እንረዳለን። ስለሆነም ፍቅርዋ ትንሣኤውን ከማመን ጋር የተዋሐደ አልነበረም ማቴ.12.ቁ.40። ዮሐ.2፥19–22።

ስለዚህ ጌታ ስለ እምነትዋ ማነስ እነሣለሁ ያለውን ቃሉን ስላላመነች ሊገሥጻት ፈልጎ ወደ አባቴ አልወጣሁምና ማለትም ገና አላመንሽብኝምና አትንኪኝ ብሏታል። ሁለተኛው ምክንያት ጌታ ስምዋን ጠርቶ ማንነቱን በገለጸላት ጊዜ የመሰናበቻው ጊዜ ማለትም ምድርን ለቆ በልዕልና በህልውና ወዳልተለየው አባቱ የሚያርግበት ጊዜ የደረሰ መስሏት በእግሩ ላይ ወድቃ ልትስመው ነበር አቀራረብዋ። ጌታ ግን የማርግበት ጊዜ ገና ነውና አትንኪኝ አላት ሦስተኛው ምክንያት ሴቶች ሥጋ ወደሙን መንካት (መፈተት) እንደማይችሉ ባጭሩ ካህን መሆን እንደማይችሉ ሥርዓት መመሥረቱ መሆኑን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያስረዳሉ። ለዚሁም ማረጋገጫ የሚያደርጉት ቶማስን ና ዳብሰኝ ብሎ መለኮት የተዋሐደ ሥጋውን እንዲዳስሰው ሲፈቅድለት ማርያም መግደላዊትን ግን እንዳትነካው ከልክሏታል። ዮሐ.20፥26–29።

«ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ» የሚለውን አባባል ዮሐንስ አፈወርቅ በሃይማኖተ አበው ላይ እንዲህ ሲል አብራርቶታል።» ነገር ግን እርሱ

## የክርስቶስ ተቃዋሚዎች የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

ካለፈው የቀጠለ

ከብርሃኑ ጎበና

በዚህ ክርስቶስ በእውነት ሰው እንደሆነ አስረዳ ዳግመኛም በተነሣ ጊዜ ከዚህ ከአዳም ባሕርይ ሰው መኾኑን አስረዳ ፈጽሞ ከእርሱ ወደ አልተለየው ወደ አብም ከማረጉ አስቀድሞ ለደቀ መዛሙርቱ አምላኬ አምላካችሁ አለ። ይህን በሰሙ ጊዜ ይህን የተናገረ ሥጋ ብቻ እንዳይመስላቸው ሰው የኾነ እርሱ እግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ አባቴ ብሎ ከዚህ በኋላ አምላኬ አለ እንጂ፤ እኔ ሰው የኾንኩ አምላክ ነኝና እኔም አንድ ነኝና ይህንንም ያንንም እኔ እላለሁ ይላል፤ የሰውን ባሕርይ ገንዘብ አድርጌአለሁና ኃጢአት የሌለበት እርሱ እኔ ነፍስና ሥጋን በእውነት ተዋሕጄ አለሁና ከእኔ ጋር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ላደረግሁት ለሥጋ ሥርዓት እንደሚገባ እንዲህ አባቴን አምላኬ ብዬ ጠራሁት ይላል» (ሃይ.አባ ገጽ 248)።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ ለመሆኑ በመዝ.2፥7። እንዲሁም በማቴ.3፥17። ላይ ተገልጿል። የአብ ልጅ ነው ሲባል ግን በሥነ ፍጥረት ሕግ ከልጅ አባት እንደሚቀድም ሁሉ አብም ከወልድ ቀድሞ ነበር ማለት አይደለም። አብ ከወልድ ቀድሞ የነበረበት ጊዜ የለም። ወልድም ከአብ የተለየበት ጊዜ የለም፤ በቅድምና አንድ ናቸው ወልድ ያልነበረበት ጊዜ የለም። «ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እርሱ ከአብ ጋር ነበረ» ኢሳ.48፥16።

አባታችሁ ሲል ግን ለእኛ የጸጋ አባታችን እንደሆነ ለማስረዳት ነው። 1 ዮሐ.3፥1። 1 ዮሐ.5፥1። ኢሳ.64፥8።

አምላኬ ሲል መለኮት የፈጠረውን ሥጋ መዋሐዱን ለማስገንዘብ የተዋሐደውንም ሥጋ በመቃብር ጥሎት እንዳልተነሣ መለኮትን የተዋሐደ ሥጋ ሞትን ድል አድርጐ እንደ ተነሣ ለማስረዳት ሲሆን ወደ እምላካችሁ ሲል ደግሞ በጥንተ ተፈጥሮ በሐዲስ ተፈጥሮ ይፈጥረናልና ነው። (እውነተኛ ፈጣሪያችን መሆኑን ሲገልጽ ነው።)

እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር ቢኖር ጌታ «አባታችንና አምላካችን» አለማለቱን ነው። በዚህ ፈንታ «አባቴና አባታችሁ አምላኬና አምላካችሁ» ነው ያለው። ስለዚህ እርሱ አምላኬ ሲል በትህትና ራሱን ዝቅ አድርጎ የሰው ልጆችን ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ ለማውጣት የፈጠረውን ሥጋ ተዋሕዶ የወደቀውን የአዳምን ባሕርይ ባሕርይው አድርጎ መምጣቱን ሊገልጽ መሆኑን በመገንዘብ ጌታን የአብ ፍጡር ከማለት ትልቅ ስህተት መጠበቅ ይገባል። ብርሃን ዓለም ቅ/ጳውሎስ የአካላዊ ቃልን (የኢየሱስ ክርስቶስን) በትህትና መገለጽ ሲገልጽ «ሁላችሁ ይህን አስቡ ለእኛም ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አደረገልን። ይኸውም የእግዚአብሔር መልኩ ነው ቀምቶ እግዚአብሔር የሆነ አይደለም ራሱን ዝቅ አድርጐ የአዳምን ባሕርይ ገንዘብ አደረገ እንጂ ሰውንም መሰለ» ፊል.2፥5–7።

### 1ቆሮ.15፥24–28

«እግዚአብሔር አብ መንግሥቱን እጅ ባደረገ ጊዜ ያን ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል ገዥም ሁሉ ንጉሥም ሁሉ ኃይልም ሁሉ በተሻረ ጊዜ ጠላቶቹ ከእግሩ በታች እስቲወድቁ ድረስ ይነግሥ ዘንድ አለውና ከዚህ በኋላ የመጨረሻው ጠላት ይሻራል። ይኸውም ሞት ነው ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቶለታልና። ሁሉ ይገዛለት ባለ ጊዜ ግን ሁሉን ከሚያስገዛላት በቀር እንደሆነ የታወቀ ነው። ሁሉም በተገዛለት ጊዜ ያን ዕለት ወልድም ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ በሁሉ ይሆን ዘንድ።»

«ወልድም ሁሉን ላስገዛላት ይገዛል» የሚለውን ነቅሰው በማውጣት ወልድ የአብ ተገዢ ይሆናል የሚሉ መናፍቃን አሉ። ዳሩ ግን አባባሉ እነርሱ እንደሚሉት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የአብ ተገዥ አድርጐ የሚያቀርብ ሳይሆን ከላይ ጀምሮ ጳውሎስ እየገለጸ የመጣው ሁሉ ስለማለፉ ሲሆን በተለይ በሰዎች ላይ ነግሦ የነበረው ሞት የመጨረሻው (የኋላ) ጠላት ተብሎ ተገልጾአል። ምክንያቱም ከአዳምና ሔዋን መሳሳት በኋላ የመጣ ነውና። እንዲሁም ከወደ ኋላ የመጣ ጠላት ጽኑዕ እንደኾነ ሁሉ ሞትንም ጽኑዕ ጠላት ሲል ነው። ይህ ሞት እንግዲህ በሰዎች ልጆች ላይ ሠልጥኖባቸው ሁሉም የእርሱ ተገዢ ሆነው ኖረዋል። እርሱም ሁሉንም ገዝቷልና። ነገር ግን ሁሉን ካስገዛለት (ሥልጣን ከሰጠው) ከወልድ ሞት እንዲያንስ ይታወቃል። ሞት በሁሉ ላይ እንዲሠለጥን ያደረገው ወልድ ነውና። ይህስ ቁም ነገር አይደለም ብሎ ካስገዛለት ከሰው ሁሉ ሞት እንዲያንስ ይታወቃል። እንዴት ቢባል በዕለተ ምፅአት የሞት ኃይል ይሻራልና ሁሉም ሞትን ድል አድርገው ይነሣሉ።

ሁሉ በተገዛለት ጊዜ ያን ጊዜ ወልድም ሁሉን እንዲገዛ ሥልጣን ሰጥቶት ለነበረው ለሞት ተገዝቷል። በዕለተ ዓርብ ጌታ ስለ ሰዎች ልጆች ብሎ እንደሞተ ሲገልጽ ነው። ነገር ግን ክርስቶስ በገዛ ፈቃዱ ሞተ እንጂ እንደሌሎች ሰዎች በግድ የሞተ አይደለም። ራሱ ወዶ ፈቅዶ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አደረ እንጂ። ይህም ወዶ ፈቅዶ ያደረገው መሆኑን ጳውሎስ ሲገልጽ «ሁሉን ላስገዛለት ተገዥ ይሆናል» አለ። ሁሉን እንዲገዛ ሥልጣን ለሰጠው ለሞት ወዶ ፈቅዶ ራሱን ሰጠ ማለት ነው።

### የሐዋ.2፥32።

«እርሱን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው» ይህን በመጥቀስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ኃይሉና ሥልጣኑ ሞቶ እንዳልተነሣ የሚናገሩና እርሱ የመነሣት ኃይል እንደ ሌለው ሌላ እንጂ ኃይል እንዳስነሣው አድርገው የሚናገሩ አሉ። ዳሩ ግን ቅዱስ ሉቃስም ሆነ ሌሎች ሐዋርያት ሲጽፉ ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው ብለው መናገራቸው መለኮት የተዋሐደውን ሥጋ ከሙታን ለይቶ እንዳስነሣው ለመግለጽ ነው። ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ መሆኑን እናምናለን። ስለሆነም እግዚአብሔር የሚለው ስም የአብ ብቻ መጠሪያ ሳይሆን የወልድም የመንፈስ ቅዱስም መጠሪያ ነው ዮሐ.1፥1። የሐዋ.20፥28። ሰው የሆነው እግዚአብሔር መሆኑንና ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የዋጀት እግዚአ ብሔር ራሱ እንደሆነ ይመሰክራሉ።

እንግዲህ እግዚአብሔር ብሎ መለኮትን ለመግለጽ ተጠቀመበት እንጂ አብ ብቻውን ያለ ወልድና ያለ መንፈስ ቅዱስ አስነሺ ወልድ በባሕርይ ሥልጣን ከአብ የተለየ ወይም አብ ብቻ ብርቱ ወልድ ግን ለመነሣት ሥልጣን የሌለው ደካማ ነው ለማለት አይደለም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ፈቃዱ ለመሞቱ በገዛ ሥልጣኑ ለመነሣቱ በዮሐ.10፥17–18 ላይ ተገልጾአል። «ስለዚህም አብ ይወደኛል እኔ ሰውነቴን ለበጎቼ ቤዛ አድርጌ አሳልፌ እሰጣለሁና እንደገና አስነሣት ዘንድ እኔ ራሴ በፈቃዴ አሳልፌ እሰጣታለሁ እንጂ ከእኔ የሚወስዳት የለም ነፍሴን ከሥጋዬ ልለያት አዋሕጄም ላስነሣት ሥልጣን አለኝና ይህን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልኩ»።

እንዲሁም ጌታ በሥልጣኑ ከሙታን ተለይቶ እንደሚነሣ ሲገልጽ «ጌታ ኢየሱስም ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስተኛውም ቀን አነሣዋለሁ ብሎ መለሰላቸው። አይሁድም ይህ ቤተ መቅደስ በአርባ ስድስት ዓመት ተሠራ አንተስ በሦስት ቀኖች ውስጥ ታነሣዋለህን? አሉት። እርሱ ግን ቤት ስለተባለ ስለ ሥጋው ነገራቸው ከሙታን በተነሣ ጊዜም ደቀ መዛሙርቱ ስለዚህ እንደነገራቸው አሰቡ» ዮሐ.2፥19–22።

እንግዲህ በሦስት ቀኖች ውስጥ የሚያስነሣኝ አለ ሳይሆን ያለው ራሱ በሥልጣኑ እንደሚነሣ መግለጹን አስተውሉ። ✣

ይቀጥላል


ለሥራ ፈላጊዎች በሙሉ

የሥራ ቦታ – መንግሥተ ሰማያት

የሥራ መደብ –ቅድስና

የሥራ ልምድ – ሕይወቱን ለአገልግሎት እግዚአብሔር የሰጠ፣ ንስሐ የገባ

ደመወዝ – የዘለዓለም ሕይወት

የትምህርት ችሎታ – በቅዱሳት መጻሕፍት የታነፀ

የመመዝገቢያ ቦታ–ቅድስት ቤተክርስቲያን

ቀን – ዛሬውኑ

ማሳሰቢያ አመልካቾች በንስሐ የታጠበ ሰውነት፥ በቅዱስ ቁርባን የተባረከ ሕይወት፥ እግዚአብሔርን ለማገልገል የተሰጠ ነፃ ፈቃድ በመያዝ መመዝገብና እስከ ዕለተ ሞት የሚሰጠውን ፈተና በማለፍ ሥራውን ማግኘት ይችላሉ።

የተዋሕዶ ድምፅ




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# መዝሙርና ምሥጢራዊ ሥርዓቱ

ዐቢይ ኃ/ጊዮርጊስ

ለማናቸውም ነገር መነሻና መግቢያ ሊኖረው ያስፈልጋል። ስለሆነም በርእሰ ነገራችን ባሕረ አድማስ ክልል የብዙ ቃላት መሣፈሪያ የሆነ መርከብ ዐነጋገር ከመመለሳችን አስቀድሞ ለዚህ ጥልቅና ስፉሕ ለሆነው ርእሳችን መርሕ (ትርጓሜ) ልንሰጠው የተገባ ነው።

እንዲህም ከሆነ መዝሙር ምንድን ነው? የሚለውን መጠይቅ ለርእሰ ነገራችን ሐተታዊ ፍሬ ነገር መነሻ በማድረግ መሠረታዊ ትምህርታችንን እንጀምራለን።

መዝሙር የባሕርይ አምላክ ልዑል እግዚአብሔር በሰማይና በምድር የሚመሰገንበት፥ የሚቀደስበት፥ የሚለመንበት፥ ዐቢይ የጸሎት ክፍል የሆነ ጣዕመ ዜማ ነው። «እግዚአብሔርን አመስገኑ መዝሙር መልካም ነውና ለአምላካችን መዝሙር ያማረ ነውና» መዝ.146፥1። ዘጸ.15፥1–22። ኢሳ.6፥1–5። ራእ.15፥1። ራእ.5፥6–14። መዝ.65፥1–5። መመልከት ስለ መዝሙር ያስረዳል።

ከዚህም ጋር መዝሙር ማለት ምን ማለት ነው? ያልን እንደሆን መዝሙር፥ ዘመረ፥ አመሰገነ ካለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙም ምስጋና፥ ልመና፥ ወይም መማጸን፥ ማራራት፥ ማስደሰት፥ መደሰት ማዜም፥ ማለት ነው። ከዚሁም ሌላ እግዚአብሔርን በእጽፍ ድርብ ማመስገን ማለት ነው፥ በመሆኑም «ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን ለአምላክ ለመድኃኒታችን እልል እንበል በምሥጋና ወደፊቱ እንድረስ በዝማሬም ለእርሱ እልል እንበል እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ነውና» የለናል። መዝ.32፥1–5። መዝ.149፥1። መዝ.150፥1–6። መዝ.80፥1–3። ማቴ.26፥30። ማር.14፥26። የሐዋ.16፥25። ቆላ.3፥16–25። ራእ.14፥1–3። ማቴ.21፥9። ማር.11፥9። ሉቃ.19፥36:38። በቅደም ተከተል መመልከት ይጠቅማል። ከላይ እንዳየነው መዝሙር ማዜም ማለት ነው ብንልም ዜማ ማለት ራሱ በቀጥታ ሲፈታ ስልት ያለው ጩኸት (ድምፅ ማሰማት) ማለት ነው።

ይሁን እንጂ ዜማ የምስጋና ብቻ ሳይሆን የሐዘን፥ የልቅሶ፥ የቀረርቶ፥ የሽለላ፥ የፉከራና የደስታ ሁሉ ስሜት መግለጫ ድምፅ ነው። ኢሳ.6፥1–5። ማቴ.26፥30። ከዚህ ላይ ግን ዜማ ባልን ጊዜ የቤተክርስቲያናችንን የምስጋና መዝሙር ድምፅ ማለታችን ነው። ለምን ቢሉ ዜማ እራሱን የቻለ ጥሬ ቃል (ነባር) ቢሆንም ዘመረ፥ አመሰገነ፥ አዜመ ካለው ቃል ጋር በጠባይና በግብር ይመሣሠላልና ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ የመዝሙር ወይም የዜማ ጥቅሙ ምንድነው?

ሀ. መዝሙር እግዚአብሔርን በተመስጦ ለማመስገን ለመቀደስ፥

ለ. ወደ እግዚአብሔር ልባዊ ጸሎት ወይም ልመናን በማራራት ለማቅረብ፥

ሐ. መዝሙር ለመማሪያና ለማስተማሪያ ወይም ልብን ለማነፅና ነፍስን ለማስደሰት ማለት መንፈስን ለማደስ ለምክር ለተግሣጽና ደግሞም ለመጽናትና ለማጽናናት እጅግ አድርጎ ይጠቅማል።

መዝሙር ወይም ዜማ:- የተጀመረው በአራቱ ሰማያት ማለት በሰማያዊት ኢየሩሳሌም፥ በኢዮር በራማና በኤረር ያሉ መላእክት እግዚአብሔር ፈጣሪያቸውን ያለ ዕረፍት ሲያመሰግኑት ነው። ይህንንም ሲያረጋግጥ ነቢዩ ኢሳይያስ «እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት። የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር። ሱራፌልም በእርሱ ዙሪያ ቆመው ነበር። እያንዳንዱም ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሰማይና ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልቷል እያሉ ይጮኹ፥ ይዘምሩ ነበር። የመድረኩም መሠረት ከጩኺው ድምፅ የተነሣ ተናወጠ ቤቱንም ጢስ ሞላው» ይላል። ኢሳ.6፥1–5። ራእ.4፥11። ይህም በኪሩቤልና በሱራፌል ማለት በመላእክት የተጀመረው ጣዕመ ዜማ (መዝሙር) በእነሱ አሰሚነት ለሰው ልጆችም ታድሏል። ይህም ይታወቅ ዘንድ ሊቀ ነቢያት ሙሴ በሥልጣነ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ የባርነት አገዛዝ ነፃ በወጣበት ጊዜ ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ በደረቅ ምድር ሲያሻግራቸው ሙሴና ተከታዮቹ በተለይም እኅቱ ማርያምና እርሱ እግዚአብሔርን በከበሮ ድምፅ እየታጀቡ በጣዕመ ዜማ አመስግነዋል። የመዝሙርም በይፋ መጀመር የታወቀው በዚሁ ጊዜ ነው። ዘጸ.15፥22።

ደግሞም ወንጌላዊው ቅ/ዮሐንስ ባየው ራእይ.14፥1–6። ከምድር የተዋጁት አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ ወገኖች ማንም ያልዘመረውንና ሊዘምረውም የማይችል ጣዕመ ዜማ ልዩ የሆነ አዲስ መዝሙርን በመድኃኒታችን ዙፋን ፊት በኪሩቤልና በሱራፌል መካከል እንደዘመሩ ይገልጻል።

የመላእክት ጣዕመ ዝማሬ ለሰው ልጆች የታደለ ስለሆነም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ዘወትር ፈጣሪዋን ታመሰግንበታለች። ለዚህም መዝሙራችን እስከ አሁን በዓለም ተወዳዳሪ አልተገኘለትም፥ የተገኘውም በኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ አማካይነት ነው።

እኛም አሁን የምንዘምረው መዝሙር የቅ/ያሬድ ዜማ ነው። የያሬድ የመጀመሪያ ዜማም «አርያም» ይባላል። አርያም ማለትም ልዑል ከፍተኛ ማለት ነው። ቅ/ያሬድ የዜማ መጀመሪያውን አርያም ብሎ የሰየመው በሰማይ ካሉ መላእክት ሰምቶ መዝሙር ስለጀመረ ነው። ይህም ሊታወቅ «ቀዳሚ ዜማ ተሰምዓ በሰማይ» እያለ ይሄድ እንደነበረ ሊቃውንት ይተርካሉ።

ይህ ታላቅ ሊቅ በመንፈሳዊ ተመስጦ ሰማየ ሰማያት ተነጥቆ ከመላእክት ያገኘው ዜማ ዓይነቱ ሦስት ነው። እነዚህም ሀ. ግእዝ ለ. ዕዝል ሐ. አራራይ ይባላሉ።

እነዚህ ሦስቱ የዜማ ስልቶችም ምሣሌና ትርጉም አላቸው። ይኸውም ግእዝ ማለት ርቱዕ ነው። አብ ርቱዕ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሎቱ ነአኩቶ ማለት ክብር ምሥጋና ለእርሱ ይሁን ለማለት፥ ዕዝል ጽኑዕ ማለት ነው። ወልድ ጽኑዕ መከራ ተቀብሎ አዳምን እንዳዳነው ለማመልከት፥ አራራይ ማለትም ጥዑም ማለት ነው። ጥዑም ሀብተመንፈስ ቅዱስን እንደተጐናጸፍን ለማስረዳት ነው። ይህም ቢሆን ታዲያ ተገንጣጥለው አይቀሩም። ግእዝ ከተሠኘው ዜማ ዕዝልና አራራይ ይወጣሉ። ይህም በአሐዱ አብ ዜማ ይታወቃል። ምሥጢሩ ከአብ እምቅድመ ዓለም ወልድ ለመወለዱ፥ መንፈስ ቅዱስ ለመሥረፁ ምሳሌ ነው። ከዚህም ጋር የንባቡና የድምፁ ቃና አንድ መሆን የሥላሴን አንድነት ሲያስረዳ የዜማው ሦስት ዓይነት መሆን ደግሞ የሦስትነታቸው ምሳሌ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የያሬድ ዜማ በቂና ጥሩ ጥሩ ምሳሌ ያላቸው ብዙ ምልክቶች ያሉት ቢሆንም ለአብነት ያህል ግን ስምንቱን ዐበይት ምልክቶች እናያለን። እነዚህም ዜማውን ለሚማር ደቀ መዝሙርና ለሚዘምረው ሁሉ በምልክትነት ሲያገለግሉ ምሳሌያቸውና ምሥጢራቸው ግን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ ስለኛ የተቀበለውን መከራ የሚያስታውሱ ናቸው። እነዚህም የኋላ ሊቃውንት ከጨመሯቸው ከድርስና ከአንብር በስተቀር ዋና ዋናዎቹ የቅ/ያሬድ ብቻ ሲዘረዘሩ

1. ይዘት – በአይሁድ ጭፍሮች ለመያዙ፥ ማቴ. 26፥50።
2. ሂደት – ታሥሮ ለመጐተቱ፥
3. ጭረት – ለግርፋቱ ሰንበር፥
4. ድፋት – አክሊለ ሶክ (የእሾክ አክሊል) ለመድፋቱ፥
5. ደረት – ሲሰቅሉት በመስቀሉ ላይ አንጋለው ከደረቱ ላይ ቆመው እየረገጡት ለመቸንከሩ፥
6. ርክርክ – ለደሙ ነጠብጣብና አወራረድ ለቸንካሩ ምልክት፥
7. ቁርጥ – በጦር ተወግቶ ፈጽሞ መሞቱ ለመታወቁ
8. ቅንዓት – በቅንዓተ አይሁድ ለመገደሉ ምልክትና ማስታወሻዎች ሲሆኑ ስምንት መሆናቸውም ስምንቱም ማኅበረ አይሁድ ተባብረው መክረው በብዙ ስቃይ ጌታን ለመግደላቸው ምሣሌ ነው። እነዚህስ ማንና ማናቸው ቢሉ

1. ጸሐፍት ፈሪሣውያን
2. ሰዱቃውያን
3. ረበናት (መምህራነ አይሁድ)
4. መገብተ ምኩራብ (የምኩራብ ሹማምንት)
5. መላሕቅተ ሕዝብ (የሕዝብ ሽማግሌዎች)
6. ሊቃነ ካሕናት
7. ኃጥአንና
8. መጸብሓን (ቀራጮች) ናቸው።

በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን የማኅበር ጸሎት ሲደርስ በጣዕመ ዜማ ወይም መዝሙር ማመስገንና መጸለይ የተለመደና የተወደደ ሥርዓት ነው። ይህ ሁሉ ሲከናወን ለምሥጋናው ለጸሎቱ ማጐልመሻ ሆነው የሚቀርቡትን ንዋየ ቅድሳትና የጸሎቱ ቅደም ተከተል ሁሉ በቂ ምክንያትና ምሳሌ ያለው ሆኖ መገኘቱ እኛን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች በጣም ያኮራናል። ይህንንም ለመረዳት በጸሎተ ማኅሌት ማለት የምስጋና መዝሙር በሚቆምበት ጊዜ የሚፈጸመውን ከልብ መመልከትና ማገናዘብ ይገባናል። ❖

ይቀጥላል

## እመአምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ

ከዲ.ተክለጻድቅ

ዘፍ.22፥9–13።

በዚህ የመጽሐፍ ክፍል የጻድቁን አባታችንን የአብርሃምን ልጅ የይስሐቅን የመሥዋዕትነት ፈተና እና በዚያም እግዚአብሔር የገለጠውን ድንቅ ምሥጢር እንመለከታለን። ይስሐቅ በአብርሃምና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው መልካም የእምነት ግንኙነትና የአምላካዊ ቸርነት ውጤት መሆኑን አበው ይተርኩልናል። ያስተምሩናልም። እርሱ እግዚአብሔር ለአብርሃም ቅድስና ምስክር ይሆን ዘንድ በእርጅና ዘመን የሰጠው ስጦታ ነው። ከዚህም የተነሣ በአባቱ ቤት እግዚአብሔርን በመፍራትና በታዛዥነት አደገ። በልጁ መልካም አስተዳደግ እየተደሰተ ፈጣሪውን በማመስገን የሚኖረው አብርሃም በስተመጨረሻ ያገኘውን ልጁን መሥዋዕት አድርጎ እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ ለመሥዋዕትነት የተፈለገው ይህ ወጣት ነበር።

ሃይማኖቱ በጊዜ ያልተለወጠው አብርሃም ከልጁ ይልቅ የእግዚአብሔርን ፍቅር በማሰብ የፈጣሪውን ፈቃድ ለመፈጸም ይስሐቅን ለመሠዋት ይዞት ወደተራራ ወጣ። መሠዊያውን አዘጋጅቶ የልጁን አንገት ለማረድ ካራውን አነሣ። ወጣቱ ይስሐቅም በፍጹም ታዛዥነት አንገቱን ወደአባቱ አዘነበለ የአባቱን ትእዛዝ ይፈጽም ዘንድ ሙሉ ፈቃደኛ ሆነ። እግዚአብሔርም የአባቱን እምነትና የልጁን ፈቃደኛነት በተመለከተ ጊዜ ድምፁን አሰማ ለአብርሃምም በዕፀ ሳቤቅ የታሠረ ነጭ በግ አቀረበለት ካራውንም በልጁ ላይ እንዳይሰነዝር ከለከለው። ያ ነጭ በግ ስለይስሐቅ ፈንታ ተሰዋ። እግዚአብሔር በክፉ የማይፈትን አምላክ በመሆኑ በታመነውና ራሱን ለመሥዋዕትነት አሳልፎ በሰጠው በይስሐቅ ፈንታ ነጩን በዕፀ ሳቤቅ የታሠረ በግ ቤዛ አድርጎ ሰጠ። በዚህ በግ ቤዛነትም ይስሐቅ ከመሞት ዳነ–ሕያውም ሆኖ መኖር ቻለ። ንጹሕ ሃይማኖቱን ለመሥዋዕት ማቅረቢያ በተረበረበው እንጨት ላይ የገለጠው ይስሐቅ «ዘርህን እንደምድር አሸዋ አበዛዋለሁ» ከመባሉም ሌላ የእሥራኤል አባት የሆነው ልጁን ያዕቆብን ለማግኘት እስኪበቃ ድረስ በረከትን አግኝቷል።

ያ በጊዜው በይስሐቅ ፈንታ የተሠዋው በግ በኋለኛው ዘመን ለዓለም ሁሉ ቤዛ ሊሆን በቀራንዮ በዕፀ መስቀል ተሰቅሎ የሚሠዋው የመድኃኒታችንና አምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነበር። ዮሐ.1፥29። በጉ የታሠረባት ዕፀሳቤቅ ደግሞ በኀቱም ድንግልና አምላክን በማኅፀኗ የወሰነችው የወላዲተ አምላክ ምሳሌ ነበር። በዚያ በግ መሥዋዕትነት ይስሐቅ ከሞት ዳነ። በኋለኛው በግ በኢየሱስ ክርስቶስ አማናዊ መሥዋዕትነት ደግሞ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ ሁሉ ከተፈረደበት ዘለዓለማዊ ሞትና ከሲኦል ቁራኛነት ዳነ። እንግዲህ ለዚህ ለዓለም ሁሉ መዳን ምክንያት የሆነችው አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን በማኅፀኗ ለመሸከም የተመረጠችው መለኮት ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በተዋሕዶ ዓለምን ለማዳን ማደሪያው ያደረጋት እመቤታችን ድንግል ማርያም መሆኗን የምናውቅና የተፈጸመልንን ታላቅ የማዳን ሥራ የምናስተውል ሁሉ ለእርሷ ሊኖረን የሚገባው ፍቅር የቱን ያህል መሆን እንዳለበት መዘርዘር አያስፈልግም።

በእኛና በፈጣሪአችን መካከል እርሷ በንጽሕናና በቅድስና ተገኝታ ለእርቃችን ምክንያት ለሰላማችን መሠረት ሆና ተገኝታለችና ለእኛ መዳን ቤዛ ሆኖ ራሱን በፈቃዱ በመስቀል ላይ መሥዋዕት አድርጎ የሰጠውን አምላካችንን ተፈትሖ በሌለበት ኅቱም ማኅፀኗ ተሸክማ በሞት ጣር ተጠርቀን በነበርንበት ጊዜ በተወሰነው ሰዓት አማኑኤልን የወለደችልን አማናዊቱ ዕፀ ሳቤቅ እርሷ መሆኗን በጽኑ ፍቅር ልናስበው ያስፈልጋል።

የጀመርነውን ይህን የአበው ትምህርት በመቀጠል ለሚከተለው እትም ደግሞ ሌላውን ይዘን እንቀርባለን። ❖

ይቀጥላል



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# የጥያቄዎቻችሁ መልስ

በዚህ ዓምድ ከአንባብያን ለቀረቡ መንፈሳውያን ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን።

ባለፈው እትማችን ከሀ–በ «ስለ ንስሐ ከተዘረዘሩት ጥያቄዎች መካከል በፊደል ተራ «ሀ» የተጠቀሰውን ንስሐ ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን ጥያቄ በሰፊው አብራርተን መመለሳችን የሚታወስ ነው። በዛሬው እትም ደግሞ የተቀሩትን ጥያቄዎች እግዚአብሔር እንደፈቀደ መጠን እንመልሳለን።

ለ. ንስሐ የሚያስፈልገው ለማን ነው? ንስሐ የሚያስፈልገው ኃጢአትን ለሠራ ሁሉ ነው። ኃጢአት ሰውነትን ስለሚያቆሽሽ ኃጢአታችንን አምነን ወደ ኃጢአት ላለመመለስ ወስነን በንስሐ ውኃ መታጠብ አለብን። ኃጢአተኞች ሁሉ ለንስሐ ተጠርተናልና «ንስሐ ግቡ ኃጢአትም እንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ።» ሕዝ.18፥30። ይላል። ይህ ቃል የሚያስተምረን ኃጢአተኞች ሁሉ ንስሐ መግባት እንደሚያስፈልገን ነው። «ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ...» የሐዋ.2፥38። ሲል ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም የተናገረው እኛን ለመሰሉ ኃጢአተኞች በመሆኑ ልጅ ከዐዋቂ ሳንል ከሊቅ እስከ ደቂቅ ዛሬውኑ ንስሐ እንግባ ነገ የእኛ አይደለምና፥ ለነገ ክፉቱ ይበቃዋልና ማቴ.6፥34።

ሐ. ንስሐ የሚገባው ሰው ለግሉ ማድረግ ይችላልን? በዘመናችን አንዳንዶች ኃጢአቴን በግል ለጌታ ብነግረውስ? ለካህን ባልናገርስ? የሚሉ አሉ። ይሁን እንጂ ይህ አመለካከት ባለማስተዋልና ምሥጢርን ካለመረዳት ወይም ሆነ ተብሎ ምእመናንን ለማሳሳት መሆኑ ግልጥ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ንስሐ መግባት ያለበት የግድ ለካህን ነግሮ መሆን እንዳለበት ሁላችንም በእምነት ልንቀበለው የሚገባን ጉዳይ ነው። ለምን? ለሚለው ጥያቄ የሚቀጥለው ጥያቄ መልስ አጠቃልሎ ይመልስልናል። በደል ከእግዚአብሔር የሚለይ ግድግዳ ነው ኃጢአትም መጋረጃ ነው። ኢሳ.59፥2።

መ. ንስሐ የሚገባው የግድ ለንስሐ አባት ተነግሮ ብቻ ነው? አዎ ምክንያቱም ምዕመናንን እንዲጠብቁ ሥልጣነ ክህነት ተሰጥቶአቸዋልና ነው። በብሉይ ኪዳን የነበሩ የምእመናን እረኞች ሓላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው እግዚአብሔር ወቅሷቸዋል። ሕዝ.34፥2–26። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመዝ.22፥1 እና በመዝሙር 79፥1። ላይ «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው።» የእሥራኤል ጠባቂ ሆይ አድምጥ» እያለ የምእመናን የነፍሳቸው እረኛ (ጠባቂ) እግዚአብሔር መሆኑን ገልጧል። ቸር ጠባቂ እግዚአብሔር የእረኞች ራስ የሆነ ሌዋውያን ካህናት እሥራኤልን እንዲጠብቁ ፈቅዶ ነበር።

**ንስሐ ለመግባት ኃጢአቴን ለካህን ባልናገርስ?**

በሐዲስ ኪዳንም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ በጎቹ (ስለ ምእመናን) ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ቸር እረኛ መሆኑን ስለ ራሱ ተናግሯል። የቀድሞ ሠዓሊዎችና አናፂዎች ክርስቶስን እንደበግ ጠባቂ እያደረጉ በግ አሸክመው ይሥሉና ይቀርፁ ነበር። ይህም ማለት እውነተኛ ጠባቂ መንጋዎቹን እንደሚወድና እንደሚንከባከብ የጠፋችውንም ፈልጎ እንደሚያመጣ ክርስቶስም መልካም እረኛ በመሆኑ ምእመናንን እንዴት እንደሚወድና እንደሚንከባከብ የሚያስረዳ ነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ምእመናንን እንዲጠብቁ ሥልጣን ሰጥቶ ሹሟቸዋል የሐዋርያት አለቃ ቅ/ጴጥሮስ «ግልገሎቼን አሰማራ። ጠቦቶቼን ጠብቅ በጎቼን አሰማራ» ተብሏል። ዮሐ.21፥15–17። እንግዲህ ግልገሎች የተባሉ ሕፃናት ጠቦቶች ወጣቶች በጎች ደግሞ አረጋውያን መሆናቸው ነው። ይህም የምእመናን እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ የእረኝነትን ሥልጣን ለሐዋርያት እንደሰጣቸው የሚያረጋግጥ ነው። ጌታ ከትንሣኤውም በኋላ «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል። የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል። ዮሐ.20፥22–23። በማለት። ነፍስን የሚያጎድፈውን ኃጢአት እንዲያስተሰርዩ ሥልጣንን ሰጥቷቸዋል። በመሆኑም በምድር የሚያሥሩት ሁሉ በሰማይ የታሠረ በምድር የሚፈቱት ደግሞ በሰማይ የተፈታ ነው። ማቴ.16፥19፤ 19፥18። ምክንያቱም ሥልጣኑን የሰጣቸው የሰማይና የምድር ጌታ ነው ማቴ.28፥18። ስለዚህ በኃጢአት ሰንሰለት ታሥሮ ኃጢአቱን ለሚናዘዝ ሁሉ «እግዚአብሔር ይፍታህ» የሚል ድምፅ ያሰሙታል።

አንዳንዶች እኛ ሁላችንም ካህናት ነን ይላሉ። ይሁን እንጂ ከመንጋው መካከል ተለይተው መንጋውን እንዲጠብቁ ሥልጣን የሚሰጣቸው ካህናት እንዳሉ ወደ ማመን መመለስ አለባቸው። ቅንነቱ ካለ ቀላል ነው። ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ በሐዋ. ሥራ 20፥28 ላይ «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» ማለቱ ለዚህ ነው። በደሙ የዋጀንን ኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔር አለው የምእመናንን አንድነት ደግሞ ቤተክርስቲያን ብሎ ጠራ የጠባቂነት (የንስሐ አባትነት) ሥልጣንም



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ተናገረ። እንግዲህ ሥልጣነ ክህነትን መቃወም መንፈስ ቅዱስን መቃወም ነው። መንፈስ ቅዱስን መቃወም ደግሞ ሥርየት የሌለው ኃጢአት ነው። ማቴ.12፥32። እንደ ተቃዋሚዎቹ አሳብ ምእመናን ሁሉ ካህናት ከሆኑ መንፈስ ቅዱስ በምእመናን ላይ ለምን ጳጳሳትን ሾመ? ተሳስቶ ይሆን? እኛስ አንልም የሚል ይበል እንጂ።

በአንጾኪያ ክርስቲያኖች ነቢያትና መምህራን በአንድነት ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ፤ ብሎ ስላዘዛቸው ከጦሙና ከጸለዩ በኋላ ከተሰበሰቡት ምእመናን ሁለቱን ብቻ በመለየት በአንብሮተ ዕድ (እጅን በመጫን) ሾመዋቸዋል። የሐዋ.13፥1። ከዚህም ሥልጣነ ክህነት ልዩ አገልግሎት መሆኑን እንማራለን። ይህም መንፈሳዊ ሥልጣን ከጌታ ለሐዋርያት፥ ከሐዋርያት ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ለዚህ አገልግሎት ለመረጣቸው ተከታዮቻቸው፥ እንዲህ እያለ ከእኛ ዘመን ደርሷል። ከእንግዲህም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ይኖራል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ «በማቴ.28፥20። ላይ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ማለቱ ለእነርሱ የተሰጣቸው ሥልጣን ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እንደሚሠራ የሚያጠይቅ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ቀሳውስትና ስለ ዲያቆናት የሹመት መመዘኛ በዝርዝር ተናግሯል። ቀዳ.ጢሞ.3፥1–13። ሁሉ ካህናት ቢሆኑ ኖሮ ይህ መመዘኛ ባላስፈለገንም ነበር። ጢሞቴዎስ በአንብሮተ ዕድ (እጅን በመጫን) የተላለፈለትን ሥልጣነ ክህነት ቸል እንዳይል ተመክሯል። ቀዳ.ጢሞ.4፥14። 2ጢሞ.1፥6።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንዳንዶቹ ሐዋርያት ሌሎችም ነቢያት ሌሎችም ወንጌልን ሰባኪዎች ሌሎችም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ። በማለት ስለ አገልግሎቱ ስፋትና ጥልቀት ሐዋር ያው በሚገባ ተናግሮታል። ኤፌ.4፥11፤ 1ኛቆሮ.12፥28። ይህ ሁሉ የሚያስተምረን ካህናት ከምእመናን አገልግሎት የተለዩ መሆናቸውን ነው።

ካህናት (ሽማግሌዎች) የእግዚአብሔርን መንጋ (ምእመናንን) በውድ ቢጠብቁ ለመንጋው በጎ ምሳሌ ቢሆኑ ማኅበረ ክርስቲያኖችን በፍቅር ቢያስተዳድሩ የእረኞች አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ የክብርን አክሊል እንደሚቀበሉ ተነግሮላቸዋል። ለካህናት (ለሽማግሌዎች) አንታዘዝም እነርሱ ከእኛ የተለየ ምን ሥልጣን አላቸው? ኃጢአቴን ለእነርሱ ለምን እናዘዛለሁ? ማለት ከመንጋው (ከምእመናን አንድነት) መለየት ቃለ እግዚአብሔርን መተላለፍ ነው። እንዲያውም ቅዱስ ጴጥሮስ «እንዲሁም ጎበዞች ሆይ ለካህናት (ለሽማግሌዎች) ተገዙ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና። ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ሲል አስተምሮናል። 1ጴጥ.5፥1–5። አባቶች ካህናት በመንፈስ ቅዱስ የተሾሙ እረኞች ባይሆኑ ኖሮ ኢየሱስ ክርስቶስ የእረኞች አለቃ ባልተባለም ነበር። ቅዱስ ጳውሎስም እረኞችን ሾመ ብሎ ባልሰበከም ነበር።

እንግዲህ የምእመናንን አንድነት እንድንጠብቅ የተሾምን ካህናት መንጋውን በፍቅር እንጠብቅ። በእምነታችን ጽናት በምግባራችን መልካምነት በፍቅር በትህትና በትዕግሥት በየዋህነት በቅንነት ራስን በመግዛት ለምእመናን መልካም ምሳሌ እንሁን። ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ እንመላለስ። የክብር አክሊል ባለቤቶች እንድንሆን በመልካም ብናስተዳድር ይልቁንም በመስበክና በማስተማር ብንደክም እጥፍ ድርብ ክብር ይጠብቀናል። 1ጢሞ.5፥17። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ በጎ ታማኝም አገልጋይ (ካህን) በጥቂቱ ታምነሃል። በብዙ እሾምሃለሁ። ወደ ጌታህ ደስታ ግባ ይለናል። ማቴ.25፥21።

ምእመናንም ከሥጋ ድካም የተነሣ በኃጢአት የቆሸሸንና በበደል የረከሰን ሁሉ ንስሐ ላለመግባት ምክንያት ከምናበዛ ቀረብ ብለን ኃጢአታችንን ለካህናት እንናዘዝና ቀኖናን እንቀበል። ቀኖናችንንም ጨረስን ሥጋውን ደሙን በመቀበል እንቀደስ፥ የሕይወት ባለቤቶችም እንሁን። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምጻሙን ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ ራስህን ለካህን አሳይ ብሎታል። ማቴ.8፥4። ኃጢአትህን ለማንም አትናገር ለካህን እንጂ ሲለው ነው። እኛ ደግሞ ከለምጸ ኃጢአት እንድንነፃ ኃጢአታችንን ለካህናት እንናዘዝ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች (ካህናት) ጸሎት ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ ያድናል ኃጢአትን ያስተሰርያል። ያዕ.5፥14።

ያልተሰጠንን ተሰጥቶናል ብለን አንታበይ። ያልተሰጣቸውን ሽተው የካህናትን ሥልጣን የተጋፉ ዳታን ቆሬንና አቤሮን ከሰማይ በወረደ እሳት ተቀጥተዋል። ዘኍ.17፥35። በሥልጣኑ ተመክቶ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ እንደ ካህናት ለማጠን የሞከረ ንጉሥ ዖዝያን በለምጽ ተመትቷል። 2ዜና.26፥17። እኛም ሳናውቀው የእግዚአብሔርን ቁጣ እንዳናነሣሣ እንጠንቀቅ።

ሠ. ንስሐ የሚገባው ለምን ዓይነት ኃጢአት ነው? ንስሐ የሚገባው በቃል ለተነገረ፥ በግብር ለተገለጠ፥ ኃጢአት ብቻ ሳይሆን በልብ ለታቀደ ኃጢአትም ነው። ምክንያቱም ከልብ የተረፈውን አንደበት ይናገራልና። ልብ ያሰበውን አንደበት የተናገረውን ሰውነት ይፈጽመዋልና ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል።» ሲል ነግሮናል። ማቴ.5፥18። ከሁሉ የልብ አመንዝራነት የከፋ ነው።

ረ. ንስሐ የተገባበት ኃጢአት እንደገና ቢሠራ ምን መደረግ አለበት?



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በድጋሚ ለተሠራ ኃጢአት ንስሐ ቢገባ እግዚአብሔር ይቅር ይላል? ከንስሐ በኋላ ኃጢአት ቢሠራ ወዲያው ንስሐ መግባት ነው። እግዚአብሔርም ይቅርታው ብዙ ስለሆነ ይቅር ይላል። ነገር ግን ከንስሐ በኋላ ኃጢአት ብንሠራ ቀድሞውኑ ኃጢአትን ፈጽመን ለመተው ሙሉ በሙሉ አለመወሰናችንን ነው። የሚያመለክተው ንስሐ መግባታችንም የአፍ እንጂ የልብ ያልሆነ መመለስ ነው። ጭቃና ትፋት የተባለው ኃጢአት ነው። እንግዲህ የንስሐ ጸጋ አለንና ኃጢአት እንሥራ ብለን አንቀልድ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጸጋ እንዲበዛልን በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? ጸጋው ስለተሰጠን ኃጢአት እንሥራን? አይደለም። አይገባም ሲል ተናግሯል። ሮሜ.6፥1–15። ማወቅ የሚገባን ንስሐ ስንገባ «ሰይጣን ክጄሃለሁ» ብለን ሰይጣንን ማሰናበታችን ነው። ሰይጣን ከተሰናበተ ኃጢአት የለም። እንግዲህ ንስሐ ወደ ተገባበት ኃጢአት መመለስ ሰይጣንን « ና አምኜሃለሁ» ብሎ መጥራት ነው። እሱ ደግሞ ምኑ ሞኝ ነው? ብቻውን አይመለስም ከእርሱ የከፉትን ሰባት አጋንንት ይዞ በመመለስ ያድርብናል። እነርሱም ከቀድሞው የከፋ ኃጢአትን ያሠሩናል ሉቃ.11፥24። እንዲህ ማድረግ ደግሞ በራስ ላይ መፍረድ ስለሆነ ንስሐ ስንገባ ወደ ኃጢአት ላለመመለስ ወስነን ከልባችን ይሁን እግዚአብሔርም ይረዳናል።

ሰ. ኃጢአትን በዝርዝር ሳይናገሩ ካህን እግዚአብሔር ይፍታህ ስላለ ብቻ ኃጢአት ይደመሰሳል ወይ? በመሠረቱ በሽታን ሳይናገሩ መድኃኒት፥ ኃጢአትን ሳይናዘዙ ሥርየት የለም። ነገር ግን በጋራ አንድ ዓይነት ኃጢአት ሠርተው ኃጢአታቸውን ቢናዘዙ ካህኑ እግዚአብሔር ይፍታህ ባለ ጊዜ ኃጢአት ይደመሰሳል። በቅዳሴ ላይ ወይም በማኅበር ጸሎት ላይ ካህኑ በማወቅ ባለማወቅ ከልጅነት እስከ ዕውቀት የተሠራውን ኃጢአት እግዚአብሔር ይፍታ። የሚለው ኃጢአታቸውን ተናዝዘው ቀኖናቸውን ጨርሰው ለጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ለሚቆሙ ምእመናን ሁሉ ነው። ኃጢአታቸውን ያልተናዘዙ (ያላመኑ) ሰዎች ከዚህ ጸጋ ውጪ ናቸው። እንግዲህ የዚህ ጸጋ ተሳታፊዎች እንድንሆን» ቂም (ኃጢአት) ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት «አይሆንምና ኃጢአታችንን ተናዝዘን ንስሐ ገብተን በእግዚአብሔር ፊት እንቁም።

ሸ. ኃጢአትን ሠርተናል ለሚሉ ሰዎች በጋራ ቀኖናው ቢሰጥ በጋራ እግዚአብሔር ይፍታችሁ ቢባሉ ትክክል ነው ወይ? ከላይ እንደተገለጠው አንድ ዓይነት ኃጢአት ሠርተው ለምሳሌ ሁሉም ዝሙት ፈጽመው ወይም ጣዖትን አምልከው ወይም ጾምን ገድፈው በጋራ ቀኖና ቢሰጣቸውና በጋራ እግዚአብሔር ይፍታህ ቢባሉ ትክክል ነው። ነገር ግን እያንዳንዱ በግሉ የተለያየ ኃጢአት ቢሠራ ቀኖናው መሰጠት ያለበት በግል ነው። እያንዳንዱ በዚህ ዓይነት በግሉ የተሰጠውን ቀኖና ከጨረሰ በኋላ ቀኖናው ይለያይ እንጂ በጋራ እግዚአብሔር ይፍታ ቢባሉ ቃሉ አንድ ነው።

ቀ. የንስሐ ጊዜ የተወሰነ ነውን? መቼ? ለንስሐ የሚሰጠው ቀኖና በምን ልክና እንዴት ነው? የንስሐ ጊዜ የተወሰነ አይደለም ማንም ሰው ኃጢአትን ለመተው በወሰነ ጊዜ ንስሐ መግባትይገባዋል። ቀኖና የሚሰጠው በቤተ ክርስቲያን የሕግና የሥርዓት መጻሕፍት መሠረት ነው። ዕድሜ ያበድረን እንጂ ዝርዝር ጉዳዩን ወደፊት በሰፊው እንነጋገራለን። እንደ ኃጢአቱ ክብደትና ቅለት ጾም ወይም ስግደት ወይም ምፅዋት እንዲሰጥ የሚታዘዝ አለ። አብዛኛውን ጊዜ ግን ካህኑ ራሱ እያመዛዘነ ቀኖና ይሰጣል።

በ. አንድ ሰው ኃጢአት እንድሠራ የሚገፋፉኝ ነገሮች እስካልተቃለሉልኝ ድረስ ንስሐ አልገባም ቢል ትክክል ነው ወይ? ትክክል አይደለም። ለኃጢአት የሚገፋፋ ሰይጣን ነው። ኃጢአትም ክፉ ነገር ነው። ንስሐ መግባትም ከዚህ መለየት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ። ከእናንተም ይሸሻል። ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል።» ብሏል ያዕ.4፥7። ንስሐ ስለመግባት ምክንያት ማለት ነው። እንዲህ ዓይነት ሕይወት ሰማያዊ ግብርን ትቶ በምድራዊ ግብር ጸንቶ መኖር ነው። ቅዱስ ጳውሎስም በበኩሉ። «መጨረሻው ጥፋት ነው ሆዳቸው አምላካቸው ነው። ክብራቸው በነውራቸው ነው አሳባቸው ምድራዊ ነው እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነውና። » ፊልጵ.3፥18። በማለት ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ያልወሰኑ ሰዎችን ባሕርይ ከዘረዘረ በኋላ እንደ እርሱ ወደ እግዚአብሔር የተመለሱ ሰዎች ግን አገራቸው በሰማይ መሆኑን በሰማያዊ ግብር በእምነት በምግባር ጸንተው እንደሚኖሩ ተናግሯል።

ተ. የንስሐ ጊዜ መፈጸሚያ ቦታ የት ነው? ሱባዔ የሚያስገባ ከሆነ በቤተ ክርስቲያን ወይም ዘወር ተብሎ በገዳም ይፈጸማል። ቀለል ያለ ከሆነ ግን በቤት ተቀምጦ መጨረስ ይቻላል።

እንግዲህ ምድራዊ ክብርን ስንሻ በአሳረ ነፍስ እንዳንያዝ ቶሎ ንስሐ እንግባ ሆዳችንን ሳይሆን እግዚአብሔርን እናምልክ ሕጉን ስንፈጽም ትእዛዙን ስንጠብቅ እንገኝ። መጨረሻችን ጥፋት ሳይሆን ሕይወት ይሁን ለዚህም በንስሐ ውኃ ታጥበን ሥጋ ወደሙን መቀበል አለብን። እሱ ፈጣሪያችን እንደ ኃጢአታችን ብዛት እንደ ሰውነታችን ክፋት ሳይሆን እንደ ቸርነቱ ብዛት ይምረናል። ባነበብነው እንድንጠቀም የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን።

### ጥያቄ

መጻሕፍትን በማሳተም በኩል ቤተክርስቲያን ደካማ ነች በእጃችን የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ሌሎች ለራሳቸው እንዲያመች አድርገው የተረጐሙት ነው ስለዚህ ሰማንያ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አሐዱን የምናገኝበትን ዘዴ ብትፈልጉልን።

ዋበ – ከአ.አ

ቤተክርስቲያን በተቻላት መጠን ታትሞ የነበረውን የሰማንያ አሐዱን መጻሕፍት ለምእመናኖቿ ለማዳረስ ሞክራለች። በወጣቶች ማደራጃ መምሪያው በኩልም በየአጥቢያው ለሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ተዳርሷል። አሁንም ቢሆን በአጥቢያ ሰንበት ትምህርት ቤታችሁ ተመዝግባችሁ ብትጠባበቁ የማግኘት እድል ይኖራችኋል በርቱ።

### ጥያቄ

የቅዳሜ ስዑር ዕለት የሚታደለው ቀጤማና ሥርዓቱ ምን ትርጉም አለው።

ጥላዬ ሽታሁን – ከልደታ ማርያም
አ.አ.

በኖኅ ዘመን በጥፋት ውሃ ጊዜ ርግብ የለመለመ የወይራ ቅጠል ይዛ የውሃውን መድረቅ እንዳበሰረችው ሁሉ የሰው ልጅ በማየ ኃጢአት ጠፍቶ ቆይቶ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት የኃጢአት ውኃ መድረቁን በመስቀሉ የጥልን ግድግዳ አፍርሶ ሰላምን መመሥረቱን የምሥራቹን መናገር የሰላም መልእክተኛዋን ርግቢቱን መምሰል ነው።

### ጥያቄ

የቅዳሴ መግቢያ ሰዓት ሁሉም ቦታ ተመሳሳይ መሆን አይችልም ወይ ምእመናንስ ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጡ ምን አሟልተው ከምን ተቆጥበው መሆን አለበት።

ኃ/ኢየሱስ ዳመን

የቅዳሴ መግቢያ ሰዓት ከልደት፥ ከጥምቀትና፥ ከትንሣኤ በስተቀር ጾም ካልሆነና ቅዳሜና እሑድ ከማለዳው 12 ሰዓት ነው። ጾም ከሆነ ደግሞ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ነው። አብዛኛውን ጊዜ በከተማው እንዲህ ሲሆን በገጠር ግን ምእመናን ተበታትነው ስለሚኖሩ ለመጠበቅ ሲባል ትንሽ ረፈድ አድርገው ይገባሉ። ከአቅም በላይ የሆነ ችግር እስካልገጠመ ድረስ ሰዓቱን ጠብቆ መግባት መልካም ነው። በአንድነትም የሁሉም ጸሎት ያርጋል።

ምእመናን ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት ያለባቸው በነፍስም በሥጋም ንጹሕ ሆነው ነው። ቅ/ጳውሎስ «በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ» ብሏል። 1ቆሮ6፥20። ስለዚህ ባልና ሚስት ምንጣፍ ለይተው አድረው ለጊዜው ሥጋዊ ፍላጐታቸውን ትተው ለመንፈሳዊው ነገር ራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው ሴቶችም ከወር አበባቸው ነጽተው መቅረብ አለባቸው። እግዚአብሔር ንጽሕናን ይወዳልና!

### ጥያቄ

በቤተ ክርስቲያናችን ተክሊል የሚባለው ሥርዓቱ በሥጋውና በደሙ ሲፈጸም እንደሆነ ትምህርት ይሰጣል። ነገር ግን ሥርዓቱን ብቻ ማየት ከጀመርን ሰንብተናል። ለመሆኑ ያለ ቁርባን ተክሊል ይቻላል ወይ?

ከተክለ ሥላሴ– አ.አ

«የሺ ፍልጥ ማሠሪያው ልጥ» እንዲሉ የምሥጢራት ሁሉ ማሠሪያው ቅዱስ ቁርባን ነው፡፡ስለዚህ ተክሊል ያለ ቁርባን አይቻልም፤ በመሆኑም መስተካከል አለበት እንላለን። ይህ ነገር ዛሬ የመጣ እንጂ ጥንት አባቶቻችን የሠሩልን አይደለም «ምን አለበት» እያልን ከምንሠራው ሥራ ሁሉ መታቀብ አለብን።

### ጥያቄ

በቤተሰብ ውስጥ ያለ ጨሌና አመቺሳ የተሰኘ አምልኮ እኔ የማላምንበት ከሆነ የሚያመጣብኝ ጉዳት አለ ወይ?

ፍቅርተ ፈይሣ
ከንፋስ ስልክ

እስካላመንሽበት ድረስ ምንም ጉዳት አያመጣብሽም። ነገር ግን የሰይጣን ዙፋን በቤትሽ ተቀምጦ ዕለት ዕለት ከምትፈተኚ በተቻለሽ መጠን በጾምና በጸሎት ጭምር ቤተሰቦችሽን ከአምልኮ ጣኦት ማላቀቅ መንፈሳዊ ግዴታሽ ነው።

### ጥያቄ

ዶግማ እና ቀኖና ምን ማለት ነው?

ዲ/ሰሎሞን ፋንቱ
ሞጆ

ዶግማ መሠረተ እምነት ሲሆን ቀኖና ደግሞ ሥርዓተ እምነት ነው። በቤተክርስቲያናችን አምስቱ አዕማደ ምሥጢር፥ ምሥጢረ ሥላሴ፥ ምሥጢረ ሥጋዌ፥ ምሥጢረ ጥምቀት፥ ምሥጢረ ቁርባን፥ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን የተባሉት ዶግማ ናቸው። ማናቸውም የቤተክርስቲያን ሥርዓት ደግሞ ቀኖና ይባላሉ። ✣

## አደገኛው በሽታ

የበሽታው ስም – ክህደት

መነሻው – ያልተስተካከለ ሕይወት የተበረዘ የወንጌል ምግብ

የበሽታው ምልክቶች – በሽተኛው ሲጀምረው ‹ምናለበት› ማለት የሚያበዛ ሲሆን፥ ራሱን ከሌሎች አብልጦ የመመልከት፥ ያለመጾም፥ ያለመጸለይ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንደሚመቸው የመተርጐም፥ ንስሐ ያለመግባት፥ ያለመቁረብ፥ ያለመዘመር ስሜቶች ይሰሙታል። በሽታው እየባሰ ሲሄድም የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የቅዱሳንን አማላጅነት የሥርዓተ ቤተክርስቲያንን አስፈላጊነት መጠራጠር ይጀምርና በሽታው የመጨረሻ ደረጃ ላይ ሲደርስ ከስሙነቱ ተሠራጭቶ በክህደት ይገለፃል።

መከላከያው

የጾምና ጸሎትን ከትባት ዘወትር ሳይሰለቹ መከተብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ላቦራቶሪ እየሄዱ ከትዕቢት ነፃ መሆንን ማረጋገጥ፥ እንዲሁም በንስሐ ሳሙና እየታጠቡ ቅዱስ ቁርባንን መውሰድ በመጨረሻም ወደ ወንጌል ዶክተሮች እየሄዱ ምክር መቀበል።

አደራችሁ ንቁ! «ምናለበት» በሚባለው ቁስል በኩል በሚገባው የክህደት ጀርም ተበርዛችሁ እንዳታልቁ!

ተዋሕዶ ሆስፒታል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ኬኒንግበበ

በኢያሪኮ ግንብ ፍርስራሽ ሥር ቁፋሮዬን ተያይዤዋለሁ ላቦቴ እየተንቆረቆረ ዓይኔን ከማየት እየጋረደው ነው። እጅግ ብዙ የሆኑ ጥንታውያን የኢያሪኮ ሰዎችን ቅርሶች አግኝቻለሁ። ግን አሁንም እቆፍራለሁ። በመጨረሻ ታዲያ በድንጋይ ላይ የተጻፈ ረዥም ጽሑፍ ለጥቂት ከመቆፈሪያዬ መሣሪያ ድኖ ወጣ፥ ሊፈረክሰው ነበር። ሁለት ናቸው በፊትም በኋላም ተጽፎባቸዋል። እንደ ምን አለህ ተርቢኖስ ሩፊኖስ ነኝ።

ጽሑፉን ከድካሜ አርፌ ላቦቴን ጠራርጌ ካነበብኩት በኋላ በእጅጉ ልቤን ስለነካው ወደ ብራናዬ ገልብጬ ላንተ ለውድ ወንድሜ ልኬልሃለሁ እስቲ ረጋ ብለህ አንብበው።

የኢያሪኮ ሰዎች በሰሙት ወሬ የመደናገጥ ስሜት የተሰማቸው አይመስሉም። ሁሉም በየገበያው፥ በየመንገዱ፥ በየቤቱ ያውቀዋል። ዔናቃውያን የቁመታቸው መርዘም የግንባራቸው ጥንካሬ የልባቸው ኩራት ያንን የመሰለ ጦር ኃይል አሸንፎ ያንን የመሰለ ግንብ ሠብሮ የትኛው ጠንካራ ጠላት ነው የሚደፍራቸው:- ኢያሪኮአውያን ወደ ጥንቱ ኑሮአቸው ተመልሰዋል። የጭፈራ ቤታቸው በዘይት መብራቶች ሌሊቱን በሙሉ ዛሬም ይጨፈርባቸዋል፥ የሴተኛ አዳሪ ቤቶች አሁንም ክፍት ሆነው ያስተናግዳሉ፥ የተሸለሙ ልጃገረዶች ዛሬም ባልታወቁ አፋኞች እየተወሰዱ ይደፈራሉ፥ የኃጢአት ጽዋቸው ሞልታ ልትፈስ ደርሳለች።

ባሻገር ደግሞ እጅግ ብዙ መንጋ የዮርዳኖስን ወንዝ በደረቅ መሬት ተሻግሮ ወደ ፊት ይተምማል። ድምፅ የለም፥ መለከት የለም። ጦርነት የለም። ፀጥ ረጭ ብሎ ወደፊት መትመም ብቻ! ያ የሕዝብ መንጋ የሦስት ቀን መንገድ ያህል ሲቀረው በዮርዳኖስ ሸለቋማ ሜዳ ላይ ከዳር ዳር ተነጠፈ። አይንቃንቅም ብቻ ማታ ማታ በየድንኳኑ እሳት ቦግ ቦግ ሲል ይታያል። ኢያሪኮን ፊት ለፊቱ አየና መንጋው ከመጓዝ ታገደ።

## ውጊያው

ከባስልዮስ ዘቂሣርያ

ይህ ሁሉ ለኢያሪኮአውያን ግሩም ድንቅ ሆኖባቸዋል። ይሁን እንጂ ያ መንጋ ያቺን የጨረቃ ከተማ ሠብሮ ድል ያደርጋል ብለው አሁንም ማሰብ ቀርቶ አልጠረጠሩም። አንዲት ነፍስ ግን በጭንቀት ላይ ነበረች።

ወሬውን የሰማችው ከኢያሪኮአውያን እኩል ነው። ነገር ግን ለሷ ወሬ ብቻ አልሆነም። ልቧን የበረበረ ዜና ጭምር እንጅ! ይህ መንጋ በኤርትራ ባሕር፥ በምድረበደና በአሞራውያንና በባሳን ያደረገውን በዮርዳኖስም የሠራውን ተአምር ሲነገራት አንድ ነገር በልቧ ውስጥ ገብቶ ኀሊናዋን ያቃጥለው ጀመር። ይህ መንጋ በማን ኃይል ነው የሚንቀሳቀሰው? ለዚህች ሴት የልቧ ትርታ ነበር። ኢያሪኮን ለማጥፋት እንደማይሳነው ዐወቀች እናም የዚህን ኃይል ማንነት በልቧ ታምሰለስለው ነበር።

ተርቢኖስ እግዚአብሔር ድንቅ ነው። የዚህችን ሴት ልቡና መረመረ ሳታየው ትእዛዙን እንኳን ሳትሰማ እንደፈለገችው አየ። እናም እግዚአብሔር ኢያሪኮን ከማጥፋት ይገርም ሃል ሦስት ቀን ዘገየ።

ይህች ሴት ረዓብ የተሰኘች ጋለሞታ ናት። ቤቷ በኢያሪኮ ድንበር ግንቡን ተለጥፎ ይገኛል። ሦስት ልጆች አሏት የምትኖረው ግን በሴተኛ አዳሪነት ነው። ቤቷ የኢያሪኮ መኳንንት መዝናኛ በመሆኑ በሌሎች ዘንድ የተፈራ ነው። በውበትዋና በአቀራረብዋ የማይማረክ አልነበረም። የቤት አያያዝዋ የሚያስደስታቸው ሁሉ ከሩቅ አገር ድረስ ረብዓን ፍለጋ ይመጣሉ።

የምታደርጋቸው ጌጦች የሩቅ ምሥራቅና የቱርክ ፈርጦችና ዕንቁዎች ናቸው። ልብሶቿ እንኳን በፋርሶቹ ጥበብ የተካኑት የሐር ቀሚሶች ናቸው። ረዓብ ከቤቷ ሠገነት ተቀምጣ የምሽቷ ፀሐይ በቤቷ ላይ ስትፈነጥቅ ከሰማይ የወረደች ልዕልት እንጅ ምድር ያበቀለቻት ስለማትመስላቸው የኢያሪኮ መኳንንትና መሳፍንት በአንድ አፍታ ግቢዋን ይሞሉታል። የመጀመርያ ባልዋ የኢያሪኮ ጦር መኰንን በመሆኑ ግቢው እጅግ ሠፊና ለመኳንንት ማስተናገጃም ታስቦ የተሠራ ነበር። ከግቢዋ በስተግራ የባልዋ እናት የነበሩት «አላረጅም አሉ» እያሉ የኢያሪኮ ነዋሪዎች የሚያሟቸው አማቷ ይኖራሉ። ነዝናዛ ቢጤ ናቸው። በምራታቸው ድርጊት ስለሚቀኑ አንድቀን በቅን ልቡና ተጫውተው አያውቁም።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ረዓብ ይህን ነገር ከሰማች ጀምሮ ከቤቷ ሠገነት ተቀምጣ በምሽት ፀሐይ ፍንጣቂ እንደ ኮከብ ማብራቷን ትታ በቤቷ እልፍኝ ውስጥ ማሰብ ጀምራለች። ልጆቿም ከእናታቸው ፊት ላይ ያልተለመደ ነገር በማየታቸው ተደናግጠው ዙሪያዋን ከበዋታል። እኒያ ነዝናዛ አማቷ ደግሞ ደርቡን እያንጋነኑ ገቡና «ምንድነው አንቺ ተጨንቀሽ ልጆቼን የምታስጨንቂያቸው። ዔናቃውያንን ንቀሻቸው ነው የፈለገው መንጋ ይምጣ!» አሉና ደነፉባት ፀባያቸውን ስለምታውቅ ቀና ብላ አየቻቸውና ዝም አለች። ቤቷ ከግንቡ አጠገብ ነው ይህ የዮርዳኖስ ወንዝ ያልገደበው መንጋ ከመጣ የመጀመሪያ ዒላማው እርሷ ናት ያ ኃይል አደገኛ ነው።

ልጆቿን አስከትላ ወደ ዋናው በር ወጣች ሁለት ሰዎች እያለከለኩ ወደ ግቢዋ ይሮጣሉ ከኋላ ደግሞ ዔናቃውያን ጦራቸውን ወድረው ይከተሉዋቸዋል። አማቷ ደንግጠው በር በሩን ሲያዩ ቆዩና ልክ ሰዎቹ ሲገቡ «ውጡ ውጡ ይኼኮ የተከበረ ቤት ነው!» አሉና ደነፉባቸው ሰዎቹ የሚደር ሱበት ጠፋቸው ዔናቃውያን አዳኞች ደግሞ ከኋላ እየደረሱባቸው ነው።

ረዓብ እየሮጠች ወረደችና «ግቡ ግቡ ግቡ እያለች ወደቤቷ አጣደፈቻቸው ረዓብ ሰዎችን እልፍኝ አስገብታ በበሩ ብቅ ስትል አማቷ እየተጣደፉ ከግቢው ወጥተው ወደ ዔናቃውያን አዳኞች አመሩ። «ገብተዋል ረዓብ ናት ያስገባቻቸው ገብተዋል! እነዚያውላችሁ» በጣታቸው ወደ እልፍኙ እየጠቆሙ ሲውረገረጉ አየቻቸው። በፍጥነት ሁለቱን ሰዎች እየመራች ወደ ሠገነቱ ከወጣችና ከላይ ምንጣፍ ከምንጣፉ ላይ ደግሞ የተልባ እግር ከመረችባቸው።

ረዓብ ወደ እልፍኙ ስትገባ አዳኞቹ አፈጠጡባት «የታሉ እነዚያ ሰላዮች» ጦሩን እየነዘረ ጠየቃት «የትኞቹ» ረዓብ ፈገግ አለች «አሁን ከቤትሽ የገቡት አማትሽ ነግረውኛል» እነርሱኮ ወደውስጥ አልገቡም በግቢው አጥር ዘለው ነው የሄዱት ደግሞ ሰላይ መሆናቸውን አላወቅኩም። ረዓብ ቀኝ እጇን ከኮስታራው አዳኝ ትከሻ ላይ ስታሳርፈው ንዴቱ እየበረደለት መጣ።

«የእስራኤል ሰላዮች ናቸው እስቲ እንፈልጋቸው» ሠገነቱ ወጣ የተረበረበ የተልባ እግር ብቻ ይታያል ከተልባ እግሩ ላይ ወጥተው በግቢው አይናቸውን አማተሩት ከዚያ ወደ ሌሎች ክፍሎች ተዘዋወሩ የሉም።

«ወዴት ነው የሄዱት ኰስታራው አዳኝ ንዴቱ ገነፈለ።

«ወደ ሸለቆው መሰለኝ» አዳኞቹ እየተምዘገዘጉ ወጥተው አጥሩን በመዝለል ወደ ሸለቆው ከሌሎች ጦረኞች ጋር ሮጡ።

ፀሐይዋ በምዕራብ መጥለቅ ያዘች። እንደ ድሮው ግን የምታበራ ኮከብ በሠገነቱ ላይ አላገኘችም። በዚያ ምትክ የተረበረበ የተልባ እግር ተከምሮበታል። ጊዜው እየመሸ ሲመጣ ረዓብ ሰላዮቹን ከተልባ እግሩ ሥር አወጣቻቸው።

የደስታና የጽንዓት መንፈስ ከፊታቸው ይነበባል። እየመራች ወደ እልፍኟ ወስዳቸው ምግብ አቀረበች ረዓብ ሰላዮቹ የመጡበትን ምክንያት ሲነግሩዋት ያ ጥርጣሬዋ እውን ሆኖ ታያት ለዚያች ለምትወዳት ለኢያሪኮ አዘነችላት ሰላዮቹም የፊቷን በሀዘን ጥላ መከበብ ሲመለከቱ «ለምን ታዝኛለሽ» አሏት «እናንተ በዮርዳኖስ ማዶ ያደረጋችሁትን ሁሉ ሰምቼ ልቤ ታወከብኝ አምላካችሁ ኃያልና ሁሉን ማድረግ እንደማይሳነው ዐወቅሁ እናም ኢያሪኮን ስታጠፉ እባካችሁ ራሩልኝ።

ዕንባዋ ፊትዋን አለበሰው ሰዎቹ ደነገጡ በኢያሪኮ ከተማ ልበ ርኅሩኅ ተአምር ያልሠራላትን እግዚአብሔርን የምታምን ሴት መገኘቷ በእጅጉ አስደነቃቸው ተያዩ። ካሌብ ወደ ረዓብ እየተመለከተ «አይዞሽ እኛ ኢያሪኮን ስናጠፋ እግዚአብሔርን አምነሻልና ለኛም ታላቅ ውለታን አድርገሻልና አንቺና ቤትሽን እንምራችኋለን ነገር ግን በዚያ ቀን ቤተሰብሽን ሰብስበሽ በቤትሽ ተገኝ። በቤትሽ በርም ቀይ ፈትል አውለብልቢ ይህን ካደረግሽ ከሞት እናድንሻለን ያለበለ ዚያ መሐላችን አይሠራም»።

ሁለቱን ሰላዮች ሲመሽ ረዓብ በግንቡ አዘልላ ሸኝታቸው ወደ ተራራው ሸሽተው እንዲቆዩም መከረቻቸው...

ያ መንጋ ከሠፈሩ ተነሣ ወደ ኢያሪኮም እየተመመ መጣ። ከፊት ለፊት ካህናቱ ታቦተ ሕጉን ተሸክመው ከዚያም ሕዝቡ ፀጥ ረጭ ብሎ ያለአንድ ኰሽታ ይከተላል። ጉዞ ወደ ኢያሪኮ ምንም ድምፅ አይሰማም እንደ ዘንዶ ብቻ እየተጠማዘዘ ወደ ከተማዋ እየተቃረበ ነው ይህ ሁሉ ለኢያሪኮ ነዋሪዎች ምናቸውም አልነበረም።

ረዓብ በግንቧ ላይ ሆና ያ ሠራዊት ግንቡን ሲዞር በፀጥታ አየችው ልጆቿን ሰብስባ በሠገነቱ ላይ ተቀምጣለች ቀዩ ፈትል በግንቡ ላይ ይውለበለባል አማቷ ግን እምቢ ብለው ከዚያችው ከደሳሳ ግንባቸው ይኖራሉ። ስድስቱ ቀናት በሚያስደንቅ ዝምታ አለፉ። የዔናቃውያን ሠራዊት ገርሟቸዋል። መሣርያ አልያዘም ጦር አልታጠቀም ድምፅ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አያሰማም ግን በዝምታ ግንቡን ይዞራል። ግማሹ እጃቸውን ሊሰጡ አስበዋል፥ ይላል ሌላው ደግሞ ድብቅ ጦር ከኋላ አስከትለዋል እያለ ያማል።

የረዓብ አማት እየተውረገረጉ መሰላሉን ወጡና «አንቺ ቀዩን ፈትሌን አምጭው!» አሉና አፈጠጡባት «ምን ያደርግልዎታል ዋጋውን ልስጥዎት» አለቻቸው። «አልፈልግም፥ አልፈልግም ቀዩን ፈትሌን!» አሉና ወደ ግንቡ ጠርዝ ተራምደው ታሥሮ ይውለበለብ የነበረውን ቀይ ፈትል በጠሱና ይዘውት ወረዱ።

ረዓብ ተስፋዋ ጨለመ። ኢያሪኮን የሚያፈርሰው ያ መንጋ ግንቡን ያዞራል። ካሌብ ቀና ብሎ የረዓብን ቤት አቅጣጫ ተመለከተ ቀዩ ፈትል የለም። ድንጋጤ ወረረው «የት ሄደች» አለ በልቦናው ያች ሴት ግን በሽብር ውስጥ ነበረች ቤቷን በሙሉ ፈተሸች ቀይ ፈትል ግን የላትም። ልብሶቿ ሁሉ የሃር ፈትል ናቸው። ቀይ ፈትል የላትም ምን ታድርግ፥ ምን ታውለብልብ፥ ያላት አማራጭ ወደ ገበያ ወርዳ መግዛት ብቻ ነው ግን ባጋጣሚ ግንቡ የወደቀስ እንደሆን።

ሮጠች...በረረች...ወደ ገበያ። ካሌብ ደግሞ አብሮት ከሰለለው ከሰሎሞን ጋር ወደ ረዓብ ቤት አቅጣጫ እየተመለከቱ «የመፈተሻው ጊዜኮ ደረሰ 13 ዙር ነው የምንዞረው። አሁን አስራ አንደኛ ጊዜ ነው» አለው።

ረዓብ ገበያ ስትወርድ ገበያተኛው ተነሥቷል ያንን በዝምታ የሚዞር መንጋ ለማየት በየ ግንቡ ቆሞአል ምን ታድርግ ወደምታውቃቸው ገበያ ሻጮች ቤት ሮጠች የሉም ጨነቃት ጠበባት ኢያሪኮም ደግሞ ልትፈርስ ነው ያ ቀይ ፈትል መውለብለብ አለበት ግን የለም። «ረዓብ – ረዓብ» አንዲት ባልቴት ጠሩዋት ዕንባዋ በጉንጮቿ ይወርዳሉ ዓይንዋ ደፍርሶአል። እጆቿ በሀዘን የተሰበሩ ይመስል ደረቷ ላይ ተለጣጥፈዋል። ቀና ብላ ወደ ቤቷ ስትመለከት ልጆቿን አማቷ ይዘዋቸው ወረዱ:-...

«ምን ሆንሺ ረዓብ» ባልቴቷ ወደርስዋ ቀረቡ «ቀይ ፈትል ፈልጌ» ነይ ነይ እኔ እሰጥሻለሁ። ምን ያህል ገንዘብ እንደሰጠቻቸው እንኳን ትዝ አላላትም። የመቀማት ያህል ነው የመነጨቀቻቸው። ሩጫ ወደ ቤቷ...

ምን አይነት ጠማማ ቀን ነው አማቷ ልጆቿን የት ወሰዱባት ፈትሉን አንጠልጥላ ወደ ቤታቸው ገባች ቤቱ ባዶውን ነው ምድር ተከፍታ ብትውጣት ደስ ባላት ካሌብ ቀና ብሎ አሁንም አየ። አሁን በደስታ ፈካ ቀዩ ፈትል ይውለበለባል። ያ – መንጋ ኢያሪኮን ሊያፈርስ አንድ ዙር ቀርቶታል። ረዓብ ግን በቤቷ የለችም። ልጆቿን ፍለጋ ትንከለከላለች።

እኒያ ነዝናዛ አማቷ የት አደረሱዋቸው ዳግመኛ ግቢውን ለቃ ወጣች። ግን የት ትፈልጋቸው ዱካ የለሽ ናቸው አማቷ አይ ሰው ሊድን ሲፈልግ የመሰናክሉ ብዛት

ያ – መንጋ ሩቡን ግንብ ዞሮታል። ልጆቿ የሉም ደጋግማ በስማቸው ጠራቻቸው ምላሹን አልሰጡዋትም ወደ ጐረቤቶቿ ቤቶች ገባች አላገኘቻቸውም።

ያ መንጋ ግማሹን ግንብ ዞሮታል ልጆቿ አልተገኙም

ምን ትሁን ዕንባ ብቻ። መሬት ላይ ተቀምጣ ተንሰቅስቃ አለቀሰች ዓይንዋ ትኩስ በርበሬ መሰለ። ሰውነቷ በአንድ ቀን ሀዘን ብቻ ውልቅልቁ ወጣ። ሀዘን ከመርዝ ይበልጣል።

«እማም እማዬ» ሴት ልጇ እየሮጠች ወደርስዋ ስትመጣ ተመለከተቻት የትናችሁ የትናችሁ ረዓብ አጣደፈቻት።

«እዚያ ቤት» ምን ትሠራላችሁ» እማማ ናቸው የወሰዱን? ወደ ቤት ግቢ ሩጭ»

ያ–መንጋ ሩብ ግንብ መዞር ብቻ፤ ቀረው ምንም አማራጭ የላትም የእናትነት አንጀት ደግሞ አልችል አላት ጊዜው ደረሰ መዳን ወይም መሞት ቀይ ፈትሉ ግን አሁንም ይውለበለባል።

ረዓብ ጨነቃት፤

በረረች...ተፈተለከች...እየተን ደረደረች ወደ ሰዎቹ ቤት ስትገባ ወይናቸውን እየጠጡ ይሳሳቃሉ ልጆቿን በእጆቿ እየጐተተች ስትወጣ አማቷ ተከተሏትና አንዱን ነጠቋት ና...ና...ና የኔ ልጅ ና ይዘውት ገቡ በሩን ከውስጥ ዘጉባት። ተስፋ ቆረጠች። አሁንም ወደየዘመድዋ ቤት እየተንከለከለች እሺ ያሏትን ወደቤቷ ሰደደቻቸው

ያ መንጋ – የሩብ የሩብ ሩብ ግንብ መዞር ብቻ ቀረው

ምንም ማድረግ ስላልቻለች ዘመዶቿ ከበቧት፥ በሩጫ ወደ ቤቷ፥ ልክ እሷ በሠገነትዋ ስትቀመጥና ግንቡ ሲፈራርስ አንድ ሆነ። ያ ዝምተኛ መንጋ ከተማውን ወረረው ትርምስ ሆነ። ሰልሞን በሩጫ ወደቀዩ ፈትል ሮጠና እያጣደፈ ረዓብንና ዘመዶቿን ብሎም ሁለት ልጆቿን አወጡ። አንዱ ግን በቃ ቀረ ምን ታድርግ ቀረ ልቧ አነባ። ስንድን ምናልባት የሚቀሩብን ነገሮች እንደሚኖሩም እናስብ። ዓለም አንድ የምትነጥቀን ና የምታስቀርብን ነገርም ሊኖር ይችላል።

ኢያሪኮ አመድ ከዱቄት ሆነች ረዓብ ግን በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ነበረች ያ በሩቅ ያመነችው አምላክ አዳናት።

ተርቢኖስ በዚህ ዓለምኮ እንደ እግዚአብሔር ታማኝ የለም። ረዓብ አመነች እምነቷንም ሰላዮቹን በመደበቅ በተግባር ገለጸች። ደም እስከታነባ ለድኅነት ተዋጋች እናም በመጨረሻ አሸነፈች። አዎ የእግዚ አብሔር ሰው ለድኅነት ይዋጋል፥ ብሎም ያሸንፋል። ❖



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ማዳኑን ያዩ ይናገሩ

ከእሥራኤል ነዋሪዎች ጋር ‹በሳተላይት› የተደረገ ቃለመጠይቅ – ከባስልዮስ ዘቢሣርያ

ይኼን ቃለ መጠይቅ በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ እየተዘዋወረ ያቀናበረልን ተርቢኖስ የተባለ ዕውቅ ታሪክ ጸሐፊ ሲሆን ቀራንዮ ከሚገኘው የወንጌል ዓለም አቀፍ የሳተላይት ጣቢያ እየተቀበለ ለእኛ ያስተላለፈልን ደግሞ አዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው የተዋሕዶ መንፈሳዊ የሳተላይት መቀበያ ጣቢያ ነው።

ለሁለቱም ምሥጋናችን በሐመር ስም ይድረስልን።

በቅድሚያ የተጓዝኩት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ ተአምሩን ወዳደረገበት ወደ ቃና ዘገሊላ ነበር። ከገሊላ ባሕር ምዕራብ ወደ 80 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ከናዝሬት ከተማ በስተምሥራቅ በኩል የምትገኝ አነስተኛ ከተማ ናት። እዚህ ከተማ እንደገባሁኝ መጀመሪያ ያቀናሁት በመሐል ከተማዋ ተንጣሎ በሚገኘው ግቢ ውስጥ ወደሚኖረው ወደ ዶኪማስ ቤት ነው። የሚኖረው በዮሐንስ ክፍለ ከተማ ከፍተኛ 2 ቀበሌ 1 ነው።

ዶኪማስ የጌታ የመጀመሪያ ተአምር እንዴት በርሱ ቤት ሊደረግ እንደቻለና ሌሎችን ነገሮች አንሥቶ ያጫውተኝ ዘንድ የጠየቅኹት ገና የግቢውን በር አንኳኩቼ ስገባ ከውስጥ አግኝቸው ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ነበር። እርሱም በርካታ ፈገግ ብሎ እጄን ይዞኝ ወደ እልፍኙ ወሰደኝና በክብር ያስቀመጣቸውን 6ቱን የድንጋይ ጋኖች አሳየኝ። እኔም ያንን የመሰለ ተአምር የተደረገበትን የድንጋይ ጋኖች በማየቴ እግዚአብሔርን ካመሰገንኩ በኋላ ወደ ውይይታችን ገባን።

ተርቢኖስ – ለመሆኑ ጌታ እመቤታችንና ሐዋርያት እንዴት በሠርጉ ሊገኙ ቻሉ?

ዶኪማስ – እመቤታችን የናዝሬት ከተማ ሰው ነች። ደግሞም ዘመዴ ናት። ናዝሬት ደግሞ ቢበዛ 5 ኪ.ሜ የምትርቅ ናት። ብዙ አንራራቅም እናም እሷን ስጠራ አብሬ የማይነጠለውን ልጇን ጠራሁ። ልጇን ስጠራ ደግሞ መለየት የሌለባቸውን ሐዋርያቱን አብሬ ጋበዝኳቸው።

ተርቢኖስ – እመቤታችንን ከነ ልጇ ስትጠራት እንዴት ተቀበለችህ?

ዶኪማስ – ልጇም ሆነ እርስዋ በደስታ ነው የተቀበሉኝ። ዛሬምኮ ጌታችን የሚጠራው ጠፋ እንጂ በማናቸውም የሕይወታችን ጉዳይ ሊገኙልን ፈቃደኛ ነው። ታዲያ ምን ያደርጋል ራሳችን እንሠራዋለን እያልን በትዕቢትና በኩራት ስንንጠራራ የቀየስነው ሕይወት ከንቱ ሆኖ ይቀርብናል። አንዳንዶቻችን ደግሞ ብቻውን ልንጠራው ሌሎች እናቲቱን ብቻ ልንጠራ እንፈልጋለን። ልጇ ከተጠራ እናቱም መጠራት አለባት እናቱ ከተጠራች ልጇ አይነጠላትም። ጌታ ከመጣ የእርሱ ወዳጆች የሆኑ ሐዋርያትና ቅዱሳን አይለዩም። ሦስት ጉልቻ ማለት ይህ ነው ጌታ እመቤታችንና ቅዱሳን የተገኙበት ሕይወት።

ተርቢኖስ – እስቲ ስለዚያች የሠርግ ቀን ውሎ ተርክልኝ?

ዶኪማስ – መቼም ግሩም ድንቅ ነው! በጓዳ የነበረው የወይን ጠጅ እንደኔ አመለካከት ብዙ ነበር። ነገር ግን በጣም ይገርምኻል ገና ታዳሚው አንድ ቀምሶ ሳይደግም ዘግይቶ የገባው ሳይቀምስ አስተናጋጆቹ ጠጅ እኮ አለቀ ብለው ነገሩኝ። ፊቴ ተለዋወጠ፥ ላብ አጠመቀኝ፥ ውርደት ወረረኝ! በዚህ ጊዜ ነው በሚያስደንቅ ሁኔታ እመቤቴ ወደእኔ የመጣችው። ከጓዳው በር አጠገብ አንገቴን ደፍቼ ተቀምጬ ነበር «ዶኪማስ» ብላ ስትጠራኝ ቀና አልኩኝ። «ምነው ድግሱ ተበላሸብህ?» ብላ ጠየቀችኝ። ችግሬን በሙሉ ነገርኳት። «ምንም ችግር የለም አትዘን» አለችኝና ከደቀመዛሙርቱ ጋር ወደተቀመጠው ልጇ ሂዳ ነገረችው። ወዲያውም «ካንቺ ጋር ምንአለኝ? ጊዜዬ ገና ቢሆን (እውነተኛ የወይን ጠጅ የምሰጥበት) እንጂ ለዚሁ ችግር የለም ብሎ ወደኔ መጣ። እመቤቴም ለአስተናባሪዎቹ «በሉ የሚላችሁን ቶሎ አድርጉ» ብላ ነገረቻቸው። 6ቱን የድንጋይ ጋኖች አጥበን ውሃ ሞልተን አቀረብናቸው። ወዲያውም በሚያስገርም ጥበቡ ጌታችን ውሃውን የወይን ጠጅ አደረገልኝ የተንቆረቆረው ላቤ ደረቀ፥ የከሰለው ፊቴ ፈካ፥ የደነገጠው ልቤ ተረጋጋ ከእፍረት፥ ከውርደት አዳነኝ እልሃለሁ።

ተርቢኖስ – ታዲያ ከዚህ ታሪክ ምን ትምህርት አገኘህበት?

ዶኪማስ – በሕይወታችን ጉዳዮች ሁሉ ጌታን ከእናቱና ከቅዱሳኑ ጋር የምንጠራው ከሆነ ይገኝልናል። እኛ የሰው ልጆች አለን የምንለው ሕይወት፥ ትዳር፥ ዕውቀት፥ ሀብት፥ ጉልበት፥ ሰላም፥ ፍቅር በመሐል ቤት ሊያከትም፥ ሊበላሽ፥ ሊጠፋና ሊናወጥ ይችላል። በዚህ ጊዜ በአካልም በመንፈስም ውድቀት ውርደትና ኃፍረት፥ የበታችነትና ሐዘን፥ ትካዜና ድህነት ሊደርስብን ቢችሉ እንኳ የሰው ልጆችን የልብ ትርታ ፈጥና የምትረዳው እመቤት ከልጇ ከወዳጇ አማልዳ ኑሮአችን እንዲስተካከል፥ የወደቀው እንዲነሣ፥ የተሰበረው እንዲጠገን፥ የተናወጠው እንዲጸና፥ የተበላሸው እንዲጠራ ታደርግልናለች። የሚጣፍጠውን የወይን ጠጅ ታሰጠናለች። እኛ የሰው ልጆች ዛሬ ወይን ያለቀብን ጋኖች ነን። ስለዚህም ወደ እመቤታችን መለመን መጸለይ ይገባናል። ጌታን ጋኑን ሙላልኝ ማለት ይጠበቅብናል። የፍቅር ወይን፥ የሰላም ወይን፥ የመተባበር ወይን፥ የጤንነት ወይን፥ የመተሳሰብ ወይን፥ የመረዳዳት ወይን፥ የመተዛዘን ወይን፥ የአገልግሎት ወይን፥ የመንፈሳዊነት ወይን አልቆብናል። ስለዚህም መጮኽ ያስፈልገናል። በዚህ ጊዜ ጋኑ እንዲታጠብ እንታዘዛለን ይህም የንስሐ እጥበት ነው። ከዚያም እውነተኛው አምላካዊ ወይን ይሰጠናል።

ተርቢኖስ – አሁን ከዚያን ቀን ወዲህ ያለህ የሕይወት ለውጥ ምንድን ነው?

ዶኪማስ – ዛሬ ችግር፥ ሐዘን፥ ሲደርስብኝ ብዙ አልከፋም አልበሳጭም። የራሴን አማራጭ ብቻ ይዤ አልንገታገትም መጀመሪያ ወደ ልዑል እግዚአብሔር እሄዳለሁ። ከዚያም እርሱ ይፈታልኛል። እነዚያን ጋኖች በጥንቃቄ ለትውልድ አቆያቸዋለሁ ብዬ አስባለሁ ለሁሉም እግዚአብሔር ይርዳኝ።

ተርቢኖስ – አሜን ዶኪማስ አመሰግናለሁ እግዚአብሔር ይስጥልኝ።

ዶኪማስን ተሰናብቼው እስከ ናዝሬት ከሸኘኝ በኋላ ተለያየን። ከዚያም በሠረገላዬ ሆኜ ከጥብርያዶስ (ገሊላ) ባሕር አጠገብ ወዳለችው የቅፍርናሆም ከተማ ተጓዝኩ። ❖

ይቀጥላል



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# እናስተዋውቃችሁ

በዚህ ዓምድ ገዳማትን፥ አድባራትን፥ ታሪካዊና ተአምራዊ ቦታዎችን፥ የቤተክርስቲያን አባቶችን እናስተዋውቃለን።

## ከቦረዳ ዋሻ ጽላት ወጣ!

ከሐመር ዘጋቢ

አምና ጥር 1985 ዓ.ም. ቁጥር 1 ሐመር መጽሔት አስደናቂ ታሪክ ይዛ ብቅ አለች። መላ ኢትዮጵያ ተደንቀ አብዛኛው በታሪኩ እውነተኛነት ላይ ተጠራጠረ ጥቂቱ ግሩም ድንቅ የአምላክ ሥራ አለ። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተቀናቃኞች የፈጠራ ታሪክ አሉ። ብዙ ተባለ ቦረዳ ግን ከኢትዮጵያ አልፎ ባሕር ማዶ ታወቀ።

### የታሪኩ መነሻ እንዴት ነበር?

ሃይማኖት የለሹ ሰው ከማለዳው አንድ ሰዓት ላይ በሬዎቹን ጠምዶ ሊያርስ ይዘጋጃል። የጠዋት ፀሐይ ብርሃንዋን ፏ አድርጋለች ግን አወጣጥዋ ከወትሮው ለየት ያለ ነበር:- ለዚህ ወጣት ገበሬ። ከወትሮው ባልተለመደ ሁኔታ ጨረርዋን ሦስት ቦታ ከፍላ ታየችው። ይህን እንግዳ ክስተት የተመለከቱ አንዳንዶች ፈርተው ወደቤታቸው ሮጠው ሄዱ ባለታሪኩ ወጣት ገበሬ እንደሌሎቹ ወደ ቤቱ ሊሮጥ ቢሞክር አልቻለም። እግሩ መንቀሳቀስ ተሳነው ሽቅብ ሲመለከት በአየር ላይ ነጭ ድንኳን ተወጥሮ ታየው ሁለት መስኮቶች ነበሩት። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ በአየር ላይ ተወጥሮ የነበረው ድንኳን ከገበሬው ዓይን ተሰወረ ይህ የሆነው ኅዳር 19 ቀን ጠዋት ላይ ነበር።

የጠዋቱ ሁኔታ እውን አልመስልህ ያለው ገበሬ ከሰዓት በኋላ እንደገና በሬዎቹን ጠመደ:- ሊያርስ። ወዲያው የጠዋቱ ድንኳን እንደ በፊቱ በአየር ላይ ተወጠረ። ከድንኳኑ ውስጥም አራት ሰዎች ወጡ ከአራቱ ሁለቱ ወደ ወጣቱ ገበሬ ቀረቡ በቀኝ ያለው ቅዱስ ሚካኤል በግራ በኩል ያለው ቅዱስ ገብርኤል መሆናቸውን ገለጹለት። ገበሬውም ይህን ሲሰማ በአፍጢሙ ተደፋ። አጣድፈው በማስነሣት አጠገቡ ወዳለው ዋሻ ይዘውት ገቡ። በውስጡ ያሉትን ጽላት አሳይተው በአቅራቢያው ወዳለው ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ለካህናቱ እንዲናገርና ጽላቱ እንዲወጡ አሳሰቡት።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአካባቢው ለክፍለ ዘመኑ ትንግርት የሚያሰኙ ክስተቶች ይከሰቱ ጀመር። የቅዳሴ ድምፅ፥ የከበሮ ምት፥ የዕጣን መዐዛ እንዲሁም ብርሃናውያን አካላት በአካባቢው ማታ ማታ ይታዩ ጀመር። ጠበል ፈለቀ ብዙ ሕሙማን ተጠምቀው ተፈወሱ። የክልሉ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ወደ ዋሻው ዘልቀው በመግባት በዋሻው ውስጥ ጽላት መኖሩን አረጋገጡ። ለአካባቢው ሕዝብ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ ትዕዛዝ ሰጡ። የአካባቢው ሕዝብ ሌት ተቀን በመትጋት በሌሎች አካባቢዎች ካሉት ምእመናን ጋር ሆኖ አዲስ ቤተክርስቲያን ሠራ። ቤተ ክርስቲያኑም የቅ/ሚካኤል መታሰቢያ ሆነ።


### ጽላቱ ከዋሻው በወጣበት ወቅት

ከአራቱም ማእዘን ቁጥሩ እጅግ በርካታ የሆነ ሕዝብ መጥቷል። አካባቢው የቀለጠ ከተማ መስሏል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ ቦረዳ ላይ የከተመ ይመስላል። ብዛት ያላቸው አውቶቡሶች መኪና የማይደፍረውን የቦረዳን ጐዳና አቋርጠው ዋሻው አካባቢ ተሰልፈው ይታያሉ። የሰው ዓይነት ነው የሚታየው።

ፈዋሹ የቦረዳ ጠበል ሽባውን ባንድ ቀን ሲፈውስ ያየ ሰው በዚያች ቅጽበት በዚያ አካባቢ ሕይወቱን ሙሉ ለማሳለፍ ይምላል። ብዙ አስገራሚ ክስተቶች ይታያሉ።

ወሩ ዝናም የማያቋርጥበት ወቅት መሆኑ አብዛኛውን ሰው አስግቶት ነበር በተለይ አካባቢው ትንሽ ዝናም ከዘነመ ጭቃ በጭቃ ስለሚሆን እንኳን ለመኪና ለሰውም ያስቸግራል። ይህን ያወቁት የድሮው ገበሬ የአሁኑ አባ ወልደገብርኤል ሱባዔ ይዘው ኖሮ አስቀድመው ታቦቱ ወጥቶ እንግዶች ወደየስፍራው እስኪመለሱ ለአሥር ቀን ያህል ዝናም በአካባቢው እንደ ማይዘንም አበሠሩ ሰው ይህን ጉድ እናያለን ብሎ በሆዱ ያዘ።

ቦረዳ የሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኤልያስ ገጥሞት አሥር ቀን ሙሉ ሰማዩ ኳ ብሎ እንደ ጠራ ምድሩም ጭቃ አልባ ሆኖ አለፈ። ጉድ እስከወዲያኛው ተሰኘ ከአሥር ቀን በኋላ ሰማዩ ቋጥሮ የያዘውን ዝናም



ጽላቱ የነበረበት ዋሻ መግቢያ በር



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



ጽላቱ ከዋሻው ወጥቶ ወደ አዲሱ ቤተክርስቲያን ሲያመራ

ዘረገፈው። ይህን የሄደ ሁሉ ያለምንም ማመንታት የሚመሰክረው ነው። እኔም ከሄድኩ ጀምሮ እስከተመለስኩበት ቀን ደመና የሚባል በአካባቢው ሰማይ ላይ ዘወር እንዳላለ ምሥክር ነኝ።

ቅዳሜ ሐምሌ 24/1985ዓ.ም. ከምሽቱ አሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጋር ሆነው ጽላቱን ሊያወጡ ወደ ዋሻው አመሩ። መቅረጸ ምስልና መቅረጸ ድምፅ የያዙ ብዙ ሰዎች የዋሻውን መሄጃ አጥረውታል እንደ ሰማይ ከዋክብት ስፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብ በሆታና በእልልታ በጭብጨባ የጽላቱን መውጣት ይጠባበቃል።

ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ከሁለት መነኮሳት ጋር ወደ ዋሻው ገቡ ከጥቂት ሰዓት በኋላ አስደናቂውና ተአምር ሠሪው ጽላት ከዋሻው አፍ በአባ ገ/ማርያም አክባሪነት ብቅ ሲል ሁሉም ነገር ጸጥ–እረጭ አለ። በዋሻው ዙሪያ የነበረው ሁሉ በድንጋጤ ፈዞ ቀርቷል። ከጥቂት ሰዓት በፊት የነበረ ርኩቻ ጭፈራ አሁን ምን ዋጠው? ድንጋጤ ይሆን ወይስ ደስታ? ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ዝምታው አስደንቋቸው መሰለኝ «እልል በሉ እንጂ» ሲሉ ፈዞ ቆሞ የነበረው ሁሉ እንደ ቅጠል ረገፈ በጽላቱ ፊት በግንባሩ ተደፋ። ከዚያ በኋላ ምድር ቁና ሆነች ከሩቅ በጠባቂዎች ታጥሮ የተያዘው ሕዝብ በካህናት በመነኮሳት እንዲሁም በምእመናን ታጅቦ የሚመጣውን ጽላት አንጋጦ እያዩ አካባቢውን በጭብጨባ በእልልታ በዝማሬ ደበላለቁት።

ጽላቱ ቀደም ብሎ በብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ቅብዓ ሜሮን የተባረከው አዲስ ቤተክርስቲያን ሲደርስ ምእመኑ የለበሰውን ጋቢ፣ ነጠላ፣ ሹራብ መሬት ላይ ማንጠፍ ጀመረ፡ ጽላቱን ያከበሩትን ካህንና ሊቀ ጳጳሱ እንዲረግጡት። ይህን ሳይ ጌታ በአህያ ውርንጫ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ የከተማው ሕዝብ ልብሳቸውን በመንገድ ላይ ያነጠፉት ታወሰኝ። የእምነት ውጤት ነው። ግን ውስጣዊ ልብም አብሮ ተነጥፎ ይሆን? መቼም ልባቸው ሳይፈቅድ ይህን አያደርጉ። አየ ቦረዳ! ስንቱን የክርስቶስ ባሪያ እንዲሆን አደረገችው! ዳግሚት ዮርዳኖስ።

ጽላቱ በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ አንድ ጊዜ ዞሮ በዓውደ ምሕረቱ ላይ በቆመ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ትምህርትና ቡራኬ ሰጥተዋል። በዚህም ትምህርታቸው። «አቤቱ አምላካችን ሆይ በዚህ ዕለት በመካከላችን ተገኝተህ ይህንን ሕዝብህን ትባርክ ዘንድ እንማልድሃለን እንለምንሃለን። ፈቃድህ ሆኖልን ብዙ ጊዜ ስንጠብቀው እና ደጅ ስንጠና ስንጸልይበት የነበረውን ነገር ሁሉ ፈጽመህ በዛሬው ዕለት ታቦቱ እንዲወጣ ፈቃድህ ሆኖ ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ በመንበሩ እንዲቀመጥ ስለፈቀድክልን እናመሰግንሃለን። የእግዚአብሔር ጸጋ እንዲያድርባችሁ እዚህ መጥታችሁ በጆሮአችሁ የሰማችሁትን በየቤታችሁ ደጅ ስትጠኑት የነበረውን ለማየት ስለበቃችሁ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን ‹ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር› እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራበት ጊዜ አለ። እግዚአብሔር እርሱ የፈቀደው ጊዜ ሲደርስ እንዲሁ በተአምራት ነገሮችን ይገልጻል። እንግዲህ እስራኤልን ሌሊት በብርሃን ቀን በደመና እየመራ ይመግባቸውና ይረዳቸው የነበረ እግዚአብሔር እኛንም በዘመናችን እነሆ ይህን ጸጋ ስለሰጠን ይህን ክብር ስለገለጸልን እኛ አገልጋዮቹ ባሪያዎቹ የእርሱን ማደሪያ ታቦቱን ተሸክመን ወደ ቤተ መቅደሱ እናስገባ ዘንድ በራእይም በገሃድም ስለረዳን እናመሰግነዋለን። እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ደብረ ሲና ውጣ ብሎ አዘዘው። ዐሠርቱ ቃላት የተጻፈበትን ጽላቱንም ሰጠው ሙሴም አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ጾሞ ከፈጸመ በኋላ ጽላቱን ይዞ ወርዷል።» በማለት ስለጽላት አመጣጥ ከብሉይ ጊዜ ጀምሮ ያለውን ታሪክ ባጭሩ ከተረኩ በኋላ «ሀገራችን ኢትዮጵያም ሀገረ እግዚአብሔር እንደመሆንዋ መጠን እግዚአብሔር የሚከበርበት ታቦት በብዙ ባህታውያን መነኮሳት አጠገብ ኖሮ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሊያርፉ ሲሉ በዋሻ ውስጥ እንደሚያኖሩት ገልጸው ይህም ጽላት ኖሮ ኖሮ ጊዜው ሲደርስ ተአምሩን እንደሚያሳይና ይህ አሁን የወጣው ታቦትም በዚያ አምሳል የኖረ የረዥም ጊዜ ዕድሜ ያለው ታቦት ነው። አሁን ከወጣንበት ዋሻ ውስጥ ብዙ ታሪካዊ ነገሮች አሉበት እንግዲህ አንዱ ቅዱስ በዚህ ዋሻ አኑሮ ሲጸልይበት የኖረ ነው ማለት ነው። እስከ ዛሬ መኖሩ ሲወራ ሦስት ዓመቱ ነው ነገር ግን በችኮላ የሚሆን ነገር ስለሌለ ሁሉ እስኪያምንበት ጊዜ ጠብቀን ዛሬ ፈቃደ እግዚአብሔር ሲሆን ወጥቷል። በዛሬው ቀን ሁሉ ነገር ተፈጽሟል።» በማለት ከመነ ሻው የነበረውን ሁኔታ አሳጥረው በመናገር ታቦቱ ወደ መንበረ ክብሩ ገብቷል።

በማግስቱ ሐምሌ 25/1985 ዓ.ም. ታቦቱ ከመንበረ ክብሩ ወጥቶ ቤተ ክርስቲያኑን ሦስት ጊዜ ከዞረ በኋላ በዓውደ ምሕረቱ ላይ ቆሟል። በዚህ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ በቦታው ለተሰበሰበው ምእመን ቃለ ቡራኬ ሰጥተዋል ቦታውንም ገዳመ ዮርዳኖስ ብለው ሰይመውታል።

ማጠቃለያ:- እንግዲህ እስከዛሬ ድረስ እግዚአብሔር በቦረዳ ያደረገውን ስናስነብባችሁ ከርመናል። ናትናኤል ፊልጶስን «ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን?» ብሎ በጠየቀው ጊዜ የፊልጶስ መልስ «መጥተህ እይ» የሚል ነበር እኛም የተናገርነውን እውነትነት እናንተም በዓይን አይታችሁ በአንደበት ለመመሥከር እንድትችሉ ወደ ቦረዳ ብቅ በሉ እንላለን።

በመጨረሻም ልንለው የምንፈልገው ነገር ቢኖር አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር በቦታው ስላደረገው ተአምር ከማመስገን ይልቅ ያላዩትን አይተናል ያልሰሙትን ሰምተናል በማለት የግል ክብራቸውንና ከንቱ ዝናን ለማግኘት ሲሯሯጡ ተመልክተናል ይህ ዓይነቱ ድርጊት ምእመናን ወደቦታው መጥተው በረከትን እንዳያገኙ ታሪኩን ተረት የሚያስመስል ስለሆነ ተናጋሪዎቹም ሆኑ ሰሚዎቹ ሊያስቡበት ይገባል።

የእግዚአብሔር ተአምር አያልቅምና በሌላም ቦታ የሚሠራውን ተአምር ማቅረብ እንችል ዘንድ የአንባብያንን ትብብር እንጠይቃለን።

እግዚአብሔር ሁላችንን ይባርክ፤ አሜን። ✣

# መታዘዝ ይበልጣል

1ኛ ሳሙ. 15፥22

እምሻው ዑመታ – ከወንጂ

ነቢዩ ሳሙኤል «መታዘዝ ከመስዋእት ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል።» በማለት በአንድ ዐ.ነገር ጥምር መልእክት አስተላለፈ። ሳሙኤል በዕንባ በጾምና በጸሎት የተገኘ የእናቱን ጡት መጥባት እንደተወ ዕድሜውን ሁሉ ለአገልግሎት ለእግዚአብሔር የተሰጠ:- በቤተ መቅደስ ውስጥ ታቦቱ ባለበት ሥፍራ እግዚአብሔር በታቦቱ እያደረ ሲያነጋግረው ያደገ:- በእግዚአብሔርም ፊት ሞገስ ያገኘ ታላቅ ብላቴና ነበር። በእግዚአብሔር መንፈስ የሚናገረውም ቃል አንዳች በምድር ላይ አይወድቅም ነበር፤ የተናገረው ሁሉ የሚፈጸም ነውና።

የእሥራኤል ሽማግሌዎች ተሰብስበው እንደአሕዛብ ንጉሥ አድርግልን ባሉት ጊዜ በተሰጠው ሞገስ እግዚአብሔርን በጸሎት ጠይቆ ሳኦልን ያነገሠላቸው ሳሙኤል ነው። እግዚአብሔር አማሌቃውያን በእሥራኤል ላይ ፈጽመውት የነበረውን ግፍ የሚበቀልበት ወቅት በደረሰ ጊዜ ሳኦል አማሌቃዊያንን አንድ ሳያስቀር እንዲያጠፋ በሳሙኤል አንደበት ነገረው። በሳሙኤል አንደበት በተነገረው በእግዚአብሔር ድምፅ «አማሌቅን ምታ ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፥ አትማራቸውም። ወንዱንና ሴቱን ብላቴናውንና ሕፃኑን በሬውንና በጉን ግመሉንና አህያውን ግደል» ተባለ።

እሥራኤል በእግዚአብሔር ታዲገነት አራት መቶ ሠላሳ ዓመታት ከተገዙበት የግብፅ ባርነት ተለቀው ወደምድረ ከነዓን ሲመለሱ አማሌቃውያን መንገድ አናሳልፍም ብለው በጦርነት አሰቃይተዋቸው ነበር። ለዚህ ነው እግዚአብሔር አማሌቅን ለመበቀል የተነሣው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ 12፥9 «ተወዳጆች ሆይ ራሳችሁ አትበቀሉ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ በቀል የእኔ ነው። እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና» በማለት አስተምሯል። ዘሌ.19፥18፣ ዘዳ.32፥35።

ሳኦል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተቀብሎ ጌል ጌላ በተባለች ሥፍራ ሕዝቡን ሰብስቦ በብዛት ሁለት መቶ ሺ እግረኛ ጦር ከአይሁድ ደግሞ አሥር ሺ ሰዎችን በመመልመል ወደ ውጊያ ወረዳ ጉዞውን አቀና። አማሌቃውያንን ከኤውላጥ ጀምሮ በግብፅ ፊት እስካለችው እስከ ስር ድረስ መታ ነገር ግን ሳኦልና ሕዝቡ በጦርነቱ የተገኘው ምርኰ አሳሳቸውና ታላላቁን በመተው ምናምንቴንና የተናቀውን ብቻ ፈጽመው በማጥፋት ትእዛዝ አፈረሱ። የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ ነደደ። ሳኦል እግዚአብሔርን ከመከተል ስለተመለሰ ትእዛዙንም ስላፈረሰ «ስላነገሥሁት ተጸጸትሁ» አለ እግዚአብሔር ለሳሙኤል።

ሳሙኤል ጊዜ ሳያጠፋ ከሳኦል ጋር ተገናኘ «ይህ የምሰማው የበሬና የላም ግሳት ምንድነው? ከአማሌቃውያን ንብረት አንዳች አታስቀር ተብለህ አልነበረምን?» አለው። ሳኦል ግን «ሕዝቡ በጌልጌላ መሰዊያ አዘጋጅተን ለእግዚአብሔር መስዋዕት እናቀርባለን ብለው እነዚህን ከብቶች አመጡ።» ብሎ ምክንያት አቀረበ። በዚህን ጊዜ ነው ሳሙኤል ሳኦልን በእግዚአብሔር ቃል የገሰጸው፥ «እነሆ መታዘዝ ከመሥዋዕት ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል።» አለው። ሳኦል የእግዚአብሔርን ቃል በመናቁ ንጉሥ እንዳይሆን እግዚአብሔር ናቀው።

ሳኦል በእግዚአብሔር ፊት ምናምንቴ እና የተናቀ የሆነው ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ሰውነቱን ባለማስገዛቱ ነው። ትእዛዙን ሰማ እንጂ አላዳመጠውም፥ አልፈጸመውምም። አድርግ የተባለውን ሳያደርግ ቀረ። እግዚአብሔርን መከተል ማለት እሱ አድርጉ ያለውን ማድረግ፥ አታድርጉ ያለውን አለማድረግ ነው። ይህም በፈቃደ እግዚአብሔር መመራት ነው። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሳኦል አማሌቃውያንን እንዲያጠፋ እንጂ ምርኰ ሰብስቦ የሚቃጠልና የሚታረድ መሥዋዕት እንዲያቀርብለት አልነበረም። ሳኦል ቃሉን ሰምቶ ትእዛዙን ቢፈጽም ኖሮ እግዚአብሔር ምንኛ በተደሰተ ነበረ። ሳኦል ትእዛዙን በመፈጸም እግዚአብሔርን ከመከተል ይልቅ በፈቃደ ሥጋው በመመራት ለተገኘው ምርኰ በመሳሳት ወደ ኋላ መመለስን መረጠ። እግዚአብሔር በዚህ ተቆጣ። እግዚአብሔርን መከተል ከጀመሩ በኋላ ወደ ኋላ መመለስ ክህደት ነው።

ሳኦል ትእዛዘ እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ከፈጸመ በኋላ በወዙ በጉልበቱ ያፈራውን የሚቃጠልና የሚታረድ መሥዋዕት ቢያቀርብ ኖሮ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እግዚአብሔር በደስታ በተቀበለው ነበር። ዳሩ ግን እግዚአብሔር የዓመፀኞችን መባ አይቀበልም። ትልቁ ዓመፅ የእግዚአብሔርን ቃል ሳይፈጽሙ መገኘት ነው። በማዳመጥና በመታዘዝ በምናቀርበው ነገር ነው እግዚአብሔርን ደስ የምናሰኘው፤ አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥን መሥዋዕት በእምነት ለእግዚአብሔር በማቅረቡ ጻድቅ እንደሆነ ተመስክሮለት ሞቶም ሳለ እስከአሁን በመሥዋዕቱ ይናገራል። ዕብ.11፥4። ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ ንጹሕ መሥዋዕት በማቅረቡ እግዚአብሔር ተቀብሎታል። መዐዛ መሥዋዕቱን አሸትቶ «ምድርን ዳግመኛ ስለ ሰው አልረግምም» ብሎ ቃል ገብቶለታል። ዘፍ.8፥20። እግዚአብሔር የአብርሃምን፥ የይስሐቅን፥ የያዕቆብን፥ የሌሎችንም ደጋግ አባቶች መሥዋዕት የተቀበለው ፍጹም ታዛዦች በመሆናቸው ነበር። ለምሳሌ አበ ብዙኃን አብርሃም «ከአገርህ ውጣ ከዘመዶች ተለይ እኔ ወደማሳይህ አገር ሂድ በተባለ ጊዜ ሁሉንም ትእዛዝ ፈጽሞ ተገኘ። መሠዊያም አዘጋጅቶ የእግዚአብሔርን ስም ጠራ። በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር የጠራቸው የጋበዛቸውና የመረጣቸው ነቢያት ሐዋርያት ቅዱሳን ሁሉ እግዚአብሔርን በማድመጥና ለእርሱም በመታዘዝ እስከመጨረሻው ተከተሉት።

ሳኦል ገን እግዚአብሔርን ከመከተል ወደ ኋላው ተመለሰ። ዴማስ ሆዴ ይሙላ ደረቴ ይቅላ ብሎ ጳውሎስን ከመከተል ይልቅ ወደ ዓለም በመመለሱ ቅዱስ ጳውሎስ አዝኖበታል። 2ጢሞ.4፥9። ዴማስ ወደ ኋላው የተመለሰው እግዚአብሔርን ከመከተል ነበረ። እግዚአብሔር ከጠራውና ከመረጠው ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ነበርና። ሳኦልንም ሆነ ዴማስን ወደ ኋላ የጐተታቸው የዚህ ዓለም ነገር ነበረ። የሎጥን ሚስት የጨው ሐውልት አድርጐ ያስቀራት በመላእክት አንደበት የተነገራትን የእግዚአብሐርን ትእዛዝ ተላልፋ ልቧ ወደ ኋላ በመመለሱ እና በመንሸራተቱ ነበር።

ዛሬ የምንኖርባት ዓለም ያጨናን ቅናት እንደሳኦል እንደ ዴማስ እና እንደ ሎጥ ሚስት ያለን ሰዎች ነን። በአለመታዘዝና በክፉ ምግባራችን እንመሳሰላለን። እግዚአብሔር በመጻሕፍት በመምህራን የሚነግረንን አናዳምጥም። ያዘዘንንም ስንፈጽም አልተገኘንም። ሳኦል የአማሌቃውያን ምርኮ እንዳሳሳው እኛም ፈቃደ ሥጋችን የሚያሳሳን ሆነን ተገኝተናል። ከዓለም የሚገኘው ጊዜያዊ የሆነ ኃላፊ ጠፊ ጥቅማ ጥቅም እግዚአብሔርን እንዳንሰማ አደነቆረን፥ እንዳንታዘዘውም አሠረን። ለምሳሌ የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ እንድናፈራ ታዝዘናል። ታዲያ ማነው አፍርቶ የተገኘ? «የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግስት፥ ቸርነት፥ በጐነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።» ገላ.5፥22። እንግዲህ ሕይወታችንን እንመርምር። ለእግዚአብሔር በመታዘዝ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ በመሆን ይህንን አፍርተናል ወይ?

ሳኦል ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ እግዚአብሔርን ከመከተል ወደ ኋላ በመመለሱ በእግዚአብሔር ፊት ተናቀ፥ ሥጋዊ ሥልጣኑን እስከማጣት ደረሰ። እኛም እንደ ሳኦል የተናቅን እንዳንሆን ታላቁን መንፈሣዊ ሥልጣን የእግዚአብሔር ልጅ እንባል ዘንድ ሥልጣንን ከሰጠን በኋላ ሥጋዊ ደማዊ ፈቃዳችንን ስንፈጽም አንገኝ። እንዲህ በማድረጋችን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እናፈርሳለንና።

በአሳባችን፥ በንግግራችን፥ በሥራችን እያመነዘርን ብንጾም ብንጸልይ፥ ብንሰግድ፥ ብንመጸውት ስንዴውን ወይኑን ጧፉን ዘይቱን ንዋየ ቅድሳቱን ለእግዚአብሔር ብናቀርብ ዋጋ የለውም። አስቀድመን ሰውነታችንን ለሕገ እግዚአብሔርና ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እናስገዛ። ከዚህ በኋላ የምንጾመው ጾም የምንጸልየው ጸሎት፥ የምናቀርበው መባዕ ለበረከት ለረድኤት ይሆናል። የብርሃን አምላክ እግዚአብሔር ብርሃነ ረድኤቱን ያበራልናል። መታዘዛችን እንደ አቤል እንደ አብርሃም እንደ ሌሎችም ይሁን። ደቀመዛሙርቱ እርሱን በመከተል እስከመጨረሻው በመታዘዛቸው ሀብት መንፈሳዊ ርስት ሰማያዊ የእነርሱ ሆነ ቀርበው የሚያቀርቡ ሆኑ።

እንግዲህ በእግዚአብሔር መሠዊያ ፊት ከመንበርከካችን ስሙን ከመጥራታችን በፊት ሕይወታችንን እንመርምር። ማንነታችንን በእግዚአብሔር ቃል እንመዝን። «መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያ ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ አስቀድመህ ከወንድምህ ጋር ታረቅ። በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።» ይላል ማቴ.5፥23። ይህ አምላካዊ ቃል የሚያዝዘን አስቀድመን ከወንድሞቻችን ጋር እንድንተራረቅ ሰላምን እንድንመሠርትና የፍቅርን ሸማ እንድንለብስ ነው። ከዚህ በኋላ የምናቀርበውን ማናቸውንም ነገር እግዚአብሔር ይቀበለዋል። የማይታዘዝ ሰውነት ይዘን እግዚአብሔርን አድርግልን ቅዱሳንን አስደርጉልን ብለን መለመን አይቻልም።

ለመሆኑ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ለእግዚአብሔር የምናቀርበው መሥዋዕት ምንድነው? በሕዝ. 18.30 «ንስሐ ግቡ ኃጢአትም እንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ። የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ። አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ የእሥራኤል ቤት ሆይ ስለምን ትሞታላችሁ። የሞዋቹን ሞት አልፈቅድምና ይላል ጌታ እግዚአብሔር ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ።» ያለውን ትእዛዝ በመፈጸም ሰውነታችንን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ ነው። ሮሜ.12፥1። ይሄኔ እኛነታችንን ይቀበለዋል። እርሱ እኛነታችንን ከተቀበለው እኛ የምናቀርበው ሁሉ በፊቱ የተወደደ ይሆናል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ.6፥16 «ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ።» ብሏል። እንግዲህ ለሞት ያውም ለዘላለም ሞት የኃጢአት ባሪያዎች ከመሆን ለእግዚአብሔር በመገዛት መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት እንዲሆንልን የመታዘዝ ባሪያዎች ብንሆን ይሻለናል። መታዘዝ ከሁሉ ይበልጣልና አብርሃም ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ወደ ምድረ ከነዓን እንደገሠገሠ እኛም ወደ ቤተ ክርስቲያን ወደ ገነት መንግሥተ ሰማያት እንገስግሥ። ሳኦል ንጉሥ እንዳይሆን የናቀው አምላክ እኛም ልጆቹ እንዳንባል እንዳይንቀን።

ከሳኦል ሕይወት እንደተማርነው እግዚአብሔር ከሚቃጠል እና ከሚታረድ መስዋዕት ይልቅ መታዘዝን መረጠ። በብሉይ ኪዳን ለኃጢያት ስርየት የእንሰሳትን ደም ያፈሱ ነበር። በአዲስ ኪዳን ግን ይህ ሁሉ ቀርቶ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነውር የሌለበት በግ ሆኖ በመስቀል ላይ ሥጋውን በመቁረስ ደሙንም በማፍሰስ የዘለዓለም መሥዋዕት ስለሆነልን ዕለት ዕለትም በቤተ መቅደስ አማናዊ ሥጋው ስለሚቆረስና አማናዊ ደሙም ስለሚፈስ፥ እርሱ ባለቤቱም በዮሐ.6፥51–56። ሥጋዬን ብሉ ደሜንም ጠጡ የዘለዓለም ሕይወት ይኖራችኋል ብሎ ባዘዘን መሠረት ከኃጢአታችን ነጽተን ከበደላችን ታጥበን የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረን ሥጋውን መብላት ደሙን መጠጣት አለብን። ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# ዓምደ ወራዙት

(የወጣቶች ዓምድ)

በዚህ ዓምድ ለመንፈሳውያን ወጣቶች የሚጠቅሙ ማናቸውንም ዓይነት ትምህርቶች፥ ምክሮችና አስተያየቶች እናስተናግዳለን።

## ካልባረክሽኝ አልለቅህም

ከዲ.ደጀኔ ሽፈራው

በረከት ለቤታቸው እንግዳ አይደለም። አባቱ ይስሐቅ አያቱ አብርሃም በእግዚአብሔር ተባርከዋል። ያዕቆብ ስለ እግዚአብሔር በረከት ጥቅም አሳምሮ ያውቃል። በሕይወቱ ዘመን ሁሉ በረከት እንዲትረፈረፍለት በመፈለጉ እግዚአብሔርን «ካልባረከኝ አልለቅህም» አለው። እግዚአብሔር የበረከት አምላክ ነውና።

ያዕቆብ የስሙ ትርጓሜ ‹ተረከዝን ይይዛል› ማለት ነው። ሲወለድ የወንድሙን ተረከዝ ይዞ ተወለደ ዘፍ.25፥19–26። ርብቃ ለይስሐቅ ከወለደችለት መንትዮች ታናሹ እና የአሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ሕዝብ ነገዶች አባት ነው። ዔሳውና ያዕቆብ በሆድ ሳሉ ይገፋፉ ነበር። ርብቃ እግዚአብሔርን ብትጠይቅ ታላቁ ለታናሹ እንደሚገዛ ተነግሮአታል።

ያዕቆብ ባደገ ጊዜ የወንድሙን ብኩርና ገዛ ዘፍ.15፥27–34። በሚጠፋው የማይጠፋውን ለወጠ። ተከታይ ባይኖርም መጀመሪያ ከማኅፀን የወጣ ልጅ በኩር ይባላል። ዔሳው «እነሆ እኔ ልሞት ነው ይህች ብኩርና ለምኔ ናት?» ብሎ ተስፋ ቆርጦ እንደ ታላቅነቱ በአባቱ እጅ የሚባረካትን በረከት በእንጀራና በምስር ወጥ ለውጦ ቃሉን በመሐላ አጸና።

ያዕቆብ እንጀራና ወጥ ይቅርብኝ አባቴ እጁን በመጫን የሚያሳድርብኝ የእግዚአብሔር በረከት ይሻለኛል በማለቱ የበረከት ባለቤት ሆነ። እግዚአብሔር አብርሃምን በባረከበት ቃለ በረከት ይስሐቅ ያዕቆብን ባረከው። ሳመው። የልብሱንም ሽታ አሸተተ። የልጄ ሽታ እግዚአብሔር እንደባረከው እርሻ ሽታ ነው አለ። እግዚአብሔር ከሰማይ ጠል ከምድርም ስብ የእህልንም የወይንንም ብዛት ይስጥህ። አሕዛብ የገዙልህ። ሕዝብም ይስገዱልህ ለወንድሞችህ ጌታ ሁን። የእናትህም ልጆች ይስገዱልህ። የሚረግምህ እርሱ ርጉም ይሁን። የሚባርክህም እርሱ ቡሩክ ይሁን።» ብሎ መረቀው። ዘፍ.27፥27–29።

ያዕቆብ ብኩርናውን የሸጠለት ወንድሙ ተቆጭቶ ሊገድለው ባለ ጊዜ ከቤርሳቤህ ወደ ካራን ሄደ ዘፍ.27፥42፤ 28፥10። ወደ ካራን ከመሄዱ በፊት ሚስት ያገባ ዘንድ በአባቱ ተባርኳል። አባቱ ይስሐቅ «ሁሉን የሚችል አምላክም ለብዙ ሕዝብ ጉባዔ እንድትሆን ይባርክህ። ያፍራህ ያብዛህ ስደተኛ ሆነህ የተቀመጥህባትን እግዚአብሔርም ለአብርሃም የሰጣትን ምድር ትወርስ ዘንድ የአብርሃምን በረከት ለአንተ ይስጥህ። ለዘርህም እንዲሁ እንደ አንተ።» ብሎ ደጋግሞ መረቀው። ዘፍ.28፥1–5።

ያዕቆብ በምድረ ሎዛ ተኝቶ ሳለ በሕልሙ መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ ጫፉም እስከ ሰማይ ደርሶ እግዚአብሔር በላይ ቆሞበት መላእክት ሲወጡበት ሲወርዱበት አየ። የአያቱ የአብርሃም አምላክ የአባቱ የይስሐቅ አምላክ ባረከው። የአብርሃምን ተስፋ ሰጠው። ያዕቆብ እግዚአብሔር የተገለጠበትን ስፍራ አከበረ። «ከእንቅልፉ ተነስዖ በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው። እኔ አላወቅሁም ነበር አለ። ፈራ እንዲህም አለ። ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራ ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም። ይህም የሰማይ ደጅ ነው።» ብሎ በዚያ ቦታ ሐውልት አቆመ። ዘይትም አፈሰሰበት። እግዚአብሔር ከእሱ ጋር ቢሆን በመንገዱ ቢጠብቀው የሚበላውን እንጀራ የሚለብሰውን ልብስ ቢሰጠው ወደ አባቱም ቤት በጤና ቢመልሰው እግዚአብሔር አምላኩ ለሐውልት የተከለው ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት እንደሚሆን ከሚያገኘው ከአሥር አንዱን (አሥራቱን) እንደሚሰጥ ቃል ገባ። ዘፍ.28፥20–22።

ያዕቆብ ለእናቱ ወንድም ለላባ ሃያ ዓመት አገለገለ። ሚስት አግብቶ ልጆችን ወለደ። ብዙ ከብትም አገኘ። ዘፍ.29፥30። እግዚአብሔር ወደ ከነዓን እንዲመለስ ባዘዘው ጊዜ ከአጎቱ ከላባ ቁጣ ከወንድሙም ከዔሳው ቁጣ ጠበቀው። ዘፍ.31፥32፥33።

ያዕቆብ ወደ ከነዓን ሊመለስ በጕዳና ሳለ አስቀድሞ ለወንድሙ ለዔሳው እጅ መንሻ ልኮ ከብቶቹንና ቤተሰቦቹን የያቦቅን ወንዝ ካሻገራቸው በኋላ ለብቻው ቀረ። በዚያችም ሌሊት እስከ ንጋት ድረስ እግዚአብሔር በሰው ተመስሎ ታገለው። የፍቅርና የሰላም ትግል ነበር። የጭኑንም ሹልዳ ነክቶ እግሩን አደነዘዘው። ሊነጋጋ ሲል እግዚአብሔር ያዕቆብን ልቀቀኝ አለው። ያዕቆብ ግን «ካልባረክሽኝ አልለቅህም» ሲል መለሰ። እግዚአብሔርም ከእንግዲህ ስምህ እሥራኤል ይሁን። ከእግዚአብሔርም ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና ብሎ ባረከው። ያዕቆብም እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ ብሎ አመነ። ዘፍ.32፥22–30።

ያዕቆብ በእምነትና በምግባር አባቱን ይስሐቅንና አያቱን አብርሃምን መስሎና ሆኖ ተገኘ። እግዚአብሔርም የአብርሃም የይስሐቅ አምላክ እንደተባለ የያዕቆብ አምላክ ተባለ። ወጣቱ ያዕቆብ በረከትን ለማግኘት ብዙ ደከመ። እንደደከመም አልቀረም በትጋቱ በአባቱም በእግዚአብሔርም ተባረከ። ወጣትነቱን ለእግዚአብሔር አስገዛ። አካሄዱንም



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ። በዚህም የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ልጅ ሆነ።

ያዕቆብ ያገኛት በረከት የዔሳው ነበረች። ዔሳው የብኩርናውን በረከት ንቆ ለሆዱ ተገዝቶ አሁን በልቶ ኋላ ሊርበው ለእንጀራና ለወጥ አድልቶ ተገኘ። ለእለት እንጀራ ብሎ ዘለዓለ ማዊቱን በረከት አጣ። በወንድሙ ቂም ያዘ። አባቱ ከጠላቸው ወገኖች ሚስት አገባ። በገዛ እጁ ተጠላልፎ ወደቀ።

እንግዲህ ዛሬም እግዚአብሔር እንደ ያዕቆብ ያለ ብላቴና ይፈልጋልና ሆነን እንገኝ። ይጣራልና አቤት እንበል። ያዕቆብን በእናቱ ማኅፀን ሳለ የመረጠ አምላክ እኛንም ከቤተ ክርስቲያን ይመርጠናል። እሷ በንስሐ የምታጥበን ሥጋውን የምትመግበን ደሙን የምታጠጣን ጸጋውን የምታ ለብሰን እናታችን ናትና።

አባቶችን ሳንንቅ ለመባረክ እንቅረብ። ይስሐቅ ያዕቆብን እደባረከ ይባርኩናል። በረከት በአባቶች እጅ ከእግዚአብሔር ነውና። እንደ ዔሳው የአባቶችን በረከት አንናቅ፥ ኋላ እንደ እሱ እንዳይቆጨን፤ ሕይወት የማይ ሆን እንጀራ አያስጐምጀን። ሆዴ ይሙላ ደረቴ ይቅላ እንጂ በረከት ምን ሊያደርግልኝ? አንበል። በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስም ከእግዚአብሔር ነው።

ያዕቆብ በሕልሙ ጫፉ ሰማይ በደረሰ መሰላል እግዚአብሔርና መላእክት እንደተገለጡለት እኛም በዚህች ሕልም በሆነች ዓለም የመሰላሏ ምሳሌ የሆነች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን እግዚአ ብሔርንና መላእክትን የምናይበት ዓይነ ልቡና ይኑረን። ያዕቆብ ያን ሥፍራ እንዳከበረ ዛሬም የእግዚ አብሔር ቸርነት የሚገለጥባትን ሥጋ ውና ደሙ የሚፈተትባትን፥ የድንግል ማርያም አማላጅነት፥ የቅዱሳን መላ እክት ተራዲኢነት የሚፈጸምባትን ቤተ ክርስቲያን እናክብር። እግሮቻ ችን በዚያ ዘወትር እንደሐውልቱ ይተከሉ። በሚያደርግልን ሁሉ ከእግዚአብሔር ላለመለየት ቃል እንግባ። አሥራቱን በኩራቱን ቀደሚ ያቱን እንስጥ። ቤተ ክርስቲያን በረከት የሚዘንብባት የሰማይ ደጅ ናት። ጥምቀቷ ወደ እግዚአብሔር መንግ ሥት የሚያስገባ ቁርባኗ (ሥጋውና ደሙ) የዘለዓለም ሕይወት የሚሰጥ ነው። ታዲያ ከዚህ የበለጠ የሰማይ ደጅ ከየት ይምጣ። ከምድር ወደ ሰማይ እንደ መላእክቱ የምንወጣበት መሰላልም ድንግል ማርያም ናት። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሥፍራ ናት።

ወገኖቼ ያዕቆብ ያቺን ሥፍራ የእግዚአብሔርን ሥፍራ፥ የሰማይን ደጅ፥ የእግዚአብሔርን ቤት ዓይቶ እንደፈራ፥ እኛስ የምንፈራውና የእግ ዚአብሔርን ቤት ከመድፈር የምንጠበቀው መቼ ነው? ዛሬ ብዙ ደፋሮች መወለድ ሳይሆን ተፈልፍለናል። እንደ አሸን ፈልተናል። እንደ ሰኔ ሰርዶ ቀና ቀና ብለናል። ለበረከት ሳይሆን ለሥጋ ተድላና ደስታ እየሮጥን ነው። መቅረባችን በሕግ በአምልኮ አይደለም። «በምን አለበት» ተመር ዘናል። መንፈሣዊ አገልግሎት አይታ ይብንም። እንደ ዔሳው የዕለቱን ነው የምናስበው ይህ ማክተም አለበት።

ያዕቆብ ከፈጣሪው እንደታገለ የፈጣሪን ሕግ ለመፈጸም ትእዛዙን ለመጠበቅ እንታገል። በጾም በጸሎት በስግደት በምጽዋት ተወሰነን እምነ ትን ከምግባር አዋሕደን ካልባረከን አንለቅህም እንበለው እግዚአብሔ ርን፥ እሱን ለቅቀን ማንን ልንይዝ ነው? ከእሱ ውጪ ሁሉ መርገም ነው። ያዕቆብ ሰውንም እግዚአብሔ ርንም ታግሎ እንዳሸነፈ በቀና እምነታችን በበጎ ምግባራችን በፍቅር በትህትና በየዋህነት፥ በገርነት የምናሸንፍ እንሁን። እግዚአብሔ ርንም ሰውንም ለማሸነፍ አስቀድሞ ፈቃደ ሥጋን ማሸነፍ ያስፈልጋል። ማሸነፍ ማለት ሰውና እግዚአብሔርን ማስደሰት ማለት ነው።

ወገኖቼ ጠቢቡ ሰሎሞን በመክ.12፥1 «የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ» እንዳለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በ2ጢሞ.2፥22 «ከክፉ የጐልማስነት ምኞት ግን ሽሽ» ባለው መሠረት ወጣትነታችንን ለእግዚአብ ሔር በማስገዛት የበረከት ሰዎች እንሁን። ንጉሥ ሳኦልና ዴማስ እግዚአብሔርን ከመከተል ወደኋላ እንደተመለሱ እኛም ከመጣን በኋላ አንመለስ፥ ከቀረብን በኋላ አንራቅ። 1ሳሙ.15፥11፤2ጢሞ.4፥9 ሐዋ ርያዊት ታሪካዊት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በኩር ናት። ስለዚህ አንሽጣት።

በዚህ በአዲስ ዓመት ለእኛ አዲስ ልብ እና አዲስ መንፈስ እናድርግ። ሕዝ.18፥31። በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት በማመን ሥጋውን በመብላት ደሙንም በመ ጠጣት አዲስ ሰው እንሁን 1ቆሮ.5፥17። አለበለዚያ አዲሲቷ ሰማይና ምድር አዲሲቷ ኢየሩሳሌም መንግሥተ ሰማያት አትገኝም። ራእይ.21፥1–4። የበረከት ሰው እንዲለን የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ ቸርነትየድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን። ✣

## በክርስቶስ

ሊለካ የማይችል ፍቅር
ሊሞት የማይችል ሕይወት
ሊደመሰስ የማይችል ጽድቅ
ሊረበሽ የማይችል ሰላም
ሊታወክ የማይችል ዕረፍት
ሊጠፋ የማይችል ደስታ
ሊያሳዝን የማይችል ተስፋ
ሊቀንስ የማይችል ክብር
ሊጨልም የማይችል ብርሃን
ሊደክም የማይችል ብርታት
ሊረክስ የማይችል ቅድስና
ሊያልቅ የማይችል በረከት
ሊሻር የማይችል ጥበብ

ወዘተ. አግኝተናል ታዲያ እኛስ እነዚህን ጸጋዎች ተቀብለን ልንጠ ቀምባቸው ምን ያህል ተዘጋጅ ተናል? እነዚህ ጸጋዎች በእኛ ላይ እንዲያድሩ ምን ያህል ተቀድ ሰናል? መልሱን ለራሳችን። ✣

ከወጣት ተስፋዬ ፈይሣ (ወልደዮሐንስ)



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «መዳን በክርስቶስ ብቻ ነው።» እንዴት?

ዲያቆን ተከለ ወልድ

ሰው ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት በማመን ይድናል። ቅ.ጴጥሮስና ቅ.ዮሐንስ በዘጠኝ ሰዓት ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስ ሲገሠግሡ ያገኙትን እግረ ሽባ ብላቴና በመፈወሳቸው ሕዝቡ ተገርመውና ተደንቀው ነበር። የሐዋ.3፥10። ቅ.ጴጥሮስ ለሕዝቡ የእሥራኤል ሰዎች ሆይ በዚህ ስለምን ትደነቃላችሁ ወይስ በገዛ ኃይላችን ወይስ እግዚአብሔርን በመፍራታችን ይህ ይመላለስ ዘንድ እንዳደረግነው ስለ ምን ትኩር ብላችሁ ታዩናላችሁ? በማለት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማራቸው። የሕዝቡ ችግር ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አለማወቅና አለማመን ነበረ። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑን አለመረዳታቸው እንጂ የእግዚአብሔርንማ አምላክነት ያውቃሉ። ማወቅ የተሳናቸው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅነት ነው።

ለምሳሌ አይሁድ «እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም አንድ አባት አለን እርሱም እግዚአብሔር ነው» ብለው ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን «እግዚአብሔርስ አባታችሁ ከሆነ በወደዳችሁኝ ነበር። እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና» ብሏቸዋል። ዮሐ.8፥41። እንግዲህ ለዚህ ሕዝብ መንገርና ማስተማር የሚያስፈልገው ስለ እግዚአብሔር አብ ሳይሆን በተለየ አካሉ በሥጋ ስለተገለጠው ስለ እግዚአብሔር ወልድ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር።

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርነት ወንጌላዊው ዮሐንስ «ቃልም እግዚአብሔር ነበረ... ቃልም ሥጋ ሆነ» በማለት ገልጦታል። ዮሐ.1፥1–14። ሐዋርያው ቅ.ጳውሎስም «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» በማለት ለቤተ ክርስቲያን (ለምእመናን ሁሉ) ደሙን ያፈሰሰውን ኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔር ብሎ ጠርቶታል። የሐዋ.20፥28።

በዘመኑ አይሁድ እግዚአብሔርን እናምናለን እያሉ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ጐን በመተዋቸው አዳኝነቱን በመካዳቸው አምላክነቱን በመጠራጠራቸው ሐዋርያት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ብቻ ማስተማር ግድ ሆኖባቸዋል። «መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» በማለት መዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ላላመኑ አይሁድ እነ ቅ.ጴጥሮስ አስተማሯቸው። የሐዋ.4፥12። ሐዋርያው ዮሐንስ «ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው» በማለት 1ዮሐ.2፥23። አብና ወልድ የማይበላለጡ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ተናገረ መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ ጋር ትክክል ነው።

ይህን ሁሉ የዘረዘርነው ያለ ምክንያት አይደለም። አንዳንድ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የሚክዱ ሰዎች «መዳን በክርስቶስ ብቻ ነው።» በሚለው እውነተኛ የክርስትና ትምህርት ሽፋፍነው በበራሪ ጽሑፍ (ትራክት) ላሰራጩት የክህደት ትምህርት መልስ ለመስጠት ነው።

በዚህ የክህደት ጽሑፋቸው መግቢያ ላይ «መዳን በክርስቶስ ብቻ ነው» ብለው በትልቁ ጽፈዋል። በእርግጥም ክርስቶስን የባሕርይ አምላክ ብሎ ማመን ብቸኛ የመዳኛ መንገድ ነው። ወደ ዝርዝር ሃሳቡ ስንገባ እነዚህ ክፍሎች ከላይ በርእስ የተጻፈውን በአግባቡ የተረዱት አይመስሉም። ለክህደታቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ እንሰጥበታለን።

1ኛ. መዳን የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ አይደለም በማለት ለዚህም ቅ.ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የላከውን መልእክት ማስረጃ እንዲሆንላቸው በማስመሰል ጠቅሰውታል። (ሮሜ.3፥20)።

ዳሩ ግን ቅ.ጳውሎስ «የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና» ሲል ሕግን አትጠብቁ አላስፈላጊም ነው ሥርዓት አልበኛ ሁኑ ማለቱ አይደለም። አስቀድመን ይህን ሊልበት የቻለበት ምክንያት ምንድር ነው ብለን ብንጠይቅ ከአይሁዳውያን መካከል ወደ ክርስትና በተመለሱትና ከአሕዛብነት ወደ ክርስትና በተመለሱት መካከል ክርክር ተነሣ። ከአይሁድ ወገን የተመለሱት ክርስቲያኖች እኛ ሕግ በመጣበቃችን ነው የዳነው



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በማለት ይታበዩ ጀመር። በዚህም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመውን ቤዛነት እንዳያቃልሉ ሕግን በመጠበቃቸው ሳይሆን በእግ ዚአብሔር ፍጹም ቸርነተ መዳናቸ ውን ከልባቸው እንዲያምኑ ብሎ «የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው» ብሎ የክርስቶስን የቤዛነት ሥራ ገለጠላቸው እንጂ ሕግን መጠበቅ አይጠቅምም አላለም።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞት ብቻ ሳይሆን የተላለፈልን ሕግንም በመጠበቅ ስለ እኛ ተላልፎ ልናል። በተወለደ በስምንተኛው ቀኑ ሕግ ለመፈጸም ወደ ቤተ መቅደስ ወስደውታል። «ሁሉንም እንደ ጌታ ሕግ ከፈጸሙ በኋላ ወደ ገሊላ ወደ ከተማቸው ወደ ናዝሬት ተመለሱ» ሉቃ.2፥39።

በአሥራ ሁለት ዓመቱ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ መውጣቱ ሕግ ሊፈጽም ነበር። «እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይመስላችሁ። ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪ ያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ» የሚለውም የጌታ ቃል የሚያስገነዝበን ይኸንኑ ነው። እንግዲህ ጌታ ፈጽሞ ያሳየንን፥ ሕግ ሠርቶ የሰጠንንም ሕገ ወንጌል እየጠበቅን ልንከተለው ይገባናል። ጌታ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ሕግን መጠበቅ እንዲገባ እያስተማረን ገና ሰማይና ምድር ሳያልፍ ሕግን መጠበቅ አይገባንም የሚሉ ወገኖች መታየታቸው እጅግ የሚያሳዝን ሲሆን ዛሬ ሕጉን ካስጣሉን ነገ ደግሞ የሕጉን ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስን ሊያስጥሉን መነሣታቸውን ያሳያል።

በክርስቶስ መዳን ማለት የዘለዓለ ምን ሕይወት ማግኘት ነው። አንድ ሰው ወደ ጌታ ቀርቦ «የዘለዓለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ» ባለ ጊዜ «አትግደል» አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፥ አባትህንና እናትህን አክብር፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ የሚለውን ሕግ እንዲጠብቅ ተነግሮታል።

ቅ.ጳውሎስ በገላትያ 2፥6 ላይ «ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን ዐውቀን ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ እና ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል» ብሎ የተናገረውንም ለአስረጂነት አቅር በዋል። ቅ.ጳውሎስ ይኸንን የጻፈበት ምክንያት አለው። እሱ በእስር ቤት ሳለ ቢጽ ሐሳውያን በሕዝቡ መካከል ገብተው ወንጌል ያለ ኦሪት ጥምቀት ያለ ግዝረት አይጠቅምም ብለው አስተማሯቸው። እንዲህ ተብሎ የተሰ በከው ሕዝብ በአምልኮተ ጣዖት በገቢረ ኃጢአት ቆይቶ በቅ.ጳውሎስ ስብከት ወደ ወንጌል የመጣ እንጂ ሕገ ኦሪትን ሲፈጽም ተስፋውን ሲጠባበቅ የኖረ አልነበረምና ተስፋ ቆረጠ። በዚህ ምክንያት ሊያጽናናቸው ይኸንን ጻፈላቸው እንጂ ሕግ መጠበቅ አይጠቅምም ማለቱ አይደለም። ሕግ በመጠበቃቸው ቀርቶ ክርስቶስን በመስቀላቸው እንኳ ይታበዩ፥ ይመኩ የነበሩትን በዚህ ጽሑፉ አሳፈራቸው። የገላትያንም ሰዎች እንዴት በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን እምነታችሁን (ወንጌልን) ትታችሁ ወደ ሕገ ኦሪት አፈገፈጋችሁ? ወንጌልን እሽቀንጥሮ ጥሎ በኦሪት በማመን ብቻ መዳን የለም አላቸው። እንግዲህ ይህ ትምህርት የሚያስፈልገው ወንጌልን አንቀበልም ላሉ አይሁድ ጥምቀትን አንቀበልም ላሉ አሕዛብ እንጂ ክርስትናን ገና በ34 ዓ.ም. ለተቀበልን ለእኛ ለኢትዮጵያውያን አይደለም። አለማስተዋል እንጂ ሕጉም ነቢያቱም የሚናገሩት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ፊልጶስ ናትናኤልን አግኝቶ ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉ ትን የናዝሬቱን ኢየሱስ ክርስቶስን አግኝተነዋል ማለቱ ለዚህ ነው። ዮሐ.1፥46። ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ሉቃስና ቀለዮጳን በጐዳና ባገኛቸው ጊዜ «ከሙሴና ከነቢያት ጀምሮ ስለእርሱ በመጻሕ ፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላ ቸው» ይላል ሉቃ.24፥27። ዳግ መኛም ለደቀመዛሙርቱ ተገልጦ የተቸነከሩትን እጆቹንና እግሮቹን አሳይቶ አብሮአቸው ከበላና ከጠጣ በኋላ «ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው» ብሏቸዋል። ሉቃ.24፥44። የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን። ✣

ይቀጥላል

## መጽሐፈ ጨዋታ

### ክፍል 5

እግዚአብሔር ለዓለሙ ሁሉ አንድ በግ ሰደደ፤ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ለተራቡ። እናንተ ምእመናን ሥጋውን በልታችሁ፤ ምናልባት ባይባቃችሁ ደሙን ጠጡት። ኦሪት ደም አትጠጡ እያለች ረሃብ ትሞታላችሁን፤ ዛሬ ጠጥታችሁ ከሞት ዳኑና በኋላ ንስሐ ትገባላችሁ። እና ንተ የዚህ ዓለም ነጋዴዎች ከዚህ ከአንድ በግ ሥጋ ተቀራምታችሁ ምነው ስንቃ ችሁን ብትይዙ።

ጴጥሮስና ጳውሎስ መድኃኒት ያላቸው ይመስለኛል። የሞተውም የታመ መውም ይነሣላቸዋልና። እንዲህ ያለ ግርማ ከታብ ሰፍተው ይዘው ይሆን፥ ኧረ ገና ከታባቸውንማ ደህና እንደሆነ እናውቀው የለምን ጴጥሮስስ ያለሁለት ከታብ፥ ጳውሎስ ያለ አሥራ አራት ከታብ ምን ከታብ አላቸው፤ እንኳን መድኃኒቱንስ በልተውታል በሆዳቸው ነው አሉ።

ምድርንስ ተገዝርአቸው ቢላት ገደልና ዱር በባሕርም እየሆነች ለምን ታው ከናለች። ደግሞም እግዚአብሔር አንድ ልጁን አስተምራት ብሎ ቢሰድላት ልጁን አስደብድባ አስገደለችውና ዋጠችው። ጤናም አልሆናት በዋጠችው በሦስተኛው ቀን አስመለሳት። ለሆድ እውጥ እውጥ ማለት ምንድነው?



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

**በዚህ ዓምድ ክርስቲያኖች በማኅበራዊ ኑሮአችን ልንመስል የሚገባንንና የኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ኑሮ በምን ላይ ተመሥርቶ ሊመራ እንደሚገባው ለማውሳት እንሞክራለን።**

## ትዳርና ሕይወት

ከግርማ ወ/ሩፋኤል

«...ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል» ይላሉ አበው የኑሮን ውጣ ውረድ አቋምና መልክ ካጤኑ በኋላ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እኔ እስከዚች ቀን ድረስ በመልካም ኅሊና ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ኖሬአለሁ» ሐዋ.23፥1። በማለት የተናገረውም የኑሮን ምንነት ሊነግረን ፈልጐ ነው።

መቼም ኑሮ ማለት ለኖረው እንጅ ለቆጠረው እምብዛም አይገባውም « ማሽላ እያረረ ይስቃል» ዓይነት ሆኖ እየኖረ በኋላ በ50 ወይ በ60ዎቹ ኖርኩ ቢል አረረ–ተከነ እንጂ ኖረ አይባልም። የኑሮን ጣዕም ዓላማና ግብ ሳይረግጥ እንደ ውኃ ላይ ኩበት ሲዋልል ከርሞ በኋላ ሲያረጅ ኖርኩ ቢል ቆጠረ–ዘመንን በዘመን ላይ ደመረ እንጂ ኖረ ልንለው አንችልም።

የዚህ የኑሮ ቀመር ብዙዎችን ሲያስጨንቃቸው ሲያሳስባቸውና ለትርጉሙም ጣዕም ሲያሳጣቸው ይታያል። ምክንያቱም የኑሮ መዋቅሩ የሕይወት ድንበሩ ከመጀመርያው ሲቀረፅ ከመሠረቱ ሲታነፅ ዓላማውና ግቡ ሂደቱና ውጤቱ ሳይታሰብበት በግብታዊነት ስለሚወጠን ነው።

የኑሮ አቋም ከሚጸናባቸው፥ የሕይወት መሠረት ሥር ከሚይዝባቸው ምዕራፎች አንዱ ደግሞ ትዳር–ጋብቻ ነው፤ ለሰው ልጅ የተሰጠ ጸጋ–ከፈጣሪያችን። ታዲያ ይኸን ጸጋ በሚገባ ተጠቅሞ ሕይወትንም በጽኑ መሠረት ላይ አቁሞ ፈጣሪ የሚገለገልበት፥ የኑሮ ጣዕም የሚታወቅበት፥ የበረከት ፍሬ የሚታፈስበት መልካም ትዳር ይሆን ዘንድ ከጋብቻ በፊትና በኋላ ሊታሰቡ ሊገነቡ የሚገባቸው ነገሮች አሉ።

እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኰሚሽን የትምህርተ አበ–ነፍስ ክፍል ኃላፊ ከቀሲስ ከፍ ያለው መራሒ ጋር ያደረግነውን ቃለ–መጠይቅ ይዘን ቀርበናል ከልቡና ሰብሰብ ከሃሳብ ቆጠብ ብለን እናዳምጣቸው ያወጉናል:- ገጠመኞቻቸውን ጭምር።

ሐመር – በእጮኝነት ዘመን ካሉ ሁለት ፍቅረኛሞች መካከል ከሁለት አንዳቸው በክርስትና ሕይወት ያልጠነከሩ ቢሆኑና ከሁለት አንዳቸው ባይስማሙ፥ ነገር ግን ፍቅራቸው እንዳለ ቢሆን ምን ዓይነት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል ይላሉ?

ቀሲስ – ይህ በአጭሩ የመንፈሳዊ ትምህርት ማነስ ይመሥለኛል። ክርስቲያን ወጣቶች በሥጋዊው ፍልስፍና እንደሚራቀቁ በክርስትና ሕይወታቸውም መጽሐፍ ቅዱስን፥ ቀኖና ቤተ–ክርስቲያንና ሥርዓተ ጋብቻን በሚገባ ቢማሩና ቢያውቁ ኖሮ፥ ስለ ክርስቲያናዊ ጋብቻ በቂ ግንዛቤ ሊኖራቸው በቻሉ ነበር።

ሁለቱ ፍቅረኛሞች እስከተዋደዱ ድረስ መለያየት የለባቸውም። ያመነው ጠንካራው ወገን ያላመነውን ለማሳመን መሞከር አለበት ካልተቻለም ለመምህረ ንስሐው ነግሮ ያላመነውን ወገን በቂ ትምህርት እንዲሰጠው ማድረግ ይኖርበታል እንጂ በቀላሉ መለያየት የለባቸውም።

ሐመር – እንደሚታወቀው የቤተ ሰብን ብዛት ለመመጠን የወሊድ መቆጣጠሪያን መጠቀም በአሁኑ ጊዜ የተለመደ ሆኗል። ይህን ሁኔታ በክርስትና ሕይወት ውስጥ እንዴት ይመለከቱታል? ምክንያቱም ብዙ ሰዎች ወሊድ መቆጣጠሪያ ስለምንወስድ ልንቆርብ አንችልም ሲሉ እንሰማለንና።

ቀሲስ – በእኔ አስተሳሰብ ከጋብቻ በኋላ ቤተሰብን በዕቅድ መምራት ለሚለው ጥያቄ ዕቅዱ ከጋብቻ በፊት ቢሆን መልካም ይመሥለኛል። ከጋብቻ በፊት የሚደረገው መሠረታዊ የጋብቻ ጥናት ከጋብቻ በኋላ የሚመጣውን ኃላፊነት ለመሸከም የሚያስችል ይሆናል ብዬ ስለምገምት ነው።

ለሁሉም ነገር ትምህርት ዋና መሠረት ነው። አበው «ከመጠምጠም ትምህርት ይቅደም» እንዲሉ ወጣቶች ለትዳር ከመመራረጣቸው በፊት ጋብቻ ስለሚሰጠው ማኅበራዊና መንፈሳዊ ጥቅም ጠለቅ ያለ ትምህርት መማር ያስፈልጋቸዋል። ሾላ በድፍኑ እኔና አንቺ ከተዋደድን በሚል ጭፍን አስተሳሰብ ትዳር ከተመሠረተ በኋላ መጨረሻው ሲጠፋ ምነው የተገናኘን ዕለት በሞትኩ ማለት ይመጣል።

ስለጋብቻ መሠረታዊ ዓላማዎች ስናስብ የመጀመሪያውና ሊታወቀን የሚገባው ጉዳይ ለመረዳዳትና አንድ ለመሆን እንዲሁም ዘር ለመተካት ሲሆን፥ ይህም አስቀድሞ በተነገረው በኦሪት ሥርዓት ዘፍ.2፥25 ዳግመኛም በወንጌል ማቴ.19፥5 ተረጋግጧል።

የቤተሰብን ብዛት ለመመጠን የወሊድ መቆጣጠሪያን መጠቀም ለሚለው ጥያቄ ቤተክርስቲያን እስከአሁን



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

አልፈቀደችም። ወደፊትም ቢሆን ጉዳዩ በጣም የሚያወያይ ነው። ሕይወት ላለው ነገር ሁሉ መመገብ፥ ማደግ፥ መራባት ወዘተ. የተፈጥሮ ሕግ እንደሆነ ይታወቃል። ነገር ግን «ተፈጥሮን እንቆጣጠራለን» የሚለው መፈክር በክርስትናው አይሠራም።

በመሠረቱ ቤተ–ክርስቲያን ሕይወት ያለውን ዘር የማምከኑን ኢ–ተፈጥሮአዊ የሆነ ፍልስፍና ያልፈቀደችበት በቂ ምክንያት አላት። መጋቤ ኲሉ መድኃኔዓለም በዓይን ለማየት ከሚያስቸግረው ረቂቅ ሕዋስ እስከ ታላላቆቹ ድረስ ፍጥረቱን ሁሉ ይመግበዋል። የእግዚአብሔርን መግቦት መጠራጠርና መቃወም የሃይማኖት ጉድለት ነው። እግዚአብሔር አምላክ «ብዙ ተባዙ» ሲል ለሰው ልጆች ምድር እንደሚጠብና እንደ ሚቸገሩ ሳያውቅ ቀርቶ ይመስልሃል? አይደለም። ይልቁንም ለዚህ ችግር መሠረቱ በሰዎች መካከል ፍቅርና ሰላም መጥፋት ነው። እውነተኛ ፍቅር ካለ መተሳሰብና መረዳዳት ይኖራል፤ ነገር ግን በሰዎች መካከል ፍቅር ስለቀዘቀዘች አንዱ ለውሻው ቀሚስ ሲያሰፋ ሌላው የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ አጥቶ በምድር ላይ ስቃዩን ያያል። ለምሳሌ፥ የመጨረሻው ሀብታም ሰው በሕንድ ሀገር ሲገኝ፥ በአንፃሩ ደግሞ የመጨረሻው ድሃና በረንዳ አዳሪ ከስልጣኔ ቁንጮ ደርሳለች ከምትባለው ሰሜን አሜሪካ ይገኛል። እስቲ ይህን የማኅበራዊ ኑሮ ዕንቆቅልሽ ምንትለዋለህ? በበኲሌ ሁለት ያለው አንዱን ይስጥ የምትለውን የፍቅር ሕግ ማስተማር ብቻ ነው መፍትሔው እንጂ የወሊድ መቆጣጠሪያ ኪኒን አይመስለኝም። ቁርባኑን ለሌሎች ምክንያቶች ብሎ ከመሸሽ ይልቅ በእምነት ብንቀርብ የምንፈልገውን የቤተሰብ ምጣኔም ሆነ የተስተካከለ የቤተሰብ ሕይወት እናገኘው ነበር።

ይህም ለብዙ ሰዎች ከሥጋ–ወደሙ መሸሽ ምክንያት እየሆነ መጥቷል ስላልከው በእውነት እኔ አልቀበለውም ምክንያቱም ስለእውነት ከሆነ ለእኛ ለክርስቲያኖች ከሥጋ ወደሙ በላይ መድኃኒት ሊኖረን አይችልም። የዘለዓለምን ሕይወት የሚሰጥ የነፍስና የሥጋ መድኃኒት ምሥጢረ ቁርባን ብቻ ነው። በባልና ሚስት መካከል እውነተኛ መተሳሰብ ካለ ከእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ ውጭ አርቲፊሻል መድኃኒት ሳይጠቀሙ ሁሉን ነገር በመመካከርና በመተሳሰብ አቅም በፈቀደ መጠን ራስን በመግዛት ለጾምና ለጸሎት ቅድሚያ በመስጠት ጤናማ ማኅበራዊ ኑሮ መኖር ይቻላል። ጠቢቡ «ለሁሉም ጊዜ አለው» ያለው ለዚህ ነው። መክ.3፥5

**ሐመር** – ስለጾም ካነሡ አይቀር ሁለት በትዳር ላይ ያሉ ባልና ሚስት በጾም ወቅት ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ቢያስረዱን።

**ቀሲስ** – ለዚህ ጥያቄ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ተገቢውን መልስ ሰጥቷል። ባልና ሚስት ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ ራሳችሁን ስለአለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈትናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ» ይላል። 1ቆሮ.7፥5።

በዚህ መሠረት ሊቃውንት አባቶቻችንም በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ቁጥር 920 ላይ ሰፋ አድርገው አትተዋል። ከዚህ በተረፈ ግን ባልና ሚስት አንድ አካል አንድ አምሳል ስለሆኑ ለጾምና ለተለያዩ የሱባኤ ጊዜያት ካልሆነ በስተቀር መለያየት የለባቸውም።

**ሐመር** – እዚህ ላይ ቀሲስ፥ ሁለት ነጥቦች ባነሣ። አንደኛ በባልና ሚስት መካከል የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከቅዱስ ቁርባን በፊትና በኋላ ስላለው ጊዜ፥ በተጨማሪም በወር አበባ ጊዜ ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ለመሳተፍ ምን ያህል መቆየት እንደሚያስፈልግ ቢገልጹልን።

**ቀሲስ** – እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ–ክርስቲያናችን ትምህርትና ሥርዓት ከቅዱስ ቁርባን በፊት አንድ ቀን፥ ቅዱስ ቁርባን ከተቀበሉ በኋላ ደግሞ ሁለት ቀናት መታቀብ እንደሚገባ አበው ሊቃውንት በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ቁጥር 926 ላይ በሚገባ ስለተገለጸ የሕጉን መጽሐፍ መመልከት ይጠቅማል።

እንዲሁም በሉቃስ ወንጌል ምዕ.1፥24 ላይ ያለውን ጥቅስ መሠረት በማድረግ ቅዱስ ያሬድ «እምድኅረ ክልኤ መዋዕል ጸንሰት ኤልሳቤጥ ብእሲቱ» ከሁለት ቀናት በኋላ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ጸነሰች ብሎ ተርጉሞታልና በሕጉ ብንመራ መልካም ነው።

የወር አበባን (ልማደ አንስትን) በተመለከተ «ትክታሃ ለብእሲት ጽጌሃ ውእቱ» ዮሐንስ አፈወርቅ በሃይማኖት አበው አንዲት ሴት የወር አበባ ስታይ ልጅ ለመውለድ (ዘር ለመቀበል) ዝግጁ መሆኗን የሚያስረዳ ምልክት እንጂ በልማድ እንደሚነገረው የመረገም ምልክት አይደለም ብሏል። በመሠረቱ መርገም ሁሉ በክርስቶስ ደም ተሽሮአል፥ ተደምስሷል። ሴቶች በወር አንድ ጊዜ ለተወሰኑ ቀናት የሚያዩት የወር አበባ የተፈጥሮ ሕግ እንጂ ከውጭ በስህተት ያመጡት የእርግማን ምልክት አይደለም።

የቀደሙት አባቶቻችን በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕ.12 ላይ የተጻፈውን መሠረት በማድረግ በፍትሐ–ነገሥት ሰፋ አድርገው አትተዋል። (ፍትሐ: ነገሥት አንቀጽ 6 ቁጥር 235።) ይኸውም ሴቶች ከወር አበባ እስኪነጹ ድረስ ይታቀቡ ሲሉ የሰጡት ምክንያት:-

1ኛ. ብዙ ደም ሲፈሳቸው ኃይል ያጣሉ፥ ይደክማቸዋል፥ ቆሞ ለማስቀደስና ለመስገድ ጉልበታቸው ይቀንሳል፥



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

2ኛ. በቅዱሱ የጸሎት ቤት ደም ሲንጠባጠብ ለተመልካች ደስ አያሰኝም በዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሕግ ሠርተዋል።

ይህም የሴቶችን ድካም ለማቃለል ተብሎ የታሰበ ይመስለኛል።

የወር አበባ ክርስቲያን ሴቶችን ከቤተክርስቲያን የሚያርቅ ርኩስ ነገር አይደለም። ለምሳሌ:- በማርቆስ ወንጌል ምዕ.5፥25 ላይ በሚገባ እንደ ተገለጸው ከአሥራ ሁለት ዓመታት ጀምሮ ደም የሚፈሳት ሴት (በተአምረ–ኢየሱስ ስሟን ‹ዮስቴና› ብለው ይጠሯታል) በአደባባይ ሮጣ የክርስቶስን ዘርፈ ልብስ ስትነካ ያለማቋረጥ የሚፈሰው ደሟ ቆሞላታል። የክርስቶስን የልብሱን ዘርፍ ለመንካት አልተከለከለችምና።

ሐመር – አባታችን እንዲያው በዚህ አጋጣሚ በቆይታችን ማብቂያ ጠቅለል አድርገው ከሕይወት ልምድዎ በመነሣት ለዘመኑ ትውልድ የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ?

ቀሲስ – አንድ ወጣት በመጀመሪያ አካላዊና አእምሮአዊ ብቃት እስኪኖረው ድረስ ንጽሕናውን ጠብቆ በትምህርትና በሃይማኖት ታንጾ ማደግ አለበት። ቀጥሎም አንድ (አንዲት) ወጣት በክርስትና ሕግ መሠረት ሥርዓተ ጋብቻውን በቤተ–ክርስቲያን ለመፈጸም ሲያስብ የትዳር ጓደኛውን ለመምረጥ ከዚህ በሚቀጥሉት ጥያቄዎች በቅድሚያ ራሱን ይመርምር።

ሀ. ልጅቱ መንፈሳዊት ናትን?

ለ. ከእኔ ጋር በአምልኮተ–እግዚአብሔር ጸንታ ለመኖር ትችላለች?

በማለት በቅድሚያ እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች መመርመር ያስፈልጋል። ጥያቄዎቹ ለሁለቱም ፆታዎች ያገለግላሉ።

የባልና የሚስት በሃይማኖት መመሳሰልና መተሣሠር የመልካም ጋብቻ መሠረት ስለሆነ ይህም ደግሞ ቤተ–ክርስቲያን የምትደግፈውና እግዚአብሔርም የሚቀበለው በመሆኑ ለዚህ ክቡር ጋብቻ ቤተ–ክርስቲያን «ኑ ወደእኔ» እያለች እጆቿን ዘርግታ ትጠራለች።

ከጋብቻ በኋላ ባል ሁልጊዜ ሚስቱን ለማስደሰት መጣር ይኖርበታል ሚስትም እንዲሁ፤ ምክንያቱም የእርሷ ደስታ ደስታው፤ መከራዋ መከራው ነውና። የትዳር ዓለም ሁልጊዜ እንደማር ወለላ ጣፋጭ ብቻ ሊሆን አይችልም። አንዳንድ ጊዜም እንደሬትና እንደኮሶ የሚመርና የሚያንገፈግፍ ውስብስብ ፈተና ሊያጋጥም ይችላል። ነገር ግን ጋብቻው በእውነተኛ ፍቅር ላይ የተመሠረተ እንጂ የይድረስ ይድረስና በችኩልነት እፍ–እፍ ባለ ፍቅር ላይ የተመሠረተ ካልሆነ፤ በትዳር ላይ የሚያጋጥመውን ዕንቅፋት ሁሉ በተቻለ መጠን ከሁለቱ ሌላ የውጭ ሰው ጣልቃ ሳይገባ፥ ባልና ሚስቱ በትዕግሥትና በጥበብ ለችግሩ የጋራ መፍትሔ መፈለግ ይኖርባቸዋል።

ብዙ ተጋቢዎች ስለማይተማመኑ ነው መሰለኝ ከቁርባን ሲሸሹ ይታያሉ። ነገር ግን እርሱ ያለ እርሷ፤ እርሷ ያለ እርሱ ሌላ ካልፈለጉ አንድ ሊያደርጋቸው የሚችለውን ቁርባንን ለምን ይፈሩታል። ምናልባት አንዱ ቢሞት ከዚያ በኋላ ሌላው የሚጠብቀው መመንኰስ ብቻ ነው የሚባል አባባል እንዳለ ይሰማኛል ለዚህ ግን ቅ.ጳውሎስ በ1ቆሮ. 7፥39 መልሱን ሰጥቷል «ሴት ባልዋ በሕይወት ሳለ የታወረች ናት፥ ባልዋ ቢሞት ግን በጌታ ይሁን እንጂ የወደደችውን ልታገባ ነፃነት አላት» እናም እርስዋ ካልፈለገች/ካልፈለገ ና መንኵስ የሚለው (የሚላት) የለም። በመሆኑም ቆርባ ልታገባ (ሊያገባ) ይችላል። እንዲያው መተማመን እየጠፋ እንጂ መጠራጠር ካለኰ መጋባቱ ባልተገባ ነበር።

በተክሊል መጋባት ማለትም ከሥነሥርዓቱ በኋላ መጥፋት ማለት አይደለም ዘወትር በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ ማስቀደስ፤ መቁረብ መማር፥ ንስሐ መግባት ያስፈልጋል።

## የሪፖርተሩ ማጠቃለያ

እስካሁን ድረስ ከቀሲስ ጋር ባደረግነው ቆይታ መቼም ብዙ ቁም ነገሮች እንደቀሰምን እንተማመናለን በዚሁ አጋጣሚ ታዲያ በማኅበራዊ ኑሮ ዙሪያ ያላችሁን ጥያቄዎች ብታቀርቡልን ሌሎችንም አባቶች ወደመድረክ ጋብዘን እናወያያለን። ለዛሬው ግን በዚህ እናብቃ።

እግዚአብሔር በቸር ያገናኘን። አብረውን ስለቆዩ እግዚአብሔር ይስጥልን ቀሲስ። ✥

## መጽሐፈ ጨዋታ
## ክፍል 4

መላእክትስ ጠጅና ሥጋ አይወዱም ይሆን? ለሰው ልጆች በሥጋ ሲያደላ አይተው ይሆን? ምነው ጌታቸው ሲሰቀል ዝም አሉ? ጌታቸው ሲሰቀል ከቶ ወዴት ሸሹ። ምናልባት እንደ እርሱ እንሞታለን ብለው ይሆን። መንጋ ፈሪ በሰማይ ተሰብስቦ ሰይፍን አስረዝሞ ቢቆሙት ካልቆሙበት ምን ይሆናል። የፈሪ በትሩ አሥር ነው እንዲሉ።

ይልቅስ ሥጋ የለበሰው፤ ጠጅ የጠጣው ጴጥሮስ ይሻላል፤ የማልኮስን ጆሮ በሰይፍ የመነጠረው።

እንግዲህ መላእክት ከሥጋና ከጠጅ ይከልከሉ ጌታቸውን ብቻውን አስደብድበውታልና።

ይልቁንስ ፀሐይና ጨረቃ ተሸልሞ መኖር ይገባቸዋል፤ የጌታቸውን ራቁትነት ሲያዩ ብርሃናቸውን ሰውረዋልና፤ ከዋክብትም ረግፈዋልና ክብር ይገባቸዋል። ሃያ አራቱ ቄሶችስ ወዴት ሄደው ነው፤ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ የቀበሩት የጦር ቀን ያልሆነ ሎሌ ለመቼ ነው።

ምድርስ የእግሩ ጫማ አልነበረችምን፤ እንዴት መቃብር ሆነችው። ወይ ጊዜ፤ ለካ ንጉሥ ሰሎሞን ለሁሉ ጊዜ አለው ያለው እውነት ነው።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# በረከተ ወንጌል

በዚህ ዓምድ ሥር የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በተከታታይ እናቀርባለን።

በሰው ልጆች የመዳን ጉዞ እና በአምላካችን የማዳን ሥራ ውስጥ ትልቁን ቦታ ይዞ የሚገኘውንና ቅ/ሉቃስ ከትቦ ያስቀመጠልንን የቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት ስንመለከት ለራሳችን ሕይወት የሚበጁ ብዙ ድንቅ ቃላትን እናገኝበታለን።

እመቤታችን ከቅዱስ ገብርኤል ጋር ተነጋገረች፥ አበሠራትም ከብዙ ጥያቄና መልስም በኋላ «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም» በሚለው ቃል ብሥራቱን ተቀበለች። ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተመልታ አመሰገነቻት፥ ዮሐንስም በማኅፀን ሆኖ ሰገደላት። ከዚህ በኋላ ነበረ እመቤታችን አንደበቷን ከፍታ ይህንን የምስጋና ቃል የተናገረችው። የእግዚአብሔር ድንቅ ምስጢር ስለተገለጠባት፥ የተናገረችው ነገር መንፈስ ቅዱስ ያቀበላት፥ የአምላካችን የ5500 ዘመን ዕቅድ ፍጻሜ፥ የሰው ልጆች መዳን የምሥራች ነበረ። ይህ ብሥራት በእኔ ንጽሕናና ቅድስና ምክንያት የመጣ ነው አላለችም። ይልቁንም ራሷን ዝቅ አድርጋ ነፍሴ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች አለች። ሰይጣን ሰዎችን የሚጥልበት ጥበብ እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ጸጋ እነርሱ በራሳቸው ኃይል ቅድስና ወይም ንጽሕና እንዳገኙት ማድረግ ነው። ብዙዎችም የወደቁት በዚሁ ነው። በቅርቡ እንኳን በምድረ አሜሪካ የተነሣው ሐሳዊ መሲሕ ዴቪድ ኮሬሽ «መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ከሆነ እኔ ክርስቶስ ነኝ» ማለቱ የዚሁ የሰይጣን ዓላማ መሆኑን የሚያሳይ ነው። እመቤታችን ግን «የባሪያይቱን መዋረድ (ትሕትና) ተመልክቶ ይህንን አደረገ» አለች። በዚህ አባባሏ የሔዋንን ቃል ነበረ የተናገረችው። ለ5500 ዘመን የሰይጣን ባርያ ሆና የኖረችውን ሔዋንን ከዕፀበለስ መቁረጥና ከእግዚአብሔር ሕግ መጣስ በኋላ ሔዋን ከእግዚአብሔር ልጅነት ተለይታ በሰይጣን ባርነት ትኖር ነበረ። የሰውን መንገላታት የማይፈልገው አምላክም ራሱን ዝቅ አድርጎ ሰው

## «ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል።»

(ሉቃ.1፥47–55)

ከኤፍሬም እሸቴ

ሆነ። መላእክት ዘወትር ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ የሚያመሰግኑት አምላክ፥ ላዩ እሳት ውስጡ እሳት የሆነ በመላው ዓለም የመላ ጌታ በዚያች ትንሽ ማኅፀን አደረ። ስለዚህም እመቤታችን «ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል» አለች። በእውነቱ ይህ የሚደንቅ ነገር ነው። ታላቁ አባት አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ላይ፥

«እሳተ መለኮት በሆድሽ ባደረ ጊዜ ፊቱ እሳት ልብሱ እሳት ቀሚሱ እሳት ነው፥ እንደምን አላቃጠለሽም ሰባት የእሳት ነበልባል መጋረጃ በሆድሽ ወዴት ተዘጋጀ...ትንሽ አካል ስትሆኚ...»እያለ ጽፏል።

ሰማዩን ያለዓላማ፥ ምድርን ያለካስማ ያቆመ አምላክ ያደረባት ይህች ትንሽ ማኅፀን የተመሰገነች ናት፥ አዳምንና ሔዋንን የፈጠረባትን እጅ የዳሰሰች የተመሰገነች ናት፥ እሳተ መለኮትን የሳመች አፍ የተመሰገነች ናት። ጌታችንን ይዛ ወደ ግብፅ በረሃ የተሰደደች እግር የተመሰገነች ናት፥

ስለዚህ ነው እመቤታችን «ከዛሬ ጀምሮ...ብላ...ትውልድ ሁሉ» በሚል ቃል የደመደመችው። ትውልድ ሁሉ ማለት የአዳም ልጅ በሙሉ ማለት ነው። ዛሬ ግን የአዳም ልጅ የዚህ ቃል ተጠቃሚ አልሆነም፥ የተጻፈለትን ትቶ ባልተጻፈለት ነው የሚመራው። የመንፈስ ቅዱስንም ቃል ወደጐን ብሏል። ቅዱስ ጳውሎስ «እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል» ሮሜ.8፥33። ብሎ የጠየቀውን ጥያቄ ዛሬ ሰዎች መልስ ሰጥተዋል። እግዚአብሔር የመረጣቸውን እኛ እንከሳቸዋለን» እያሉ ነው። ይህንንም የእመቤታችንን ቃል በመተዋቸው ልናረጋግጥ እንችላለን።

እመቤታችን በእርሷ ታላቅ ሥራን ያደረገው እግዚአብሔር መሆኑን፥ ትዕቢተኞችን የበተነ፥ ገዥዎችን ከዙፋናቸው ያዋረደ፥ ትሑታንን ደግሞ ከፍ ከፍ ያደረገ፥ የተራቡትን በበረከት የመገበ፥ ባለጠጐችን ደግሞ ባዶ እጃቸውን የሰደደው፥ ከቀደሙ አባቶችም ለአብርሃምና ለይስሐቅ የማዳን ቃሉን የተናገረ አሁን ለእኔ ድንቅ ነገር አደረገልኝ አለች። ስለዚህ በመንፈስ ቅዱስ ቃል መታዘዝ ታላቅ በረከትን ያስገኛል። ብዙ ቅዱሳን በዚህ ቃል ተመርተው በበረከትና በጸጋ ተትረፍርፈዋል። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው» መዝ.118፥105 ማለቱ በእግዚአብሔር ቃል ሙሉ በሙሉ እንደሚመራ ያሳያል። ዛሬ ግን ከእግዚአብሔር ቃል እየቀነጨብን እኛ በፈለግነው ሥጋችንና የራሳችን ሃሳብ በፈቀደው መንገድ ለመምራት እንፈልጋለን። ቃል እግዚአብሔር ግን



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

እኛ በፈለግነው መንገድ ሲሄድ የምንሳፈርበት አለበለዚያ ደግሞ የምንተወው የከተማ አውቶቡስ አይደለም። የእግዚአብሔር ሰዎች በሙሉ የተመሰገኑት ሙሉ በሙሉ ያለመጠራጠር በማመናቸው ነበር። አብርሃም ልጅህን ሰዋልኝ የሚል ቃል ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ ወደኋላ አላለም። ነገር ግን እምነቱን ዓይቶ እግዚአብሔር የበለጠ ክብርን ሰጠው። ዘፍጥ.22፥1–8። ሕዝቅያስ ትሞታለህ ነገር ግን ሐዘን እንዳይሰማህ እንዳታለቅስ ተባለ። በዚያች የሞትና የጣር ሰዓት ትእዛዙ የእግዚአብሔር ነውና ሐዘንና ልቅሶን ከራሱ አራቀ በዚህም 15 ዓመት በዕድሜው ላይ ተጨመረለት።

ታላቁ ነቢይ ሆሴዕ ጋለሞታ ይቱን፥ ራሷንም የሸጠችውን (በዛሬ አነጋገር ሴትኛ አዳሪ የሆነችውን) እንዲያገባ ሲነገረው በፍጹም ታዘዘ፥ ሚስቱ ራሷን ለግልሙትና ከሸጠች በኋላ እንደገና ገዝተህ አምጣት ሲባልም እምቢ አሻፈረኝ አላለም ቃሉ የእግዚአብሔር ነውና ሆሳዕ.1፥2።

የዘመናችን ሰው ግን ራሱ ለሚሠራው የውሸት ቤት ዓለት የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል እየጠራረበ፥ እየሸራረፈ እርሱ እንደሚመቸው እያስተካከለ ለቤቱ ግንብ ማድረግ ይፈልጋል። የተወደዳችሁ ክርስቲያኖች፥

ኖህ 120 ዘመን በተስፋ ቃሉን ጠብቆ በመኖሩ በንፍር ውሃ ከመቀቀል ድኗል፥ ዮሴፍ ሕጉን በመፍራቱ ክብርን አግኝቷል፥ ሎጥ ወደ ኋላህ አትመልከት ያለውን በመስማቱ የጨው ሐውልት ከመሆን ድኗል። ብዙ ቅዱሳን ታዘዙ...ተመሰገኑ...የዘላለም ሕይወት አገኙ። እንታዘዝ...እንቀበለው...እንመሰገን በታለን።

ሰይጣን ግን ሰዎች የዚህ ቃል ተጠቃሚዎች እንዳንሆን ዓይነ ልቡናችንን ሰውሮ ልባችንን በትዕቢት ነፍቶ ዘለላ ስንኝ እየጠቀሰ ወደማንወጣበት ማጥ ሊመራን ይፈልጋል። ነገር ግን በሕይወታችን ሁሉ ልንቃወመው በእግዚአብሔርም ኃይል ልንፈታው ያስፈልጋል። ክርስትናችን ክርስትና የሚሆነው ቃሉና ሕጉ መመሪያችን ሲሆን ነው። ከትዕቢት ይልቅ ትዕግሥትን፥ ከሐሜት ይልቅ ምስጋናን፥ ከስርቆት ይልቅ መስጠትን፥ ከዘፈን ይልቅ መዝሙርን፥ በመጠጥ ከመስከር ይልቅ ራስን መግዛትን፥ በዝሙት ከመቃጠል ይልቅ በተክሊል በቅዱስ ቁርባን ተወስኖ መኖርን፥ ጉቦ ከመቀበል በአድልዎ ከመፍረድ ይልቅ ትክክለኛ መሆንን፥ በሥልጣን በሀብት ከመመካት ይልቅ በእግዚአብሔር መመካትን፥ ቅዱሳንን ከማዋረድና ከመናቅ ይልቅ ማክበርን የተካን እንደሆነ እንደ እመቤታችን ቃሉን ተቀብለናል ማለት ነው። ክቡር ዳዊት «የእግዚአብሔር ቃል የነጠረ ነው በእርሱ ለሚታመኑት ሁሉ ጋሻ ነው» ብሏል 2ሳሙ.22፥31 ሰይጣንን የምንጋፈጥበት፥ ክፉ መንፈስ የተሞሉ ተጠራጣሪዎችን ድል የምናደርግበት፥ እምነታችንን የምናጠነክርበት ጋሻችን ነውና እንያዘው፤ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ያለንን ግንኙነት እናጠንክር ሕጉም በልባችን ይቀረፃል። ያን ጊዜ ክፉውን ከደጉ ለመለየት እንችላለን። ያን ጊዜ አንዳንዶች የወደቁበትን እኛ ግን እየፈጸምነው ያለነውን «ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል» የሚለውን ቃል ምሥጢር እንረዳለን። ያን ጊዜ ሰዎች ፍጡር ወይም ነቢይ ነው እያሉ የተሰናከሉበትን አልፋና ኦሜጋ የሆነውን የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት እንረዳዋለን። ስለዚህ ወደ ቃለ እግዚአብሔር እንቅረብ፤ አሜን። ❖

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## አማላጅ አብጁ

እመቤቴ ማርያም
ሠርግ ቤት ተጠርታ
የደጋሹን ጭንቀት
ዕፍረቱን ተረድታ
ውኃ ወይን አረገች
ለልጇ አመልክታ
ዮሐን 2፥1።

አይሁድ በባቢሎን
ሰባ ዓመት ሲገዙ
ስቃይ በዝቶባቸው
ጩኸትን ቢያበዙ
ወደ ኢየሩሳሌም
ደግም ሊመለሱ
መልአኩ ለምኗል
ቆሞ ስለነርሱ።
ዘካ 1፥12።

መልካሙ ንግግር
ባይወጣ ካፋቸው
በተናገሩት ቃል አምላክ ቢቆጣቸው
የኢዮብን ጓደኞች
ወደ ኢዮብ ላካቸው
መሥዋዕት ሠውቶ
እንዲያስታርቃቸው።
ኢዮ.42፥8።

ንጉሥ አቤሜሌክ
ሣራን ተመኝቶ
ሊወስዳት ሲፈልግ
በራእዩ ጠርቶ
ነቢዩ ነውና።
እርሱ እሚያማልደው
ልዑል እግዚአብሔር
ወደ አብርሃም ላከው
ከመረጥኳቸው ጋር
ይጸናል ኪዳኔ
መከራውም ያጥራል
ስለቅዱሳኔ
ብሎ በሰጠው ቃል
ሊሻር በማይችለው
ቅዱሳንን እምነን
ማረን እንበለው
ያምናው ጥፋታችን
በንስሐ ታጥቦ
ያሠረው ተፈትቶ ዲያብሎስ ተባትቦ
ጌታን አመስግነን ስለቸርነቱ
ስለጨመረልን ዕድሜን በያመቱ
ለወዲያኛው ደግሞ
ኑሮአችን እንዲያምር
አትለየን ድንግል ከኛ ጋር ትኑር።
ስለዚህ ዐዋቂው ጎልማሳና ልጁ
ለነፍሳችሁ በርቱ አማላጅ አብጁ
ከዲ.ክፍሌ ገ/መስቀል
ከማኅበረ ማርያም ዘጉርጉርዮስ
አ.አ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው።»

ከዲ. ሙሉጌታ ስዩም (ተክለ ጻድቅ) ዘፍቼ።

እግዚአብሔር አስቀድሞ በነቢዩ ኢሳይያስ አንደበት «በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ በመዳንም ቀን ረዳሁህ...» ኢሳ.49፥8። ብሎ የተናገረውን ቃል መሠረት በማድረግ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ሁለተኛ መልእክቱ ላይ «እነሆ የተወደደ ሰዓት አሁን ነው። እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው» 2ቆሮ.6፥2። በማለት ትምህርቱን ይጀምራል።

ሰው የመዳን ቃል ከሰማበት የሕይወት ቃል ከተማረበት ወንጌል ከተሰበከለት ጊዜ ደቂቃና ሰኮንድ አንሥቶ የመዳን ቀኑ ለእርሱ እንደ ቀረበ አውቆ በኃጢአት የተጐሳቆለ፥ በክህደት ያደፈ፥ በበደል የረከሰ ሰውነቱን በንስሐ አዘጋጅቶ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመንና ፈቃዱን በመፈጸም መዳን እንዳለበት ያስገነዝባል።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው ለሰው ልጅ በሕይወቱ ሁለት አማራጮች ብቻ አሉት እነርሱም:-

1. በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ ፈቃዱን በመፈጸም መኖርና ኋላም በዘላለማዊ ሕይወት በደስታ እና በክብር መኖር።

2. የሥጋን ፈቃድ በመፈጸም ከእምነትና ከምግባር ተለይቶ ከሰይጣን ጋር በኃጢአት መኖርና ኋላም በዘላለማዊ ፍርድ ትሉ በማያንቀላፋ እሳቱ በማይጠፋ በገሃነም እሳት በስቃይ መኖር ናቸው።

ይህ የሰው ልጅ በተሰጠው አእምሮ ተጠቅሞ መዳኑን ወይም መጥፋቱን ለይቶ የሚወስንበት ሌላ አማራጭ የሌለው ብቸኛ መንገድ ነው። ስለዚህም ነው ሰው ለመዳን ምርጫውን ማስተካከል መንገዱንም ማቅናት ስላለበት በዘመነ ኦሪት እነ ኢያሱ «የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ...እኔና ቤቴ ግን እግዚ አብሔርን እናመልካልን።» ኢያሱ. 24፥15። በማለት ያስተማሩት። በዚሁም ላይ ቅዱስ ዳዊት የመዳን መንገዱ አንድ ብቻ መሆኑንና እርሱም ከሁሉ በላይ የከበረ እንደሆነ በመረዳት ከአምላኩ የሚፈልገው የቱን እንደሆነ ገልጾ አስቀምጧል። «እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንኩት እርስዋንም እሻለሁ በእግዚአብሔር ቤት ለዘለዓለም እኖር ዘንድ።» መዝ.26፥4።

ከላይ ለማስቀመጥ እንደተሞከረው የሰው ልጅ ከሁለቱ በአንዱ መንገድ የመሄድ ምርጫ ቢኖረውም ኋላ ግን ፍርድ እንደሚጠብቀው ከቅዱሳት መጻሕፍት እንረዳለን። ነቢዩ ዳንኤል በትንቢት መጽሐፉ «በምድር ትቢያ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፥ እኩሌቶቹ ወደዘለዓለም ሕይወት፥ እኩሌቶቹ ወደዘለዓለም እፍረትና ጉስቁልና» ዳን.12፥2። በማለት ያስረዳል። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሁሉ ይድኑ ዘንድ ቢሆንም ሞትን ግን ሕግንና ትእዛዝን በመተላለፍ ወደራሱ ያመጣ የሰው ልጅ ነው። ከጥንቱ ከመሰረቱ የሰው አፈጣጠር ለክብር እንጂ ለሞትና ለውርደት አልነበረም። ይሁን እንጂ በአዳምና በሔዋን በደል የሰው ልጅ በፍርድ ወድቆ በዲያብሎስ ተረግጦ እንዳይቀር የጠፉትን ሊፈልግ በጨለማ ላሉት ሊያበራ ክርስቶስ በሥጋ ተገለጠ። ኢሳይያስ በትንቢቱ «በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ፥ በሞት ጥላ አገርም ለሚኖሩ ብርሃን ወጣላቸው።» ኢሳ.9፥2። በማለት አስቀድሞ የተናገረው ቃል በጊዜው ተፈጸመ። ጌታም በጊዜው በተገለጸ ሰዓት «በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁና።» ዮሐ.12፥46። ብሎ አስተማረ። ይህ ሁሉ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን ያደረገው በመሆኑ ሁላችን ለመዳን የተዘጋጀን መሆን አለብን።

ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ ስለክርስቶስ ሲመሰክሩና ወንጌልን ሲያስተምሩ አይሁድ በቅናት ተነሣሥተው በወኅኒ አኖሩዋቸው። በዛም እጃቸው በሰንሰለት ታሥሮ ሳለ በእኩለ ሌሊት በመዝሙር ጌታን ሲያመሰግኑ የወኅኒ ቤቱ መሠረት ተናግቶ የታሠሩበት ሰንሰለት ተበጣጥሶ መስኮቶቹ እና ደጃፎቹ ሁሉ ተከፍተው የወኅኒ ጠባቂው ቢመለከት ጳውሎስና ሲላስ ከእሥር አምልጠው የጠፉ መስሎት ደንግጦ ራሱን ሊያጠፋ ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ተመልክቶ «አይዞህ እራስህን አታጥፋ እኛ ከዚህ አለን» ብሎ ሲመልስለት በሁኔታው ተደንቆ የጠየቀው አንድ ታላቅ ጥያቄ ነበር። እርሱም በፊታቸው ተደፍቶ «ጌቶቼ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» ነበር ያለው። እነርሱም የመለሱለት ቢኖር «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ።» ሐዋ.16፥30–31። አዎ መዳን ለምንፈልግ ሁሉ መልሱ ይኸው ነው። እያንዳንዳችን እንድን ዘንድ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ይገባናል። የወኅኒ ጠባቂውም ወዲያውኑ አምኖ እንደተጠመቀና እንደዳነ ነው የምንረዳው። ይህ የሚያመለክተን የመዳን ቀናችን ቃሉን የሰማን ዕለት መሆኑን እና



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ቃሉን ስንሰማ ወንጌሉ ሲሰበክልን ሁላችን ሳናመነታ ለመዳን መቅረብ እንዳለብን ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ «በአፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና፥ በአፉም መስክሮ ይድናልና። መጽሐፍም በእርሱ የሚያምን አያፍርም ይላልና።» ሮሜ.10፥8። በማለት በእርሱ አምነን ስለእርሱ መስክረን እንደምንድን ያስተምረናል። የጌታም ፈቃዱ በስሙ አምነን ቃሉንም መስክረን እንድንድን ነው። «ልጅን ዓይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው አስነሣዋለሁ።» ዮሐ.6፥40። በክርስቶስ ክርስቲያን የሚለውን ስም በማግኘታችን በስሙ መጠራት ብቻ ሳይሆን ክርስቶስን በሕይወታችን ልንይዘው ልንመሰክረው ይገባል። ክርስቲያን መባላችን ወይም ከክርስቲያን ቤተሰብ መገኘታችን ብቻውን አያድነንም። እኔ ዲያቆን ነበርኩ፥ እኔ የቄስ የመነኩሴ ዘር ነኝ፥ በማለት መመካት ብቻውን ያለእምነትና ምግባር ሊያድን አይችልም። ይህንን ስል የክህነት ታላቅነትን ለማቃለል፥ የምንኩስናን ማዕረግ ለመንካት ሳይሆን አባቶቻችን እምነትን ከምግባር ጋር በመከወን ያገኙትን ሥልጣንና መጠሪያ እኛም እምነትን ከምግባር ጋር አዋሕደን ልንከተላቸው ሲገባ በስማቸው ብቻ እየታበይን የኃጢአት ተገዢ መሆናችንን ለመንቀፍ ነው። እንኳንስ ሌሎቹ እመቤታችን እንኳን በቃና ዘገሊላ ልታማልድ በተነሣችበት ሰዓት ጋኖቹ ሞልተው ውኃው የወይን ጠጅ ይሆን ዘንድ የሚላችሁን አድርጉ ነው ያለችው።

ጌታ ሲያስተምር በአብርሃም ጽድቅ ሲመኩና ሲታበዩ ባያቸው ጊዜ «የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር» ዮሐ.8፥39። እያለ ነው የገሰጻቸው። ስለዚህ ‹ነበርኩ› የሚለውን ቃል ወይም አባባል ትቶ ሆኖ መገኘት ይጠቅማል። እንደዚህ ከሆነማ ዛሬ ተዋርዶ የጨለማ ገዥ የሆነ ዲያብሎስም እኮ የመላእክት ሁሉ አለቃ ነበር። ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ ጌታ ያስተማረውን ሲያስቀምጥ «ክርስቶስን ዐውቄዋለሁ የሚል ትእዛዙንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነት በእርሱ ዘንድ የለም...በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን። በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል።» ፩ዮሐ.2፥4። እንደ ሥጋ ፈቃድ ብንመላለስ ግን የሚጠብቀን መዳን ሳይሆን ሞት መሆኑን ጳውሎስ ሲገልጽ «እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ።» ሮሜ.8፥12 ይላል። ከላይ በዝርዝር እንዳየነው ለመዳን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን መሠረቱ ሲሆን ግድግዳው ደግሞ ምግባር መሆኑን ሲያስረዳ፥ ትእዛዙንም መጠበቅ እንደሚገባ ጌታ አስተምሮናል። የዘለዓለም ሕይወትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ? ብሎ ጌታን ለጠየቀው ሰው የሰጠው መልስ «መልካም የሆነው አንድ ነው ወደሕይወት መግባት ብትወድ ትእዛዛትን ጠብቅ።» ነው ያለው ማቴ.19፥16። በጸጋው ድነናል፥ እምነት እንጂ ምግባር ለመዳን አያስፈልግም። የሚሉ ቢኖሩ መጽሐፉን ሊያነቡትና ቃሉን ሊረዱት ይገባል። በጌታችን መድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ብናምን ትእዛዙንም ብንጠብቅ በሥጋና በነፍስ ድነን የእግዚአብሔር ልጆች እንደምንሆን ቃሉ ያስረዳል፥ «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው።» ዮሐ.1፥12። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፥ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።» ዮሐ.14፥12። እያለ በእርሱ አምነን ሁሉን ማድረግ እንደሚቻለን አስተምሯል። ብዙዎቻችን ግን በእምነት ፍጹም ስላይደለንና በምግባርም ስንኩላን ስለሆንን እንኳን ታላቅ ነገር በጌታ ስም ለመሥራት ኢምንት ነገር እንኳን መከወን አቅቶናል። ሁሉን ማድረግ ተስኖን እሥረኞች ያደረገንም የኃጢአት ደዌ (በሽታ) ነው። ጌታ በመዋዕለ ስብከቱ «ሕመምተኞች እንጂ ባለጤናዎች ባለመድኃኒት አያስፈልጋቸውም።» ማቴ.9፥12። ብሎ እንዳስተማረ እርሱ መድኃኒት በመሆኑ እርሱን በማመን ሁላችን መዳን ይገባናል። ጌታን አምነን መዳን ያለብን ደግሞ ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ሳይሆን፥ የመዳን ቀናችን ዛሬ ቃሉን በሰማንበት ዕለት ነው። እርሱን አምነን ለመዳን ግን የልብ ዝግጅት ያስፈልጋል። «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ይላል» እንግዲህ ባሮጌ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ ቢይዙ አቁማዳው ይፈነዳል። ስለዚህ አዲስ የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ሊያዝ ይገባል። ማቴ.9፥17። ብሎ ጌታ እንዳስተማረ እኛም በአዲስ ሕይወት ከኃጢአት፥ ከተንኮል ተለይቶ በጠራና በተዘጋጀ ልቡና ጌታን ተቀብለን ለመዳን መቅረብ ይኖርብናል። ባንድ ጊዜ የኃጢአትና የጽድቅ፥ የዓለምና የክርስቶስ መሆን አይቻለንምና።

አንድ ሰው በእንግድነት ከቤታችን ተቀብለን ለማስተናገድ እንኳ የቱን ያኽል እንጨነቃለን፥ እንዘጋጃለን። የጌታ እንግድነት ግን ከሁሉ ይከብዳል (ይከብራል)። ስለዚህም ነው መጥምቁ ዮሐንስ ጌታን በመቀበል (በማመን) መዳን ታገኙ ዘንድ ጥርጊያውን አዘጋጁ የተጣመመውን አቅኑ ብሎ የሰበከው። ይህም የሚያመለክተን በትዕቢት ከፍ ከፍ ያለ ልቡናችንን በትህትና ዝቅ እንድ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org


ናደርግ በተንኮልና፥ በክፉ ሃሳብ የተጣመመ ልቡናችንን በጽድቅና በፍቅር እንድናቃና ነው። ስለዚህ በኃጢአት የደነደነ በዓለም የሰመጠ ልቡናችንን (ሕይወታችንን) በጫት፥ በሲጋራ፥ በመጠጥ፥ በዝሙት ወዘተ. የበለዘ አካላችንን በንስሐ አጥርተን በነፍሳችን የተኛነው በሥጋችን የተጋ ነው ሁሉ ዛሬ ለመዳን በተራው ለነፍስ ሥራ መንቃት አለብን። ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ «ከእንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን ዕወቁ ካመንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደእኛ ቀርቧል። እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ እና ጦር እንልበስ በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ። በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን በክርክርና በቅናት አይሁን፥ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።» ሮሜ.13፥11–14 ይለናል። እስካሁን ባለ ዘመናችን ሁሉ ለዚህ ዓለም ሥራ ለሥጋችን ሮጠናል። ያተረፍነው ነገር ቢኖር ግን ችግርና ስቃይ ነው። አባቶች ሲተርቱ «አትሩጥ አንጋጥ» እንዲሉ በቀረው ዘመናችን ደግሞ ካወቅንበት የዘላለሙን እያሰብን ለነፍሳችን ልንሮጥ ይገባናል። «በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሮጡ ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን እንዲሁ ሁሉ ታገኙ ዘንድ ሩጡ» 1ቆሮ.9፥24። ጳውሎስ ቀጠል አድርጐ ‹እነርሱ ለሚጠፋውና ለሚያልፈው እንደሚሮጡ የእኛ ሩጫ ግን ለማያልፈው ለዘለዓለሙ ክብር እንደሆነ ያብራራል። እኛ ለመዳን ፈቃደኛ ከሆንን እርሱ ግን ሊያድነን ዝግጁ ነው። «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ወደእኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና» ማቴ.11፥28።

ጌታ በሆሳዕና እለት የታሠረችውን አህያ ከነውርንጭላዋ ሂዱና ፈትታችሁ አምጡልኝ ማንም ቢጠይቃችሁ ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ እንዳለ እኛም ዛሬ ከኃጢያት እሥራት ተፈትተን የዓለምን ሸቀጥ አራግፈን የእርሱ ማረፊያ የእርሱ ማደሪያ እንድንሆን ይፈልጋል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት እሥራት ሊፈታን በፍጹም ፍቅሩ ሊዋጀን መጥቷልና በእርሱ አምነን እንድን ዘንድ ወድዷል። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን ወዷልና»ዮሐ.3፥15። በመሆኑም በጌታ ለምናምን በፈቃዱና በሕጉ ልንመላለስ በፍቅሩ ልንተሣሠር የምንፈልግ ሁሉ ጊዜውና ሰዓቱ አሁን ነው። በኋላም አይደለም። ነገና ከነገወዲያም አይደለም። ዛሬና አሁን ነው። ስለነገው የምናውቀው ነገር የለምና። ነቅተንና ተዘጋጅተን እንድንኖር ነው ቃሉ የሚያዘን። ለመዳን ቀጠሮ የለምና «ቀኒቱንና ሰዓቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ።» ማቴ.25፥13፤ 1ተሰሎ.5፥4–9። ብዙ ወገኖቻችን ለመዳን ቀጠሮ ሲያበዙ፥ ሲያመነቱ በሞት ተነጥቀዋል። ለፍርድ ተጋልጠዋል። ዛሬ ለመዳን በእርሱ ብናምን ግን አይፈረድብንም። «በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።» ዮሐ.3፥18 ይለናል። የመዳን ጊዜ አሁን ነው «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደእርሱ እገባለሁ። ራእይ.3፥20 ይላል ጌታ። ስለዚህ ሲጠራን ድምፁን ሰምተን ልንቀርበው፥ ሲያንኳኳም ልንከፍትለት ይገባናል። ኢሳይያስ በትንቢቱ «እግዚአብሔር፥ በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት ቀርቦም ሳለ ጥሩት ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም ሃሳቡን ይተው» ኢሳ.55፥6–7። የለናል። እኛ ግን በሁለት ልብ ሆነን በሁለት እግራችን እያነከስን የመዳን ቀናችንን ችላ ብለን እንገኛለን። ያለን አማራጭ ግን አንድ ነው እርሱም በክርስቶስ አምነን ፈቃዱንም ፈጽመን መዳን ነው። ዕለቱም ዛሬ ነው። ጌታ ከዓለሙም ከመንፈሳዊውም ሕይወት እየሸቃቀጡ እንዲያው በለብታ የስም ክርስቲያን ብቻ ሆነው መኖር የሚሹትን ሲነቅፍ «በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን ዐውቃለሁ። በራድ ወይንም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር፥ እንዲሁ ለብ ስላልክ በራድም ትኩስም ስላልሆንክ ከአፌ ልተፋህ ነው።» ራእይ.3፥15። እያለ ያስጠነቅቀናል። ስለዚህ ጊዜዋንና ሰዓቷን መጠቀም ያሻል። ከጌታ አፍ ከመተፋታችን በፊት ለመዳን መፍጠን ይኖርብናል። ሲያንኳኳ መከፈት፥ ሲጠራን መስማት አለብን። የጌታን ጥሪ ቸል አንበል። በስሜ የሚያፍር እኔም በክብሬ ስመጣ አሳፍረዋለሁ ይላልና። ጠቢቡ ሰሎሞን «የጭንቀትህ ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ ደስ አያሰኙም የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ ፀሐይና ብርሃን ጨረቃ እና ከዋክብትም ሳይጨልሙ» መክብብ 12፥1።


እነዚህን ሁሉ የጌታን ቃል በማመንና በመቀበል ለኃጢአታችን ይቅርታን ከጌታ ለመጠየቅ እንቅረብ። የንስሐ ፍሬ እናድርግ። መንፈሳዊ ዕውቀትን ለማዳበር መጽሐፍ ቅዱስን እናንብብ፥ ወንጌል በሚነገርበት ቦታ በመሄድ ለመማር እንወስን። «እምነት ከመስማት ነው መስማትም የእግዚአብሔርን ቃል ነው።» ሮሜ.10፥17። ስለሚለን በጸሎትና በጾም ወደጌታ እንቅረብ፥ እንትጋ የመዳን ቀናችን ዛሬ ነውና። ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



የእግዚአብሔርን ቸርነት ዘወትር ይመረምራሉን ?
BAR
ዲን ብርብር መዝናኛ
ካዛንቺስ ጠጅ ቤት



ዋጋ 3.00 ብር

አርቲስቲክ ማተሚ
ARTISTIC PRINT

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org